# ሰሙነ ሕማማት
# የሕማማት ሣምንት
# Passion Week






ሐመረ ብርሃን ቅዱስ አባ ሳሙኤል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ገዳም

**Hamere Berhan St. Abba Samuel Ethiopian Orthodox Tewahedo Monastery**

https://www.abbasamueleotm.org/

# የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ የስቅለት በዓል



# ግብረ ሕማማት ዓርብ ቀን
# Gibire Himamati
# Friday

**ነግህ**

ትእዛዝ ዓርብ በነግህ ካህናት በከበረች በቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው የዳዊትን መዝሙር ብፁዕ ብእሲ ዘኢሖረ (የዳዊት መዝሙር ምዕራፍ ፩ ቁጥር ፩) ከሚለው እስከ ተዐገሡ ወአጽንዑ ልበክሙ (የዳዊት መዝሙር ምዕራፍ 30 ቁጥር 34) እስከሚለው ድረስ ይፀልዩ።

ውዳሴ ማርያምን ሰኞን ይበሉ መሪ በሦስት ሃሌታ ስምዕዎኬ ማርቆስ ይበል።

ti’izazi (Order) On Friday 1st hour, let the priests gather in Church to pray the Song of David (Psalms 1: 1) to Psalms 30:34

Let them pray the Mondays Praise of Mary and chant the below hymn.

ትእዛዝ ዓርብ በነግህ ካህናቱ ይፀልዩ መሪዉ በዘጠኝ ሃሌታ ይበል።

በዕዝል ዜማ

በመሪ ወገን አንድ ጊዜ በመከተል በተመሪ ወገን አንድ ጊዜ ለሦስተኛ ጊዜ ደግሞ በጋራ ይባላል።

ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ

ነአምን ነአምን ነአምን ሕማሞ ለዘኢየሐምም ርግዘተ

ገቦሁ ነአምን ወቅንዋተ እደዊሁ ነአምን ዬ ዬ ዬ

ነአምን ሞቶ ወትንሣኤሁ።

በመለኮቱ የማይታመም በሥጋዉ የታመመ የእርሱን ሕማሙን እናምናለን የጐኑን መወጋት የእጀቹን መቸንከር እናምናለን ወዮ ወዮ ወዮ ሞቱንና ትንሣኤዉን እናምናለን። ይፀልዩ።

ሁሉም በአንድነት እየሰገዱ 6 በግራ 6 በቀኝ በአንድ ዓይነት ዜማ አሥራ ሁለት ጊዜ ለከ ኃይል ይበሉ።

This is chanted 12 times (6 times alternating on the right and left aisles of the Church) with prostrations and after each they recite "Our Father..."

ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወዕዘዝ ለዓለም ዓለም።

ኃይል ክብር ጌትነት ገዥነት ለዘላለሙ ለአንተ ይገባል።

For Thine is the power, the glory, the blessing, and the majesty, forever and ever.

ዐማኑኤል አምላኪየ ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወዕዘዝ ለዓለም ዓለም።

ፈጣሪዬ ዐማኑኤል ሆይ ኃይል ክብር ጌትነት ገዥነት ለዘላለሙ ለአንተ ይገባል።

Emmanuel my God, For Thine is the power, the glory, the blessing, and the majesty, forever and ever.

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወዕዘዝ ለዓለም ዓለም።

ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ኃይል ክብር ጌትነት ገዥነት ለዘላለሙ ለአንተ ይገባል።

O My Lord Jesus Christ, for Thine is the power, the glory, the blessing, and the majesty, forever and ever.

ኃይልየ ወፀወንየ ዉእቱ እግዚእየ እስመ ኮንከኒ ረዳእየ እብል ወአኮቴት

አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ

ኃይሌና አምባ መጠጊያዬ ጌታዬ ነህ ረዳት ሁነኸኛልና በምሥጋና እንዲህ እላለሁ

በሰማያት ያለህ አባታችን ሆይ ስምህ ይመስገን

The Lord is my power, strength and shelter; for you became my Holy Salvation, I say with thanks-giving

Lord’s prayer: Our Father

## አቡነ ዘበሰማያት / Abune Zebesemayat / አባታችን ሆይ / Our Father

አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ ትምጻእ መንግሥትከ ወይኩን ፈቃደከ በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር ሲሳየነ ዘለለ ዕለትነ ሀበነ ዮም ንኅድግ ለዘአበሰ ለነ ወጌጋየነ ከመ ንሕነኒ ንኅድግ ለዘአበሰ ለነ ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት አላ አድኅነነ ወባልሐነ እምኲሉ እኩይ እስመ ዚአከ  ይእቲ መንግሥት ኃይል ወስብሐት ለዓለመ ዓለም አሜን ።

Abune Zebesemayat Yitkedes Simike Timsa Mengistike Weyikun Fekadeke Bekeme Besemay Kemahu Bemedir Sisayene Zelele Ilitene Habeneyom Hidig Lene Abesane Wegegayene Keme Nihinenee Nihidig Leze Abese Lene Etabiane Igzeeo Wiste Mensut Ala Addihanene Webalihane Imkwulu Ikuy Isme Zeake  Yeite Mengist Hayl We Sebhat Lealem alem Amen.

Our Father who art in Heaven, Hallowed be thy name. Thy Kingdom come. Thy will be done On Earth as it is in Heaven.  Give us this day our daily bread And forgive us our trespasses  As we forgive those who trespass against us And lead us not into temptation But deliver us from evil one in Christ Jesus Our Lord.  For thine is the Kingdom The Power and the Glory Forever and ever. Amen.

ለአምላክ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለአምላክነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to God forever and ever.

ለሥሉስ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለሦስትነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to the Holy Trinity forever and ever.

ለማሕየዊ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለአዳኝነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to the Life giver forever and ever.

ለእዘዙ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለጌትነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to His Glory forever and ever.

ለመንግሥቱ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለመንግሥቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to His Kingdom forever and ever.

ለዕበዩ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለገናናነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to His Majesty forever and ever.

ለሥልጣኑ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለሥልጣኑ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to His Power forever and ever.

ለምኵናኑ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለፈራጅነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to His Authority forever and ever.

ለኢየሱስ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለኢየሱስ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to Jesus forever and ever.

ለክርስቶስ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለክርስቶስ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to Christ forever and ever

ለሕማሙ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለመከራው ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to His Suffering forever and ever

ለመስቀሉ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለመስቀሉ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to the Cross forever and ever

ለከ ይደሉ ኃይል ለከ ይደሉ ስብሐት ወለከ ይደሉ አኮቴት ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለመ ዓለም።

ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ለአንተ ከሀሊነት ይገባሃል ለአንተ ክብር ይገባሃል ለአንተ ከምስጋና ይገባሃል ለዘላለሙ።

Power, Glory and blessing be to my Lord Jesus Christ forever and ever.

የዓርብ ጠዋት ፩ ሰዓት ምንባባት

Friday 7 AM Readings

# የተአምረ ማርያም መቅድም
## Introductory Chant to the Miracle of Mary

ምንተኑ አዐስየኪ ዕሤተ። በእንተ ኵሉ ዘገበርኪ ሊተ። ማርያም ሠናይት ዘታፈቅሪ ምሕረተ። ሶበሰ ትትዓቀቢ ዘዚአየ ኀጢአተ። እምኢሐዮውኩ አሐተ ሰዓተ።

ምሕረትን የምትወጂ መልካሚቱ ማርያም ስለአደረግሽልኝ ሁሉ ምን ዋጋ እከፍልሻለሁ? የእኔንም ኀጢአት የምትቈጣጠሪ ቢሆን አንዲት ሰዓት እንኳን ባልኖርሁ ነበር።

በሰላመ ገብርኤል መልአክ ኦ እግዚእትየ ማርያም ሰላም ለኪ። ድንግል በኅሊናኪ ወድንግል በሥጋኪ። እመ እግዚአብሔር ጸባኦት ሰላም ለኪ። ቡርክት አንቲ እምአንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ። ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልእተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ በመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እልሻለው። በሐሳብሽ ድንግል ነሽ በሥጋሽም ድንግል ነሽ። የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናት ሆይ ሰላምታ ላንቺ ይገባል፡፡ ከሴቶች ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ። የማህፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው፡፡ ጸጋን የተሞላሽ ሆይ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና ደስ ይበልሽ።

ተአምረ ማርያም ይነበባል።

Reading of the Miracles of Saint Mary

# ከተአምረ ማርያም በኋላ

## After reading the Miracles of Saint Mary chant the following

ወላዲተ አምላክ ማርያም እንበለ ሰብሳብ ወሩካቤ። በይነ ዘአቀረብኩ ለኪ ንስቲተ ቃለ ይባቤ። ፈትቲ እሙ በረከተ አፉኪ መዓዛ ከርቤ። እስመ ለነዳይ ብእሲ ወለዘረከቦ ምንዳቤ። ኅብስተከ ፈትት ኢሳይያስ ይቤ።

ያለ ርኩሰትና ያለ ሩካቤ አምላክን የወለድሽ ማርያም ሆይ ስለአቀረብኩልሽ ትንሽ የምስጋና ቃል እናቱ የከርቤ መዐዛ ያለዉን የአፍሽን በረከት ስጭ። ኢሳይያስ ለድኃ ሰዉና ችግር ላገኘዉ እንጀራህን ስጥ ብሏልና።

ስብሐት ለኪ ማርያም በኀልቄ መላእክት ዘአርያም።
ስብሐት ለኪ ማርያም በኀልቄ ጻድቃን ዘገዳም።
ስብሐት ለኪ ማርያም በኀልቄ ርደቱ ለዝናም።
ስብሐት ወክብር ወሰጊድ ለተአምርኪ ዮም።
ወበተአምረ ወልድኪ ተፈሥሐ ኵሉ ዓለም።

እመቤታችን ማርያም ሆይ በሰማይ መላእክት ቍጥር ምስጋና ላንቺ ይገባል።
እመቤታችን ማርያም ሆይ በገዳም በሚኖሩ ጻድቃን ቍጥር ምስጋና ላንቺ ይገባል።
እመቤታችን ማርያም ሆይ በዝናሙ መዉረድ ቍጥር ምስጋና ላንቺ ይገባል።
ክብር ስግደትና ምስጋናም ዛሬ ለተአምርሽ ይገባል።
በልጅሽ ተአምር ዓለሙ ሁሉ ደስ ተሰኝቷልና።

# መቅድመ ተአምረ ኢየሱስ

## ተአምረ ኢየሱስ ከመነበቡ በፊት

## Chant before the reading of Miracles of Jesus

ኢየሱስ ክርስቶስ ጥዑመ ስም ለዘይጼዉዖ። ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብስተ ሕይወት ለዘይበልዖ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ጽዋዓ መድኃኒት ለዘይጸዉዖ። ከመ ይባርኩነ ይፈኑ አርዳአ ለጸባዒነ ይጽብዖ ወልታሁ ነሢአ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚጠራዉ ስሙ ጣፋጭ ነዉ። ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚበላዉ የሕይወት እንጀራ ነዉ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚሰዋዉ የድኅነት በግ ነዉ። ይባርኩን ዘንድ ደቀ መዛሙርቱን ይላክ። ጋሻ ጦሩን አንሥቶ የሚጣላንን ይጣላዉ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ዘአጽልእቲሁ ምስሌሁ። ወመስቀለ ሞቱ ቅድሜሁ።

አዘቅተ ወይን ገቦሁ ቍርባነ አምልኮ ሥጋሁ። ያብእነ ቤተ መርዓሁ ውስተ ደብተራሁ አመ ይትጋብኡ ለምሳሕ ሥርግዋን ሐራሁ።

ቍስሉ ከእርሱ ጋራ መከራ መስቀሉ በፊቱ የሚታሰብ ኢየሱስ ክርስቶስ ጎኑ

የወይን አዘቅት ሥጋው የአምልኮ መሥዋዕት የሆነ በቅድስና ልብስና ጌጥ የተሸለሙ ባለሟሎቹ ለምሳ በሚሰበሰቡ ጊዜ ወደ ሙሽርነቱ ድንኳን ያስገባን።

ለጥብሓ ሥጋከ ንሴሰዮ ወለነቅዐ ደምከ ንረውዮ ኢየሱስ ክርስቶስ በግዕ ዘቀራንዮ፤

ለላህይከ ገጽከ ንትሜነይ ከመ ንርአዮ። ውስተ ስያሓ ሱራፌ ለስእለትየ ደዮ። ወበሕማመ ሞትከ አምላካዊ ለቍስልነ አጥዕዮ።

የተሠዋውን ሥጋህን ተመግበን ከደምህ ምንጭ እንረካለን የቀራንዮ በግ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ

ውበትህን እናየዉ ዘንድ እንመኛለን። በሱራፌ ጽዋ ውስጥ ልመናችንን ጨምረዉ። አምላክ ሆይ ለሞት በሚያበቃ ሕማምህ ቊስላችንን አድነዉ።

ለጥብሐ ሥጋከ እጸግቦ ወለነቅዓ ደምከ እሰርቦ ኢየሱስ ክርስቶስ በግዕ ርጉዘ ገቦ።

አይሁዳዊ ከሃዲ አሚነ ሥላሴ ዘአልቦ። ኢተወልደ እማርያም ዘይቤለከ እመቦ፤ አህጉራተ (ጽጌዳተ) ዓለም ለይዑድ ከመ ከልብ ርኂቦ።

ተአምረ ኢየሱስ አንብብ

Read the Miracles of Jesus

# ከተአምረ ኢየሱስ በኋላ

## Chant after the Miracles of Jesus is read

**አመ ትመጽእ ለኰንኖ መስለ ደመ ገቦ ወአእጋር። አማኅፀንኩ ነፍስየ ውስተ እዴከ ክቡር። ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአ ሰማያት ወምድር። ይትዋቀሱ በእንቲአየ ተኰርዖትከ በበትር። ወተሠይጦትከ ከመ ገብር ለኅዳጥ ብሩር።**

**ከጎንህና ከእግሮችህ ደም ጋራ ለፍርድ በምትመጣ ጊዜ። በከበረዉ እጅህ ውስጥ ነፍሴን አደራ አስጠበቅሁ። የሰማይና የምድር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራስህን በበትር መመታትህና እንደ ባሪያ በጥቂት ብር መሸጥህ ስለ እኔ ይከራከሩልኝ።**

ስብሐት ለከ ኢየሱስ በአፈ ኵሉ ውዱስ።
ስብሐት ለከ ኢየሱስ ቀዳሴ ሥጋ ወነፍስ።
ስብሐት ለከ ኢየሱስ ለዕሩቃን ልብስ።
ስብሐት ለከ ኢየሱስ ዘኢትሠአር ንጉሥ።
ስብሐት ለከ ኢየሱስ ቃለ አብ ቅዱስ።

በሁሉም አፍ የተመሰገንክ ኢየሱስ ሆይ ምስጋና ላንተ ይገባል።
ሥጋንና ነፍስን ያከበርክ ኢየሱስ ሆይ ምስጋና ላንተ ይገባል።
ለታረዙት ልብስ የሆንክ ኢየሱስ ሆይ ምስጋና ላንተ ይገባል።
የማትሻር ንጉሥ ኢየሱስ ሆይ ምስጋና ላንተ ይገባል።
ቅዱስ የአብ አካላዊ ቃል ኢየሱስ ሆይ ምስጋና ላንተ ይገባል።

# ዲያቆን ከወንጌል በፊት

# Deacon Chants Psalms before the Gospel is read

መዝ. መዝሙር ፹፩ : ፲፩ _ ፲፪

**ተንሥኡ ላዕሌየ ሰማዕተ ዐመፃ**

**ወዘኢአምር ነበቡ ላዕሌየ።**

**ፈደዩኒ እከተ ህየንተ መናይት።**

የሐሰት ምስክሮች በጠላትነት ተነሡብኝ። በእኔ ላይም የማላውቀውን ነገር ተናገሩብኝ። በጎ ስለአደረግሁላቸው ፈንታ ክፉ ብድራት መለሱልኝ። ፥

**Psalms (Mezimuri) 82: 5-6**

False witnesses did rise up; they laid to my charge things that I knew not. They rewarded me evil for good to the spoiling of my soul.

ሕዝቡም እንዲሁ ይበሉ።

**So let the people say the same way.**

ዲያቆኑ:ሃሌ ሉያ ቁሙ ወአጽምዑ ከመ ንኩን ድልዋነ ለመንግሥተ ሰማያት አ እግዚእነወ አምላክነ መሐረነ ወተሣሃለነ ወረሰየነ ድልዋነ ለሰሚዓ ወንጌል ቅዱስ።

ካህኑ: ወንጌል ቅዱስ ዘዜነወ ማቴዎስ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር።

ማቴዎስ ያስተማረውን ቅዱስ ወንጌል ይበል።

Priest says the Gospel of Matthew is the Word of God.

Read the Holy Gospel that Matthew taught.

ሕዝቡ ምሥጋና ላንተ ይገባል ይበሉ።

Let the people say thanksgiving belongs to You.

Read the Gospel of the hour

ማቴዎስ ምዕራፍ ፳፯:፩-፲፬ Matthew 27:1-14

ይ.ካ ወንጌል ቅዱስ ዘዜነዉ ማቴዎስ ወማርቆስ ሉቃስ ወዮሐንስ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር።

## የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፳፯፥፩-፲፬ (Mt. 27:1-14)

1 ሲነጋም የካህናት አለቆችና የሕዝቡ ሽማግሎች ሁሉ
ሊገድሉት በኢየሱስ ላይ ተማከሩ ፤ 2 አስረውም ወሰዱት ፥
ለገዢው ለጴንጤናዊው ጲላጦስም አሳልፈው ሰጡት።
3 በዚያን ጊዜ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ እንደ ተፈረደበት
አይቶ ተጸጸተ ፥ ሠላሳውንም ብር ለካህናት አለቆችና
ለሽማግሎች መልሶ።

[1] When the morning was come, all the chief priests and elders of the people took counsel against Jesus to put him to death: [2] And when they had bound him, they led him away, and delivered him to Pontius Pilate the governor. [3] Then Judas, which had betrayed him, when he saw that he was condemned, repented himself, and brought again the thirty pieces of silver to the chief priests and elders,

4 ንጹሕ ደም አሳልፌ በመስጠቴ በድያለሁ አለ። እነርሱ
ግን። እኛስ ምን አግዶን? አንተው ተጠንቀቅ አሉ። 5
ብሩንም በቤተ መቅደስ ጥሎ ሄደና ታንቆ ሞተ። 6 የካህናት
አለቆችም ብሩን አንሥተው። የደም ዋጋ ነውና ወደ መባ
ልንጨምረው አልተፈቀደም አሉ። 7ተማክረውም የሸክላ
ሠሪውን መሬት ለእንግዶች መቃብር ገዙበት። 8 ስለዚህ ያ
መሬት እስከ ዛሬ ድረስ የደም መሬት ተባለ።

[4] Saying, I have sinned in that I have betrayed the innocent blood. And they said, What is that to us? see thou to that. [5] And he cast down the pieces of silver in the temple, and departed, and went and hanged himself. [6] And the chief priests took the silver pieces, and said, It is not lawful for to put them into the treasury, because it is the price of blood. [7] And they took counsel, and bought with them the potter's field, to bury strangers in. [8] Wherefore that field was called, The field of blood, unto this day.

9 በዚያን ጊዜ በነቢዩ በኤርምያስ የተባለው። ከእስራኤል
ልጆችም አንዳንዶቹ የገመቱትን ፥ የተገመተውን ዋጋ ሠላሳ ብር
ያዙ ፥ 10 ጌታም እንዳዘዘኝ ስለ ሸክላ ሠሪ መሬት ሰጡት።
የሚል ተፈጸመ። 11 ኢየሱስም በገዢው ፊት ቆመ ፤ ገዢውም።
የአይሁድ ንጉሥ አንተ ነህን? ብሎ ጠየቀው ፤ ኢየሱስም።
አንተ አልህ አለው። 12 የካህናት አለቆችም ሽማግሎችም
ሲከሱት ምንም አልመለሰም። 13 በዚያን ጊዜ ጲላጦስ። ስንት
ያህል እንዲመሰክሩብህ አትሰማምን? አለው። 14 ገዢውም
እጅግ እስኪደነቅ ድረስ አንዲት ቃል ስንኳ አልመለሰለትም።
[9] Then was fulfilled that which was spoken by Jeremy the prophet, saying, And they took the thirty pieces of silver, the price of him that was valued, whom they of the children of Israel did value; [10] And gave them for the potter's field, as the Lord appointed me. [11] And Jesus stood before the governor: and the governor asked him, saying, Art thou the King of the Jews? And Jesus said unto him, Thou sayest. [12] And when he was accused of the chief priests and elders, he answered nothing. [13] Then said Pilate unto him, Hearest thou not how many things they witness against thee? [14] And he answered him to never a word; insomuch that the governor marvelled greatly.

ወጸቢሖ ተማከሩ ሊቃነ ካህናት
ይስቅልዎ ለኢየሱስ በቀራንዮ መካን።

በነጋም ጊዜ የካህናት አለቆች ጌታችን ኢየሱስን ቀራንዮ በሚባል ቦታ ይሰቅሉት ዘንድ ተማከሩ።

ይካ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት።

ዲያቆኑ:ሃሌ ሉያ ቁሙ ወአጽምዑ ከመ ንኩን ድልዋነ ለመንግሥተ ሰማያት ኦ እግዚእነወ አምላክነ መሐረነ ወተሣሃለነ ወረሰየነ ድልዋነ ለሰሚዓ ወንጌል ቅዱስ።

ካህኑ: ወንጌል ቅዱስ ዘዜነወ ማርቆስ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር።

ማቴዎስ ያስተማረውን ቅዱስ ወንጌል ይበል።

Priest says the Gospel of Mark is the Word of God.

Read the Holy Gospel that Mark taught.

ሕዝቡ ምሥጋና ላንተ ይገባል ይበሉ።

Let the people say thanksgiving belongs to You.

Read the Gospel of the hour

ማርቆስ ምዕራፍ ፲፭ : ፩ - ፲፭ Mark 27:1-14

## የማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፭፥፩-፭□(Mk. 15:1-5)

1 ወዲያውም ማለዳ የካህናት አለቆች ከሽማግሌዎችና ከጻፎች
ከሸንጎውም ሁሉ ጋር ከተማከሩ በኋላ ፥ ኢየሱስን አሳስረው
ወሰዱትና ለጲላጦስ አሳልፈው ሰጡት። 2 ጲላጦስም። አንተ
የአይሁድ ንጉሥ ነህን? ብሎ ጠየቀው። እርሱም። አንተ አልህ
ብሎ መለሰለት። 3የካህናት አለቆችም ብዙ ያሳጡት ነበር ፤
እርሱ ግን ምንም አልመለሰም። 4 ጲላጦስም ደግሞ። አንዳች
አትመልስምን? እነሆ ፥ በስንት ነገር ያሳጡሃል ብሎ ጠየቀው።
5 ኢየሱስም ከዚያ በኋላ ጲላጦስ እስኪደነቅ ድረስ ምንም
አልመለሰም።

[1] And straightway in the morning the chief priests held a consultation with the elders and scribes and the whole council, and bound Jesus, and carried him away, and delivered him to Pilate. [2] And Pilate asked him, Art thou the King of the Jews? And he answering said unto him, Thou sayest it. [3] And the chief priests accused him of many things: but he answered nothing. [4] And Pilate asked him again, saying, Answerest thou nothing? behold how many things they witness against thee. [5] But Jesus yet answered nothing; so that Pilate

ወጸቢሖ ተማከሩ ሊቃነ ካህናት አውጽእዎ
አፍአ ለኢየሱስ ውስተ አውደ ምኩናን።

በነጋም ጊዜ የካህናት አለቆች ጌታ ኢየሱስን ከአደባባዩ ወደ ውጭ አወጡት ይሰቅሉትም ዘንድ ተማከሩ።

ይካ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት።

ዲያቆኑ:ሃሌ ሉያ ቁሙ ወአጽምዑ ከመ ንኩን ድልዋነ ለመንግሥተ ሰማያት ኦ እግዚእነወ አምላክነ መሐረነ ወተሣሃለነ ወረሰየነ ድልዋነ ለሰሚዓ ወንጌል ቅዱስ።

ካህኑ: ወንጌል ቅዱስ ዘዜነወ ሉቃስ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር።

ሉቃስ ያስተማረውን ቅዱስ ወንጌል ይበል።

Priest says the Gospel of Luke is the Word of God.

Read the Holy Gospel that Luke taught.

ሕዝቡ ምሥጋና ላንተ ይገባል ይበሉ።

Let the people say thanksgiving belongs to You.

Read the Gospel of the hour

ሉቃስ ምዕራፍ ፳፪ : ፷፮ - ፸፩ Luke 22:66-71

## የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ ፳፪፥፷፮-፸፩□(Luke 22:66-71)

66 በነጋም ጊዜ የሕዝቡ ሽማግሌዎችና የካህናት አለቆች
ጻፎችም ተሰብስበው ወደ ሸንጎአቸው ወሰዱትና 67 ክርስቶስ
አንተ ነህን? ንገረን አሉት። እርሱ ግን እንዲህ አላቸው።
ብነግራችሁ አታምኑም ፤ 68 ብጠይቅም አትመልሱልኝም
አትፈቱኝምም። 69 ነገር ግን ከአሁን ጀምሮ የሰው ልጅ
በእግዚአብሔር ኃይል ቀኝ ይቀመጣል።

[66] And as soon as it was day, the elders of the people and
the chief priests and the scribes came together, and led
him into their council, saying, [67] Art thou the Christ?
tell us. And he said unto them, If I tell you, ye will not
believe: [68] And if I also ask you, ye will not answer me,
nor let me go. [69] Hereafter shall the Son of man sit on
the right hand of the power of God.

70 ሁላቸውም። እንግዲያስ አንተ የእግዚአብሔር
ልጅ ነህን? አሉት። እርሱም። እኔ እንደ ሆንሁ
እናንተ ትላላችሁ አላቸው። 71 እነርሱም። ራሳችን
ከአፉ ሰምተናልና ከእንግዲህ ወዲህ ምን ምስክር
ያስፈልገናል? አሉ።

[70] Then said they all, Art thou then the Son of God? And he said unto them, Ye say that I am. [71] And they said, What need we any further witness? for we ourselves have heard of his own mouth.

ወጸቢሖ ተማከሩ ሊቃነ ካህናት ሐመይዎ
ለኢየሱስ ወመጠውዎ ለጲላጦስ።

በነጋም ጊዜ የካህናት አለቆች ጌታ ኢየሱስን
አስረው ለጲላጦስ ይሰጡት ዘንድ ተማከሩ።

ይካ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል
ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት።

ዲያቆኑ:ሃሌ ሉያ ቁሙ ወአጽምዑ ከመ ንኩን ድልዋነ ለመንግሥተ ሰማያት አ እግዚእነወ አምላክነ መሐረነ ወተሣሃለነ ወረሰየነ ድልዋነ ለሰሚዓ ወንጌል ቅዱስ።

ካህኑ: ወንጌል ቅዱስ ዘሰበከ ዮሐንስ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር።

ዮሐንስ ያስተማረውን ቅዱስ ወንጌል ይበል።

Priest says the Gospel of John is the Word of God.

Read the Holy Gospel that John taught.

ሕዝቡ ምሥጋና ላንተ ይገባል ይበሉ።

Let the people say thanksgiving belongs to You.

Read the Gospel of the hour

ዮሐንስ ምዕራፍ ፲፰ : ፳፰ - ፵ John 18:28-40

# የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፰:፳፰-፵ (John 18:28-40)

28 ኢየሱስንም ከቀያፋ ወደ ገዡ ግቢ ወሰዱት ፤ ማለዳም
ነበረ ፤ እነርሱም የፋሲካ በግ ይበሉ ዘንድ እንጂ
እንዳይረክሱ ወደ ገዡ ግቢ አልገቡም። 29 ስለዚህ ጲላጦስ
ወደ ውጭ ወደ እነርሱ ወጥቶ። ይህን ሰው ስለ ምን
ትከሱታላችሁ አላቸው። 30 እነርሱም መልሰው። ይህስ ክፉ
አድራጊ ባይሆን ወደ አንተ አሳልፈን ባልሰጠነውም ነበር
አሉት።

**[28] Then led they Jesus from Caiaphas unto the hall of
judgment: and it was early; and they themselves went not
into the judgment hall, lest they should be defiled; but that
they might eat the passover. [29] Pilate then went out unto
them, and said, What accusation bring ye against this
man? [30] They answered and said unto him, If he were
not a malefactor, we would not have delivered him up
unto thee.**

31 ጲላጦስም። እናንተ ወስዳችሁ እንደ ሕጋችሁ ፍረዱበት
አላቸው። አይሁድም። ለእኛስ ማንንም ልንገድል
አልተፈቀደልንም አሉት ፤ 32 ኢየሱስ በምን ዓይነት ሞት
ሊሞት እንዳለው ሲያመለክት የተናገረው ቃል ይፈጸም ዘንድ
ነው። 33 ጲላጦስም እንደ ገና ወደ ገዡ ግቢ ገባና
ኢየሱስን ጠርቶ። የአይሁድ ንጉሥ አንተ ነህን? አለው።
34 ኢየሱስም መልሶ። አንተ ይህን የምትለው ከራስህ ነውን
ወይስ ሌሎች ስለ እኔ ነገሩህን? አለው።

**[31] Then said Pilate unto them, Take ye him, and judge him according to your law. The Jews therefore said unto him, It is not lawful for us to put any man to death: [32] That the saying of Jesus might be fulfilled, which he spake, signifying what death he should die. [33] Then Pilate entered into the judgment hall again, and called Jesus, and said unto him, Art thou the King of the Jews? [34] Jesus answered him, Sayest thou this thing of thyself, or did others tell it thee of me?**

35 ጲላጦስ መልሶ። እኔ አይሁዳዊ ነኝን? ወገኖችህና የካህናት
አለቆች ለእኔ አሳልፈው ሰጡህ ፤ ምን አድርገሃል? አለው። 36
ኢየሱስም መልሶ። መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም ፤
መንግሥቴስ ከዚህ ዓለም ብትሆን ፥ ወደ አይሁድ እንዳልሰጥ
ሎሌዎቼ ይዋጉልኝ ነበር ፤ አሁን ግን መንግሥቴ ከዚህ
አይደለችም አለው። 37 ጲላጦስም። እንግዲያ ንጉሥ ነህን?
አለው። ኢየሱስም መልሶ። እኔ ንጉሥ እንደ ሆንሁ አንተ
ትላለህ። እኔ ለእውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ ስለዚህም
ወደ ዓለም መጥቻለሁ ፤ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል
አለው።

[35] Pilate answered, Am I a Jew? Thine own nation and the chief
priests have delivered thee unto me: what hast thou done? [36]
Jesus answered, My kingdom is not of this world: if my kingdom
were of this world, then would my servants fight, that I should not
be delivered to the Jews: but now is my kingdom not from hence.
[37] Pilate therefore said unto him, Art thou a king then? Jesus
answered, Thou sayest that I am a king. To this end was I born, and
for this cause came I into the world, that I should bear witness unto
the truth. Every one that is of the truth heareth my voice.

38 ጲላጦስ። እውነት ምንድር ነው? አለው። ይህንም ብሎ
ዳግመኛ ወደ አይሁድ ወጥቶ። እኔስ አንዲት በደል ስንኳ
አላገኘሁበትም። 39 ነገር ግን በፋሲካ አንድ ልፈታላችሁ
ልማድ አላችሁ ፤ እንግዲህ የአይሁድን ንጉሥ ልፈታላችሁ
ትወዳላችሁን? አላቸው። 40 ሁሉም ደግመው። በርባንን
እንጂ ይህን አይደለም እያሉ ጮኹ። በርባን ግን ወንበዴ
ነበረ።

[38] Pilate saith unto him, What is truth? And when he had said this, he went out again unto the Jews, and saith unto them, I find in him no fault at all. [39] But ye have a custom, that I should release unto you one at the passover: will ye therefore that I release unto you the King of the Jews? [40] Then cried they all again, saying, Not this man, but Barabbas. Now Barabbas was a robber.

ወጸቢሖ ተማከሩ ሊቃነ ካህናት አውጽእዎ
አፍአ ለኢየሱስ ወነበረ አውዶ ሶቤሃ።

በነጋም ጊዜ የካህናት አለቆች ተማከረዉ ጌታ ኢየሱስን ወደ ውጭ አወጡት ያን ጊዜም በአደባባዩ ተቀመጠ።

ይካ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት።

ከወንጌል በኋላ ካህኑ፦

ጸልዩ በእንተ ጽንዐ ዛቲ የሚባለውን ጸሎት በየክፍሉ ያንብብ ሕዝቡም በየምዕራፉ እግዚኦ ተሣሃለነ (አቤቱ ይቅር በለን) እያሉ እየሰገዱ ይመልሱ።

After the Reading of the Gospel

LITANY PRAYER

The priest prays the Morning Litany prayer, after each part, the congregation responds with Lord have mercy (Egzio Tesehalene) and kneel.

ይካ. ስለዚች ቦታ መጽናት በቅዱሳን አባቶቻችን ስም ስለሚጠሩም ቦታዎችና ገዳማት በውስጣቸውም ስለሚኖሩ ሽማግሎች በጠቅላላም ስለዚህ ዓለም መጠበቅ ጸልዩ ጌታ ከክፉ ሁሉ ይጠብቃቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for this church, and all Orthodox churches, the desert monasteries, the elders dwelling therein, and for the peace of the whole world, that the Lord our God may protect us and them from all evil and malice and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በዚች ቦታና በሌሎችም ቦታዎች ስለሚገኙ በነፍስ በሥጋ ስለታመሙ አባቶቻችንና ወንድሞቻችን ጸልዩ። ጌታ ለኛም ለነርሱም ሕይወቱን ጤንነቱን ሰጥቶ በጎ ነገርን ያደርግ ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask God for our fathers and brothers who are sick with any sickness whether in this place or in any place, that the Lord our God, may grant them and us health and healing, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በባሕር በየብስ በወንዝ በቀላይ በሌላውም መንገድ ሁሉ ስለሚጓዙ አባቶቻችንና ወንድሞቻችን ጸልዩ። ጌታ በቀና መንገድ መርቶ በሰላም በደስታ ወደ መኖሪያቸዉ ይመልሳቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for our fathers and brothers who are traveling and those who intend to travel in all places. May God aid their ways. Those who are traveling by seas, rivers, lakes, roads or any other means, may the Lord our God guide them, bring them back to their dwelling place in peace, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ከእርሻ ስለሚገኝ ፍሬ ስለ ዛፎችና ስለ ወይኖች በዓለምም ውስጥ ፍሬን ስለምታፈራ ዕንጨት ሁሉ ጸልዩ። ጌታ ባርኮ አብዝቶ ከጥፋትም ጠብቆ ለፍጻሜ ፍሬ ያደርሳቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for the winds of the heaven, the fruits of the earth, all the trees and vineyards and all fruitful trees in the world, that Christ our God may bless them, preserve them, and bring them to completion in peace, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. አምላካችን ክርስቶስ በገዡችና በፈራጆች ፊት ይቅርታንና ምሕረትን እንዲሰጠን ልቡናቸውንም ሁልጊዜ በቸርነቱ እንዲያራራልን ጸልዩ። ኃጢአታችንንም ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask that God may grant us mercy and compassion before the sovereign rulers and incline their hearts with goodness towards us at all times, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በክርስቶስ አምነው ከዚህ በፊት ስለሞቱ ወንድሞቻችንና አባቶቻችን ጸልዩ። እነርሱም የተቀደሱ አባቶቻችን ሊቃነ ጳጳሳትና አባቶቻችን ጳጳሳት አባቶቻችን ኤጲስ ቆጶሳት አባቶቻችን ቆሞሳት አባቶቻችን ቀሳውስት ወንድሞቻችን ዲያቆናት አባቶቻችን መነኮሳትና አባቶቻችን ሕዝባውያን ሌሎችም ከክርስቲያን ወገን በሞት ያረፉት ሁሉ ናቸዉ። ጌታ ዕረፍተ ነፍስን ይሰጣቸው ዘንድ ጸልዩ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚአ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for our fathers and brethren who have fallen asleep and reposed in the faith of Christ since the beginning, our holy fathers the patriarchs, our fathers the metropolitans, our fathers the bishops, our fathers the hegomens, our fathers the priests, our brethren the deacons, our fathers the monks, and our brethren the laymen, and for the repose of all Christians who have fallen asleep, that the Lord our God may repose their souls, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. የክርስቲያን እምነት ላልተፈጸመላቸው ወገኖቻችን ጸልዩ። ጌታ ይባርካቸው ዘንድ እስከ መጨረሻዪቱም ሕቅታ በቀናች ሃይማኖት ያጸናቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for the catechumens, that the Lord our God may bless them, enlighten their hearts, confirm them in the Orthodox faith until the last breath, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ሐዋርያት ስላጸኗትና ስለሰበሰቧት ስለ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ሰላም ጸልዩ። ስለ ሕዝቡም ሁሉ መዳንና ስለ ቦታው ሁሉ መጠበቅ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray for the peace of the church, for the apostles and the gathering of the church. And for the salvation of all the people, and for all the places and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ንዑድ ክቡር ስለሚሆን ስለአባታችን ___________የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሊቀ ጳጳሳቱ አባታችን አቡነ_____________ና ብፁዕ አባታችን አቡነ____________ በሕይወት በሞት በኑሮም ስለሚደርስባቸዉ ሁሉ ጸልዩ። ሕይወታቸውን ጠብቆ ለብዙ ዘመን በመንበረ ስብከታቸው ያጸናቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for the life of our honored father, our patriarch Abba (...), the archbishops ______ and __________, that the Lord God may keep them and confirm them on his throne for many years and long peaceful times, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ስለ አንድነታችንና የቀናች ሃይማኖት ስላላቸው ሕዝበ ክርስቲያን አንድነት ጌታ ይጠብቃቸውና በሰላም ያስፈጸማቸው ዘንድ ጸልዩ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray that the Lord will guard them and make them live in peace by the unity of the Christian community because of our unity and of the true religion and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ለከበረች ቤተ ክርስቲያን መባን ስለሚያቀርቡ ሰዎች ጸልዩ። ጌታ ይባርክላቸው ዘንድ። በሥራቸውም እንዲጸኑ ይረዳቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray for those who offer an offering for the glorious church. That the Lord may bless them. That he might sustain them and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ምእመናንን በየስፍራቸው ሁሉ በቸርነት ስለሚያስቡና ለበጎ ነገር ስለሚደክሙ የቀና ሃይማኖት ስላላቸው ሰዎች ሁሉ ጸልዩ። ጌታ ባርኮ ዋጋቸውን እንዲሰጣቸውና ይቅርታን እንዲያደርግላቸው። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray for every believer who has the true religion and for those who care and labor for the the good of the Church. That the Lord bless them and reward them and forgiveness and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ለቍርባን የሚሆን ስንዴውን ዕጣኑን ዘቢቡን የሚነበብባቸው መጻሕፍትን ሌላውንም የቤተ መቅደስ ዕቃ ሁሉ በመስጠት ስለሚያስቡ ሰዎች ጸልዩ። ጌታ በመንግሥተ ሰማያት የበለጠ ዋጋ ይሰጣቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for those who care for the sacrifices, the oblations, the wine, the oil, the incense, the covering, the books of prayers, the altar vessels, that the Lord our God may reward them in heavenly Jerusalem, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ስማቸውን በያንዳንዳቸው እንድንጠራ ስላዘዙን ስለ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና ስለ ታላላቆች አባቶች ጸልዩ። ጌታ በረከትን ሰጥቶ በባለስልጣኖችና በሹማምት ፊት በፈራጆችም አደባባይ ፍቅርን መወደድን ያድላቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for all for our fathers, the Orthodox metropolitans and bishops in every place who asked us to remember them by name in our prayers, that the Lord God may bless and remember them with His mercy and grant them grace before powerful rulers, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በደዌ ሥጋ በደዌ ነፍስ ለደከሙና ለተቸገሩ ለባልቴቲቱም አባት እናት ለሌላቸው ለድኆቹ ልጆችና ለተጨነቁ ሰዎች ዘር ለዘሩ እርሻ ላረሱ ለሚሸጡ ለሚገዙ ለተጨነቀችም ሰውነት በማናቸውም ቦታ ሁሉ ጸልዩ። ጌታ ራርቶ ይቅር እንዲላቸው። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for the poor, the needy, the afflicted, the weak, the farmers, the traders, the fatherless and all those who are in adversities of any kind, that the Lord our God has kindness on them and us, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በግዞት በምርኮኝነት ተይዘው ለተጨነቁ አገር ለቀው ለተሰደዱ በአጋንንት አሽክላም ለተያዙ ሰዎች ጸልዩ። ጌታ ከግዞት ከምርኮኝነት ያወጣቸው ዘንድ። ይቅርታውንም ሰጥቶ እነርሱንም እኛንም ያድነን ዘንድ። ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for those who are in the distress of prisons and dungeons, and those in captivity or exile, and those who are afflicted by devils, that the Lord our God may free them from their hardships, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ለነፍሳቸው ይቅርታን እየፈለጉ ክቡር በሆነ በዚህ ስፍራ ስለተሰበሰቡ ሁሉ ጸልዩ። የአምላካችን የጌታችን ይቅርታ ፈጥኖ ይደረግላቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for all the souls assembled with us this day, in this holy place, seeking mercy for their souls, that the mercies of the Lord our God may come upon them speedily and us, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በዚህ ዓመት ስለዝናም መዝነም ስለ ባሕርና ስለ ወንዞችም መምላት ጸልዩ። እውነተኛ አምላካችን ክርስቶስ በረከቱን ሰጥቶ እስከ ልካቸው እንዲመላቸው ለምድርም ልምላሜውን ሰጥቶ ደስ እንዲያሰኛት ሥጋዊን ደማዊን ሁሉ በረድኤት እንዲያጸና ለእንስሳትም ሁሉ ድኅነትን እንዲሰጥ ጸልዩ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for the rising of the waters of the rivers this year, that Christ our Lord may bless them and raise them according to their measure, give joy to the face of the earth, sustain us, deliver man and beast, and lift away from the world death, inflation, plagues, annhilation, evacuation, and the sword of the enemies. Grant peace and tranquility in our holy church and raise the state of Christians in every place and around the whole world till the last breath, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በጸሎታችን እናስባቸው ዘንድ አስቡን (አትርሱን) ስላሉን ሰዎች ጸልዩ። እግዚአብሔር በበጎ ያስባቸው ዘንድ በየጊዜውም ይቅር ይላቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for those who requested from us to remember them in our prayers by name, that the Lord our God may remember them according to His goodness at all times, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ይህችን ሳምንት ጌታ በበጎ ይፈጸማት ዘንድ ከኛም የጠላትን መፈታተን አርቆ ሰውነታችንን እንዲያድን ይቅር እንዲለን ጸልዩ። ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray that the Lord will complete this week in peace and to save our bodies from the temptation of our enemy and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ጌታችን አምላካችን ራርቶ ይቅር እንዲለን ልመናችንንም ተቀብሎ ለዚያ ለፋሲካው እንዲያበቃን የትንሣኤውንም ብርሃን በፍጹም ደስታ እንዲያሳየን ጸልዩ። ኃጢአታችንንም ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for this Holy Week of Pascha, of our Good Savior, that He may complete it for us in peace and show us the joy of His holy resurrection in safety and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ክርስቶስ አምላክነ ዘመጽአ ወሐመ በእንቲአነ በሕማማቲሁ ቤዘወነ።

ክርስቶስ አምላካችን ሰዉ ሁኖ መጥቶ ስለእኛ መከራ ተቀበለ በመከራውም አዳነን።

Christ our Lord who came down from heaven, has suffered for us and saved us through His affliction.

ንሰብሖ ወናልዕል ስሞ ኅቡረ እስመ ውእቱ ገብረ መድኃኒተ በዕበየ ሣህሉ።

እርሱ በይቅርታው ገናናነት ድኅነትን አድርጎአልና በአንድነት ፈጽመን ስሙን እናመስግን።

According to His steadfast love, together we praise and exalt His name because he saves us.

ትእዛዝ ሕዝቡ በሁለት ክፍል ሁነው የሚከተለዉን ጸሎት ሁለት ጊዜ በመከታተል አንድ ጊዜ በማስተዛዘል ይበሉት።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን እብኖዲ ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ታዖስ ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ማስያስ ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ኢየሱስ ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ክርስቶስ ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን አማኑኤል ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ትስቡጣ ናይናን ኪርያላይሶን።

ትእዛዝ ከዚህ በኋላ ኪርያላይሶን (41) አርባ አንድ ጊዜ ይባል። ይኸውም በአንድ ወገን ሃያ አንድ በሌላው ወገን ሃያ ጊዜ።

# መልክአ ሕማማት ዘነግህ ሰዓት

## ጸሎት ሰብዓቱ ጊዜያት ዘደረሰ አባ ጊዮርጊስ መምህር ዘጋሥጫ።

### የሰባቱ ጊዜያት የአባ ጊዮርጊስ ጸሎት በጠዋት የሚጸለይ የእመቤታችን ሰላምታ

ሰላም ለኪ ዳግሚት ሰማይ ሰላም ለኪ ፤ ማርያም ሙፃአ ፀሐይ ሰላም ለኪ፡፡

አንቀፀ መድኃኒት ሰላም ለኪ ሙዳየ ዕፍረት ሰላም ለኪ ገነተ ትፍሥሕት ሰላም ለኪ

እመ እግዚአብሔር ጸባኦት ሰላም ለኪ።

ዘምስለ ሰጊድ ንኤምኅኪ ለባርኮትነ ስፍሒ እዴኪ ጸሎተነ ወስእለተነ ማርያም ባርኪ።

ወኪያነኒ እሞተ ሙስና መሐኪ ፀዳለ ወልድኪ ዲቤነ ይዋኪ ጸልዩ ውስተ ማኅበርነ ኢይባእ ሀዋኪ።

ሰላም ለኪ ቤተ ክርስቲያን እምየ ዘትጼንዊ መጽርየ ብኪ ጸናዕኩ እምከርሠ እምየ ቤተ ክርስትያን አክሊለ ርእስየ ሰላም ለኪ።

ቤተ ክርስትያን ብሂል ነፍሰ ክርስቲያን ብሂል እንተ ቀደስኪ ደመ ወልድ ጥሉል ቤተ ክርስትያን ማኅደረ ልዑል ሰላም ለኪ።

መሠረትኪ ሳውል ወጠፈርኪ ኬፋ ወአናቅጽኪ ነቢያተ አልፋ ቤተ ክርስትያን ጸጋዊተ ተስፋ ሰላም ለኪ።

አሕዛብ ወሕዝብ ይሰግዱ ለኪ ወይትመሐለሉ በቅድመ ገጽኪ ቤተ ክርስትያን ማኅደረ መላኪ ሰላም ለኪ።

በሐኪ በሐኪ ቤተ ክርስትያን እምነ ግበሪ ሰላመ ማእከሌነ እምኀይለ ጸላኢ ወፀር ዕቀቢ ኪያነ ትንባሌኪ የሀሉ ምስሌነ ሰላም ለኪ።

ማርያም ድንግል ዘመዐዛ አፉኪ ኮል እንተ ትጼንዊ በገዳም ወሐቅል ወልታ ረዲኦትየ በውስተ ቀትል ሰላም ለኪ።

ተሰፍዎ ባዕድ አልብየ ዘእንበለኪ ምክሕየ በኢመንኖ በልኒ ገብርየ ገብርየ ተሣየጥኩከ በንዋይየ ሰላም ለኪ።

አትሮንስ ሰሎሞን አንቲ ለሐና ባሕርያ ንግሥታት ስሳ ወዕቁባት ሰማንያ ወደሳኪ እንዘ ይገንያ ሰላም ለኪ።

አመ ይከውን ድኅረ ዕለተ በቀል ወፍዳ ወአመ ኢትድኅን እም ዘወለደት ወልዳ ባልሕኒ እሞተ ዕዳ ሰላም ለኪ።

በከመ ልማድኪ በሊ ኅበ ወልድኪ ከሃሊ አ ርኅሩኅ ኢተበቃሊ ያጠፍአኑ ለሥዕሉ ሠዓሊ ኪነተከ ዘትካት ኅሊ።

ስብሐት ለከ ከመ ንንግር ኵሎ ስብሐቲከ በአናቅጺሃ ለጽዮን ማኅደረ ብዙኅ ሰላም ዘአንቃህከነ እምነ ንዋም ኢየሱስ ወልደ ማርያም ስብሐት ለከ።

ላዕለ ጻድቃን ወኃጥአን ብርሃነ ጸጋ ምውቅ ዘታሠርቅ ለነ እምነ ምሥራቅ ኢየሱስ ፀሐየ ጽድቅ ስብሐት ለከ።

ለዘመጠነዝ ገበርከ ላዕሌሆሙ ፍድፍድና ጸጋ ወሀብት ፈደዮከ እፎ እኪተ ህየንተ ሠናይት ኢየሱስ ንጉሠ ስብሐት ስብሐት ለከ።

ኢየሱስ ኅሙይ በእንቲአነ ኢየሱስ ሙቁሕ እንተ አቀሙከ ውስተ ዐውደ ፍትሕ ጊዜ ኮነ ኅሐ ጽባሕ ስብሐት ለከ።

ከመ በግዕ የዋህ ወከመ ላሕም መግዝእ መሥዋዕተ መድኃኒት ትኩን ለቤዝወ ሰብእ ዘኅለፍከ ዐጸደ ግፍዕ ስብሐት ለከ።

እምልብነ አግሕሥ እግዚኦ ነገረ ጸላኢ መስሕት ዘአግሐሥከ ለነ ጽልመተ ሌሊት ኢየሱስ ብርሃነ ሕይወት ስብሐት ለከ።

አኰቴት ስብሐት ወትረ ለመንግሥትከ ስቡሕ ጊዜ እምንዋምነ ንነቅህ። ናቄርብ ለከ በቃለ ክላሕ ወንፌኑ ስብሐተ ዘነግህ ስብሐት ለከ።

ግናይ ለክሙ ሥሉስ ቅዱስ መዋዕያነ ክልኤ አእምሮ ለብርሃን ዐቢይ ዘፈጠሮ ቃልክሙ በተናግሮ ግናይ ለክሙ፡፡

እምነ ብርሃን ብርሃነ መጠነ አሐቲ ሥርናይ እለ አልበስክሙ ነገሥተ ሰማይ ለወርኀ ወለፀሐይ ግናይ ለክሙ፡፡

ሰዓተ ሌሊት ሥላሴ ዘወሰንክሙ በኀሕ ወዘአክበርክሙ በጸዳል ብሩህ ፀሐየ እምነ ወርኀ ግናይ ለክሙ፡፡

ኀበ ርኀራሄክሙ በዝኀ ወኀበ አልቦቱ መስፈርት እለ ትሰመዩ በስመ ብእሲት ሥላሴ ዕድወ ምሕረት ግናይ ለክሙ፡፡

ከመ ኀብረ ለይ ሥጋየ አመ በኃጢአት ቈሐ ሐዘን ብየ አምጣነ በዝኀ ሥላሴ ዘዮም ወዘአሜሃ በጽባሕ ሀቡኒ ፍሥሐ።

ስብሐት ለእግዚአብሔር ኪያነ ዘፈጠረ ከመ ናምልኮ

ስብሐት ለማርያም እመ አምላክ እግዝእትነ ወመድኃኒትነ

ስብሐት ለመስቀለ ክርስቶስ ዕፀ መድኃኒት ኃይልነ ወፀወንነ።

ጸሎተ ቡራኬ

## የቡራኬ ጸሎት Prayer of Blessing by Priest

ከዚህ በኋላ ሕዝቡ ይቀመጡ። ካህኑ ግን ቆሞ ፊቱን ወደ ሕዝቡ መልሶ የቡራኬውን ጸሎት ይበል።

Let the people seat and the priest will stand and turn his face to the people, and say the prayer of the blessing.

የኢየሱስ ክርስቶስ ማኅበር ቤተ ሰብእ የምትሆኑ ወንድሞቼ ሆይ በዚች በጌታ ማደርያ መሰብሰባችሁ አይሁድ ፋሲካቸውን በአደረጉበት ቀን በመቅናታቸው ለኅጢያተኞች አሳልፈው በሰጡ ጊዜ ጌታችን የተቀበለውን መከራ ሞቱን ኅኑን መወጋቱን ደሙን ማፍሰሱን መስቀሉን እያሰባችሁ ነው።

ስለዚህ እግዚአብሔር ድካማችሁንና ጸሎታችሁን ስግደታችሁንና መዝሙራችሁን ይቀበልላችሁ ከኀሊና ሥጋ የተነሣ በኀሊና መንፈስ የምትሹትን ሁሉ በፈቃዱ ይፈጽምላችሁ።

ተስፋ ትንሣኤውን ይስጣችሁ የደስታውን ቃል ያሰማችሁ በይቅርታው ቸርነት ከመከራው ይሠውራችሁ።

ደቀ መዛሙርቱን እንደጐበኛቸው እንዲሁ እናንተንም ይጎብኛችሁ።

በኀጢአት እንዳትወድቁ ይደግፉችሁ ከሐዘናችሁ ያረጋጋችሁ ከድካማችሁ ያጽናችሁ።

እናንተንም ለማገልገል የተዘጋጀሁ ከምሆን ከእኔ ከወንድማችሁ ጋር።

በሩቅና በቅርብ ካሉ በጸሎታችሁም ከተማጸኑ ወንድሞቻችን ሁሉ ጋራ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ በደስታ ቀን ከናንተ ጋር አንድ ይሆኑ ዘንድ።

በአባታችሁ ጉባኤ በቀኙ ያቁማችሁ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ተድላ ደስታ ወደሚገኝበት ቤቱ ወደ መንግሥተ ሰማያት ያግባችሁ ለዘላለሙ።

ሕዝቡ ስለ ክርስቶስ ሥጋና ደም አሜን ይደረግልን ይሁን ይሁን ይበሉ።



# ግብረ ሕማማት ዓርብ ቀን
# Gibire Himamati Friday

**በሦስት ሰዓት**
**9 AM**

ትእዛዝ ዓርብ በሦስት ሰዓት ካህናት በከበረች በቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው የዳዊትን መዝሙር ብፁዓን እለ ተኃድገ ሎሙ (መዝሙር 31: 1) ከሚለው ጀምሮ እስከ ከመ ተሀበኒ ተምኔትየ ኵሎ አሚረ (መዝሙር 60: 8) የሚለው ድረስ ይፀልዩ።

ውዳሴ ማርያምን የማክሰኞን ይድገሙ። መሪ በሦስት ሃሌታ ስምዕዎኬ ለእግዚእነ ይበል።

ti'izazi (Order) On Friday 3rd hour, let the priests gather in Church to pray the Song of David (Psalms 31: 1) to Psalms 60:8

Let them pray the Tuesday Praise of Mary and chant the below hymn.

ትእዛዝ ዓርብ በሦስት ሰዓት ካህናቱ ይፀልዩ መሪዉ በዘጠኝ ሃሌታ ይበል።

በዕዝል ዜማ

በመሪ ወገን አንድ ጊዜ በመከተል በተመሪ ወገን አንድ ጊዜ ለሦስተኛ ጊዜ ደግሞ በጋራ ይባላል።

ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ

አርዑተ መስቀሉ ጾረ አርዑተ መስቀሉ ጾረ ይስቅልዎ ሖረ ዬ ዬ ዬ ከመ ኪያነ ይቤዙ እግዚእ ኮነ ገብረ።

ቅድመ ዓለም የነበረ ዛሬም ያለ ወደፊትም ዓለምን አሳልፎ የሚኖር መስቀሉን ተሸክሞ ይሰቅሉት ዘንድ ጌታ ባርያ ሆነ።

ሁሉም በአንድነት እየሰገዱ 6 በግራ 6 በቀኝ በአንድ ዓይነት ዜማ አሥራ ሁለት ጊዜ ለከ ኃይል ይበሉ።

This is chanted 12 times (6 times alternating on the right and left aisles of the Church) with prostrations and after each they recite "Our Father..."

ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወዕዘዝ ለዓለም ዓለም።

ኃይል ክብር ጌትነት ገዥነት ለዘላለሙ ለአንተ ይገባል።

For Thine is the power, the glory, the blessing, and the majesty, forever and ever.

ዐማኑኤል አምላኪየ ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወዕዘዝ ለዓለም ዓለም።

ፈጣሪዬ ዐማኑኤል ሆይ ኃይል ክብር ጌትነት ገዥነት ለዘላለሙ ለአንተ ይገባል።

Emmanuel my God, For Thine is the power, the glory, the blessing, and the majesty, forever and ever.

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወዕዘዝ ለዓለም ዓለም።

ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ኃይል ክብር ጌትነት ገዥነት ለዘላለሙ ለአንተ ይገባል።

O My Lord Jesus Christ, for Thine is the power, the glory, the blessing, and the majesty, forever and ever.

ኃይልየ ወፀወንየ ዉእቱ እግዚእየ እስመ ኮንከኒ ረዳእየ እብል ወአኮቴት

አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ

ኃይሌና አምባ መጠጊያዬ ጌታዬ ነህ ረዳት ሁነኸኛልና በምሥጋና እንዲህ እላለሁ

በሰማያት ያለህ አባታችን ሆይ ስምህ ይመስገን

The Lord is my power, strength and shelter; for you became my Holy Salvation, I say with thanks-giving

Lord's prayer: Our Father

## አቡነ ዘበሰማያት / Abune Zebesemayat / አባታችን ሆይ / Our Father

አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ ትምጻእ መንግሥትከ ወይኩን ፈቃደከ በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር ሲሳየነ ዘለለ ዕለትነ ሀበነ ዮም ንኅድግ ለዘአበሰ ለነ ወጌጋየነ ከመ ንሕነኒ ንኅድግ ለዘአበሰ ለነ ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት አላ አድኅነነ ወባልሐነ እምኵሉ እኩይ እስመ ዚአከ ይእቲ መንግሥት ኃይል ወስብሐት ለዓለመ ዓለም አሜን ።

**Abune Zebesemayat Yitkedes Simike Timsa Mengistike Weyikun Fekadeke Bekeme Besemay Kemahu Bemedir Sisayene Zelele Ilitene Habeneyom Hidig Lene Abesane Wegegayene Keme Nihinenee Nihidig Leze Abese Lene Etabiane Igzeeo Wiste Mensut Ala Addihanene Webalihane Imkwulu Ikuy Isme Zeake Yeite Mengist Hayl We Sebhat Lealem alem Amen.**

**Our Father who art in Heaven, Hallowed be thy name. Thy Kingdom come. Thy will be done On Earth as it is in Heaven. Give us this day our daily bread And forgive us our trespasses As we forgive those who trespass against us And lead us not into temptation But deliver us from evil one in Christ Jesus Our Lord. For thine is the Kingdom The Power and the Glory Forever and ever. Amen.**

ለአምላክ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለአምላክነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to God forever and ever.

ለሥሉስ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለሦስትነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to the Holy Trinity forever and ever.

ለማሕየዊ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለአዳኝነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to the Life giver forever and ever.

ለእዘዙ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለጌትነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to His Glory forever and ever.

ለመንግሥቱ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።
ለመንግሥቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።
Honour and Glory be to His Kingdom forever and ever.

ለዕበዩ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።
ለገናናነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።
Honour and Glory be to His Majesty forever and ever.

ለሥልጣኑ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።
ለሥልጣኑ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።
Honour and Glory be to His Power forever and ever.

ለምኵናኑ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።
ለፈራጅነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።
Honour and Glory be to His Authority forever and ever.

ለኢየሱስ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለኢየሱስ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to Jesus forever and ever.

ለክርስቶስ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለክርስቶስ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to Christ forever and ever

ለሕማሙ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለመከራው ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to His Suffering forever and ever

ለመስቀሉ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለመስቀሉ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to the Cross forever and ever

ለከ ይደሉ ኃይል ለከ ይደሉ ስብሐት ወለከ ይደሉ አኰቴት ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለመ ዓለም።

ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ለአንተ ከሀሊነት ይገባሃል ለአንተ ክብር ይገባሃል ለአንተ ከምስጋና ይገባሃል ለዘላለሙ።

Power, Glory and blessing be to my Lord Jesus Christ forever and ever.

የዓርብ ጠዋት ፫ ሰዓት ምንባባት

Friday 9 AM Readings

## የተአምረ ማርያም መቅድም
## Introductory Chant to the Miracle of Mary

**ምንተኑ አዐስየኪ ዕሴተ። በእንተ ኵሉ ዘገበርኪ ሊተ። ማርያም ሠናይት ዘታፈቅሪ ምሕረተ። ሶበሰ ትትዓቀቢ ዘዚአየ ኀጢአተ። እምኢሐዮውኩ አሐተ ሰዓተ።**

**ምሕረትን የምትወጂ መልካሚቱ ማርያም ስለአደረግሽልኝ ሁሉ ምን ዋጋ እከፍልሻለሁ? የእኔንም ኀጢአት የምትቈጣጠሪ ቢሆን አንዲት ሰዓት እንኳን ባልኖርሁ ነበር።**

በሰላመ ገብርኤል መልአክ ኦ እግዚእትየ ማርያም ሰላም ለኪ። ድንግል በኅሊናኪ ወድንግል በሥጋኪ። እመ እግዚአብሔር ጸባኦት ሰላም ለኪ። ቡርክት አንቲ እምአንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ። ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልእተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ በመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እልሻለው። በሐሳብሽ ድንግል ነሽ በሥጋሽም ድንግል ነሽ። የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናት ሆይ ሰላምታ ላንቺ ይገባል፡፡ ከሴቶች ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ። የማህፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው፡፡ ጸጋን የተሞላሽ ሆይ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና ደስ ይበልሽ።

ተአምረ ማርያም ይነበባል።

Reading of the Miracles of Saint Mary

# ከተአምረ ማርያም በኋላ

## After reading the Miracles of Saint Mary chant the following

**ወላዲተ አምላክ ማርያም እንበለ ሰብሳብ ወሩካቤ። በይነ ዘአቀረብኩ ለኪ ንስቲተ ቃለ ይባቤ። ፈትቲ እሙ በረከተ አፉኪ መዓዛ ከርቤ። እስመ ለነዳይ ብእሲ ወለዘረከቦ ምንዳቤ። ኅብስተከ ፈትት ኢሳይያስ ይቤ።**

ያለ ርኩሰትና ያለ ሩካቤ አምላክን የወለድሽ ማርያም ሆይ ስለአቀረብኩልሽ ትንሽ የምስጋና ቃል እናቱ የከርቤ መዐዛ ያለዉን የአፍሽን በረከት ስጭ። ኢሳይያስ ለድኃ ሰዉና ችግር ላገኘዉ እንጀራህን ስጥ ብሏልና።

ስብሐት ለኪ ማርያም በኍልቈ መላእክት ዘአርያም።
ስብሐት ለኪ ማርያም በኍልቈ ጻድቃን ዘገዳም።
ስብሐት ለኪ ማርያም በኍልቈ ርደቱ ለዝናም።
ስብሐት ወክብር ወሰጊድ ለተአምርኪ ዮም።
ወበተአምረ ወልድኪ ተፈሥሓ ኵሉ ዓለም።

እመቤታችን ማርያም ሆይ በሰማይ መላእክት ቍጥር ምስጋና ላንቺ ይገባል።
እመቤታችን ማርያም ሆይ በገዳም በሚኖሩ ጻድቃን ቍጥር ምስጋና ላንቺ ይገባል።
እመቤታችን ማርያም ሆይ በዝናሙ መዉረድ ቍጥር ምስጋና ላንቺ ይገባል።
ክብር ስግደትና ምስጋናም ዛሬ ለተአምርሽ ይገባል።
በልጅሽ ተአምር ዓለሙ ሁሉ ደስ ተሰኝቷልና።

# መቅድመ ተአምረ ኢየሱስ

## ተአምረ ኢየሱስ ከመነበቡ በፊት

## Chant before the reading of Miracles of Jesus

ኢየሱስ ክርስቶስ ጥዑመ ስም ለዘይጼዉዖ። ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብስተ ሕይወት ለዘይበልዖ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ጽዋዓ መድኃኒት ለዘይጸዉዖ። ከመ ይባርኩነ ይፈኑ አርዳኦ ለጸባዒነ ይጽብዖ ወልታሁ ነሢኦ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚጠራዉ ስሙ ጣፋጭ ነዉ። ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚበላዉ የሕይወት እንጀራ ነዉ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚሰዋዉ የድኅነት በግ ነዉ። ይባርኩን ዘንድ ደቀ መዛሙርቱን ይላክ። ጋሻ ጦሩን አንሥቶ የሚጣላንን ይጣላዉ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ዘአጽልእቲሁ ምስሌሁ። ወመስቀለ ሞቱ ቅድሜሁ።

አዘቅተ ወይን ገቦሁ ቍርባነ አምልኮ ሥጋሁ። ያብአነ ቤተ መርዓሁ ውስተ ደብተራሁ አመ ይትጋብኡ ለምሳሕ ሥርግዋን ሐራሁ።

ቍስሉ ከእርሱ ጋራ መከራ መስቀሉ በፊቱ የሚታሰብ ኢየሱስ ክርስቶስ ጎኑ

የወይን አዘቅት ሥጋው የአምልኮ መሥዋዕት የሆነ በቅድስና ልብስና ጌጥ የተሸለሙ ባለሟሎቹ ለምሳ በሚሰበሰቡ ጊዜ ወደ ሙሽርነቱ ድንኳን ያስገባን።

ለጥብሓ ሥጋከ ንሴሰዮ ወለነቅዐ ደምከ ንረውዮ ኢየሱስ ክርስቶስ በግዕ ዘቀራንዮ፤

ለላህይከ ገጽከ ንትሜነይ ከመ ንርአዮ። ውስተ ስያሓ ሱራፊ ለስእለትየ ደዮ። ወበሕማመ ሞትከ አምላካዊ ለቍስልነ አጥዕዮ።

የተሠዋውን ሥጋህን ተመግበን ከደምህ ምንጭ እንረካለን የቀራንዮ በግ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ

ውበትህን እናየዉ ዘንድ እንመኛለን። በሱራፌ ጽዋ ውስጥ ልመናችንን ጨምረዉ። አምላክ ሆይ ለሞት በሚያበቃ ሕማምህ ቊስላችንን አድነዉ።

ለጥብሐ ሥጋከ እጸግቦ ወለነቅዓ ደምከ እሰርቦ ኢየሱስ ክርስቶስ በግዕ ርጉዘ ገቦ።

አይሁዳዊ ከሃዲ አሚነ ሥላሴ ዘአልቦ። ኢተወልደ እማርያም ዘይቤለከ እመቦ፤ አህጉራተ (ጽጐጓተ) ዓለም ለይዑድ ከመ ከልብ ርኊቦ።

ተአምረ ኢየሱስ አንብብ

Read the Miracles of Jesus

# ከተአምረ ኢየሱስ በኋላ
## Chant after the Miracles of Jesus is read

አመ ትመጽእ ለኰንኖ መስለ ደመ ገቦ ወአእጋር። አማኅፀንኩ ነፍስየ ውስተ እዴከ ክቡር። ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአ ሰማያት ወምድር። ይትዋቀሱ በእንቲአየ ተኰርያትከ በበትር። ወተሠይጦትከ ከመ ገብር ለኅዳጥ ብሩር።

ከጎንህና ከእግሮችህ ደም ጋራ ለፍርድ በምትመጣ ጊዜ። በከበረዉ እጅህ ውስጥ ነፍሴን አደራ አስጠበቅሁ። የሰማይና የምድር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራስህን በበትር መመታትህና እንደ ባሪያ በጥቂት ብር መሸጥህ ስለ እኔ ይከራከሩልኝ።

ስብሐት ለከ ኢየሱስ በአፈ ኵሉ ውዱስ።
ስብሐት ለከ ኢየሱስ ቀዳሴ ሥጋ ወነፍስ።
ስብሐት ለከ ኢየሱስ ለዕሩቃን ልብስ።
ስብሐት ለከ ኢየሱስ ዘኢትሠአር ንጉሥ።
ስብሐት ለከ ኢየሱስ ቃለ አብ ቅዱስ።

በሁሉም አፍ የተመሰገንከ ኢየሱስ ሆይ ምስጋና ላንተ ይገባል።
ሥጋንና ነፍስን ያከበርከ ኢየሱስ ሆይ ምስጋና ላንተ ይገባል።
ለታረዙት ልብስ የሆንከ ኢየሱስ ሆይ ምስጋና ላንተ ይገባል።
የማትሻር ንጉሥ ኢየሱስ ሆይ ምስጋና ላንተ ይገባል።
ቅዱስ የአብ አካላዊ ቃል ኢየሱስ ሆይ ምስጋና ላንተ ይገባል።

## ዲያቆን ከወንጌል በፊት

## Deacon Chants Psalms before the Gospel is read

በሦስቱ ሰዓት መዓልት ዘዓርብ: ትእዛዝ

ከምስባክ አስቀድሞ ይህ ከዚህ በታች ያለው መዝሙር ይባላል። ካህኑ ከመቅደስ ገብቶ እያጠነ ፫ ጊዜ እንደዚህ ይበል።

ግፍዖሙ እግዚኦ ለእለ ይገፍዑኒ

ጽብአሙ እግዚኦ ለእለ ይጸብኡኒ

ግፍዖሙ እግዚኦ ለእለ ይገፍዑኒ።

አቤቱ ሳልበድላቸው የሚበድሉኝን አጥፋቸው

ሳልጣላቸው የሚጣሉኝን አቤቱ ተጣላቸው

ሳልገፋቸው የሚገፉኝን አቤቱ ግፋቸው።

ሕዝቡም ካህኑን እየተከተሉ እንደዚሁ ይበሉ። So let the people say the same way.

ከዚህም ቀጥሎ ፩ ዲያቆን መዝሙር ሠላሳ አራትን በወርድ ንባብ ያንብብ

# ዲያቆን ከወንጌል በፊት

# Deacon Chants Psalms before the Gospel is read

ዐገቱኒ ከለባት ብዙኃን።
ወአኀዙኒ ማኅበሮሙ ለእኩያን
ዐገቱኒ ከለባት ብዙኃን

ብዙ ውሾች ከብበውኛልና ፤ የክፉተኞች ጉባኤም ያዘኝ ፤ መዝ. ዳ 22:16

For dogs have compassed me: the assembly of the wicked have inclosed me: Psalm 22:16

ሕዝቡም እንዲሁ ይበሉ።

So let the people say the same way.

ዲያቆኑ:ሃሌ ሉያ ቁሙ ወአጽምዑ ከመ ንኩን ድልዋነ ለመንግሥተ ሰማያት ኦ እግዚእነወ አምላክነ መሐረነ ወተሣሃለነ ወረሰየነ ድልዋነ ለሰሚዓ ወንጌል ቅዱስ።

ካህኑ: ወንጌል ቅዱስ ዘዜነወ ማቴዎስ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር።

ማቴዎስ ያስተማረውን ቅዱስ ወንጌል ይበል።

Priest says the Gospel of Mathew is the Word of God.

Read the Holy Gospel that Mathew taught.

ሕዝቡ ምሥጋና ላንተ ይገባል ይበሉ።

Let the people say thanksgiving belongs to You.

Read the Gospel of the hour

ማቴዎስ ምዕራፍ ፳፯:፲፭-፳፮ Mathew 27:15-26

ይ.ካ ወንጌል ቅዱስ ዘዜነዉ ማቴዎስ ወማርቆስ ሉቃስ ወዮሐንስ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር።

## ወንጌል፥ ማቴዎስ ምዕ ፳፯ ቁ. ፲፭-፳፯

15 በዚያም በዓል ሕዝቡ የወደዱትን አንድ እስረኛ ሊፈታላቸው ለገዢው ልማድ ነበረው። 16 በዚያን ጊዜም በርባን የሚባል በጣም የታወቀ እስረኛ ነበራቸው። 17 እንግዲህ እነርሱ ተሰብስበው ሳሉ ጲላጦስ። በርባንን ወይስ ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን ማንኛውን ልፈታላችሁ ትወዳላችሁ? አላቸው ፤

**[15] Now at that feast the governor was wont to release unto the people a prisoner, whom they would. [16] And they had then a notable prisoner, called Barabbas. [17] Therefore when they were gathered together, Pilate said unto them, Whom will ye that I release unto you? Barabbas, or Jesus which is called Christ?**

18 በቅንዓት አሳልፈው እንደ ሰጡት ያውቅ ነበርና። 19
እርሱም በፍርድ ወንበር ተቀምጦ ሳለ ሚስቱ። ስለ እርሱ
ዛሬ በሕልም እጅግ መከራ ተቀብያለሁና በዚያ ጻድቅ ሰው
ምንም አታድርግ ብላ ላከችበት። 20 የካህናት አለቆችና
ሽማግሎች ግን በርባንን እንዲለምኑ ኢየሱስን ግን
እንዲያጠፉ ሕዝቡን አባበሉ።

**[18] For he knew that for envy they had delivered him. [19] When he was set down on the judgment seat, his wife sent unto him, saying, Have thou nothing to do with that just man: for I have suffered many things this day in a dream because of him. [20] But the chief priests and elders persuaded the multitude that they should ask Barabbas, and destroy Jesus.**

21 ገዢውም መልሶ። ከሁለቱ ማንኛውን ልፈታላችሁ
ትወዳላችሁ? አላቸው ፤ እነርሱም። በርባንን አሉ። 22
ጲላጦስ። ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን እንግዲህ ምን
ላድርገው? አላቸው ፤ ሁሉም። ይሰቀል አሉ። 23
ገዢውም። ምን ነው? ያደረገው ክፋት ምንድር ነው? አለ ፤
እነርሱ ግን። ይሰቀል እያሉ ጩኸት አበዙ።

**[21] The governor answered and said unto them, Whether of the twain will ye that I release unto you? They said, Barabbas. [22] Pilate saith unto them, What shall I do then with Jesus which is called Christ? They all say unto him, Let him be crucified. [23] And the governor said, Why, what evil hath he done? But they cried out the more, saying, Let him be crucified.**

24 ጲላጦስም ሁከት እንዲጀመር እንጂ አንዳች እንዳይረባ
ባየ ጊዜ ፥ ውኃ አንሥቶ። እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም
ንጹሕ ነኝ ፤ እናንተ ተጠንቀቁ ሲል በሕዝቡ ፊት እጁን
ታጠበ። 25 ሕዝቡም ሁሉ መልሰው። ደሙ በእኛና
በልጆቻችን ላይ ይሁን አሉ። 26 በዚያን ጊዜ በርባንን
ፈታላቸው ፥ ኢየሱስን ግን ገርፎ ሊሰቀል አሳልፎ ሰጠ።

**[24] When Pilate saw that he could prevail nothing, but that rather a tumult was made, he took water, and washed his hands before the multitude, saying, I am innocent of the blood of this just person: see ye to it. [25] Then answered all the people, and said, His blood be on us, and on our children. [26] Then released he Barabbas unto them: and when he had scourged Jesus, he delivered him to be crucified.**

## ከወንጌል በኋላ ካህኑ፦

## After the Reading of the Gospel

**ጊዜ ሠለስቱ ሰዓት አሐዝዎ ለኢየሱስ ወወሰድዎ ይስቅልዎ**

**At 9:00 a.m they seize Jesus and took Him to be crucified.**

ሦስት ሰዓት በሆነ ጊዜ ኢየሱስን ይዘው ይሰቅሉት ዘንድ ወሰዱት።

ይካ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተወልደ እምርያም እምቅድስት ድንግል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ልዩ ሕያው የማይሞት ከንጽሕት ድንግል ማርያም የተወለደ አቤቱ ይቅር በለን።

ልዩ ገዥ ልዩ ኃያል ልዩ ሕያው የማትሞት በዮርዳኖስ ውኃ የተጠመቅህ በዕንጨት መስቀልም የተሰቀልህ አቤቱ ይቅር በለን።

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has born from the holy Virgin Mary; have mercy upon us, Lord.

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has babelized in Jordan and crucified on the tree of the cross; have mercy upon us, Lord.

ዲያቆኑ:ሃሌ ሉያ ቁሙ ወአጽምዑ ከመ ንኩን ድልዋነ ለመንግሥተ ሰማያት ኦ እግዚእነወ አምላክነ መሐረነ ወተሣሃለነ ወረሰየነ ድልዋነ ለሰሚዓ ወንጌል ቅዱስ።

ካህኑ: ወንጌል ቅዱስ ዘዜነወ ማርቆስ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር።

ማርቆስ ያስተማረውን ቅዱስ ወንጌል ይበል።

Priest says the Gospel of Mark is the Word of God.

Read the Holy Gospel that Mark taught.

ሕዝቡ ምሥጋና ላንተ ይገባል ይበሉ።

Let the people say thanksgiving belongs to You.

Read the Gospel of the hour

ማርቆስ ምዕራፍ ፲፭:፮-፲፭ Mark 15:6-15

## ወንጌል፥ ማርቆስ ምዕ. ፲፭፥ቁ. ፮-፲፭

6 በዚያም በዓል የለመኑትን አንድ እስረኛ ይፈታላቸው ነበር።
7 በዓመፅም ነፍስ ከገደሉት ከዓመፀኞች ጋር የታሰረ በርባን
የተባለ ነበረ። 8 ሕዝቡም ወጥተእንደ ልማዱ ያደርግላቸው
ዘንድ እየጮኹ ይለምኑት ጀመር። 9 ጲላጦስም። የአይሁድን
ንጉሥ እፈታላችሁ ዘንድ ትወዳላችሁን? ብሎ መለሰላቸው ፤ 10
የካህናት አለቆች በቅንዓት አሳልፈው እንደ ሰጡት ያውቅ
ነበርና።

[6] Now at that feast he released unto them one prisoner, whomsoever they desired. [7] And there was one named Barabbas, which lay bound with them that had made insurrection with him, who had committed murder in the insurrection. [8] And the multitude crying aloud began to desire him to do as he had ever done unto them. [9] But Pilate answered them, saying, Will ye that I release unto you the King of the Jews? [10] For he knew that the chief priests had delivered him for envy.

11 የካህናት አለቆች ግን በርባንን በእርሱ ፈንታ ይፈታላቸው ዘንድ
ሕዝቡን አወኩአቸው። 12 ጲላጦስም ዳግመኛ መልሶ። እንግዲህ
የአይሁድ ንጉሥ የምትሉትን ምን ላደርገው ትወዳላችሁ? አላቸው።
13 እነርሱም ዳግመኛ። ስቀለው እያሉ ጮኹ። 14 ጲላጦስም።
ምን ነው? ያደረገው ክፋት ምንድር ነው? አላቸው። እነርሱ ግን።
ስቀለው እያሉ ጩኸት አበዙ። 15 ጲላጦስም የሕዝቡን ፈቃድ
ሊያደርግ ወዶ በርባንን ፈታላቸው ፥ ኢየሱስንም ገርፎ እንዲሰቀል
አሳልፎ ሰጠ።

[11] But the chief priests moved the people, that he should rather release Barabbas unto them. [12] And Pilate nswered and said again unto them, What will ye then that I shall do unto him whom ye call the King of the Jews? [13] And they cried out again, Crucify him. [14] Then Pilate said unto them, Why, what evil hath he done? And they cried out the more exceedingly, Crucify him. [15] And so Pilate, willing to content the people, released Barabbas unto them, and delivered Jesus, when he had scourged him, to be crucified.

# ከወንጌል በኋላ ካህኑ፦

## After the Reading of the Gospel

ጊዜ ሠለስቱ ሰዓት አሕየወ ሎሙ በርባንሃ ወወሀቦሙ ኢየሱስሃ ይስቅሉ።

**At 9:00 a.m they released Barabas and sentenced Jesus to death.**

ሦስት ሰዓት በሆነ ጊዜ በርባንን አድኖ ኢየሱስን ይሰቅሉት ዘንድ ሰጣቸው።

ይካ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተወልደ እምርያም እምቅድስት ድንግል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ልዩ ሕያው የማይሞት ከንጽሕት ድንግል ማርያም የተወለደ አቤቱ ይቅር በለን።

ልዩ ገዥ ልዩ ኃያል ልዩ ሕያው የማትሞት በዮርዳኖስ ውኃ የተጠመቅህ በዕንጨት መስቀልም የተሰቀልህ አቤቱ ይቅር በለን።

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has born from the holy Virgin Mary; have mercy upon us, Lord.

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has babelized in Jordan and crucified on the tree of the cross; have mercy upon us, Lord.

ዲያቆኑ:ሃሌ ሉያ ቁሙ ወአጽምዑ ከመ ንኩን ድልዋነ ለመንግሥተ ሰማያት ኦ እግዚእነወ አምላክነ መሐረነ ወተሣሃለነ ወረሰየነ ድልዋነ ለሰሚዓ ወንጌል ቅዱስ።

ካህኑ: ወንጌል ቅዱስ ዘዜነወ ሉቃስ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር።

ሉቃስ ያስተማረውን ቅዱስ ወንጌል ይበል።

Priest says the Gospel of Luke is the Word of God.

Read the Holy Gospel that Luke taught.

ሕዝቡ ምሥጋና ላንተ ይገባል ይበሉ።

Let the people say thanksgiving belongs to You.

Read the Gospel of the hour

ሉቃስ ምዕራፍ ፳፫ :፲፫- ፳፮ Luke 23:13-26

# ወንጌል፥ ሉቃስ ምዕ. ፳፫ ቁ. ፲፫-፳፯

13 ጲላጦስም ፥ የካህናትን አለቆችና መኳንንትን ሕዝቡንም በአንድነት
ጠርቶ እንዲህ አላቸው። 14 ሕዝቡን ያጣምማል ብላችሁ ይህን ሰው
ወደ እኔ አመጣችሁት ፤ እነሆም ፥ በፊታችሁ መርምሬ ከምትከሱበት
ነገር አንድ በደል ስንኳ በዚህ ሰው አላገኘሁበትም። 15 ሄሮድስም
ደግሞ ምንም አላገኘም ፤ ወደ እኛ መልሶታልና ፤ እነሆም ፥ ለሞት
የሚያደርሰው ምንም አላደረገም ፤ 16-17 እንግዲያስ ቀጥቼ
እፈታዋለሁ። በበዓሉ አንድ ይፈታላቸው ዘንድ ግድ ነበረና።

[13] And Pilate, when he had called together the chief priests
and the rulers and the people, [14] Said unto them, Ye have
brought this man unto me, as one that perverteth the people:
and, behold, I, having examined him before you, have found
no fault in this man touching those things whereof ye accuse
him: [15] No, nor yet Herod: for I sent you to him; and, lo,
nothing worthy of death is done unto him. [16] I will therefore
chastise him, and release him. [17] (For of necessity he must
release one unto them at the feast.)

18 ሁላቸውም በአንድነት። ይህን አስወግድ ፥ በርባንንም ፍታልን
እያሉ ጮኹ ፤ 19 እርሱም ሁከትን በከተማ አንሥቶ ሰውን ስለ
ገደለ በወኅኒ ታስሮ ነበር። 20 ጲላጦስም ኢየሱስን ሊፈታ ወድዶ
ዳግመኛ ተናገራቸው ፤ 21 ነገር ግን እነርሱ። ስቀለው ስቀለው
እያሉ ይጮኹ ነበር። 22 ሦስተኛም። ምን ነው? ያደረገውስ ክፋት
ምንድር ነው? ለሞት የሚያደርሰው በደል አላገኘሁበትም ፤ ስለዚህ
ቀጥቼ እፈታዋለሁ አላቸው።

**[18] And they cried out all at once, saying, Away with this man, and release unto us Barabbas: [19] (Who for a certain sedition made in the city, and for murder, was cast into prison.) [20] Pilate therefore, willing to release Jesus, spake again to them. [21] But they cried, saying, Crucify him, crucify him. [22] And he said unto them the third time, Why, what evil hath he done? I have found no cause of death in him: I will therefore chastise him, and let him go.**

23 እነርሱ ግን እንዲሰቀል በታላቅ ድምፅ አጽንተው ለመኑት።
የእነርሱ ጩኸትና የካህናት አለቆችም ቃል በረታ። 24
ጲላጦስም ልመናቸው እንዲሆንላቸው ፈረደበት። 25 ያንን
የለመኑትንም ፥ ስለ ሁከት ሰውንም ስለ መግደል በወኅኒ ታስሮ
የነበረውን አስፈታላቸው ፥ ኢየሱስን ግን ለፈቃዳቸው አሳልፎ
ሰጠው። 26 በወሰዱትም ጊዜ ስምዖን የተባለ የቀሬናን ሰው
ከገጠር ሲመጣ ይዘው ከኢየሱስ በኋላ መስቀሉን እንዲሸከም
ጫኑበት።

[23] And they were instant with loud voices, requiring that
he might be crucified. And the voices of them and of the
chief priests prevailed. [24] And Pilate gave sentence that it
should be as they required. [25] And he released unto them
him that for sedition and murder was cast into prison, whom
they had desired; but he delivered Jesus to their will. [26]
And as they led him away, they laid hold upon one Simon, a
Cyrenian, coming out of the country, and on him they laid
the cross, that he might bear it after Jesus.

## ከወንጌል በኋላ ካህኑ፦

## After the Reading of the Gospel

ጊዜ ሠለስቱ ሰዓት ወሰድዎ ለኢየሱስ ውስተ ዓውደ ምኲናን።

**At 9:00 a.m they took Jesus to the court to be judged.**

ሦስት ሰዓት በሆነ ጊዜ ጌታ ኢየሱስን ወደ ፍርድ ዐደባባይ ወሰዱት።

ይካ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተወልደ እምርያም እምቅድስት ድንግል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ልዩ ሕያው የማይሞት ከንጽሕት ድንግል ማርያም የተወለደ አቤቱ ይቅር በለን።

ልዩ ገዥ ልዩ ኃያል ልዩ ሕያው የማትሞት በዮርዳኖስ ዉኃ የተጠመቅህ በዕንጨት መስቀልም የተሰቀልህ አቤቱ ይቅር በለን።

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has born from the holy Virgin Mary; have mercy upon us, Lord.

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has babelized in Jordan and crucified on the tree of the cross; have mercy upon us, Lord.

ዲያቆኑ:ሃሌ ሉያ ቁሙ ወአጽምዑ ከመ ንኩን ድልዋነ ለመንግሥተ ሰማያት ኦ እግዚእነወ አምላክነ መሐረነ ወተሣሃለነ ወረሰየነ ድልዋነ ለሰሚዓ ወንጌል ቅዱስ።

ካህኑ: ወንጌል ቅዱስ ዘሰበከ ዮሐንስ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር።

ዮሐንስ ያስተማረውን ቅዱስ ወንጌል ይበል።

Priest says the Gospel of John is the Word of God.

Read the Holy Gospel that John taught.

ሕዝቡ ምሥጋና ላንተ ይገባል ይበሉ።

Let the people say thanksgiving belongs to You.

Read the Gospel of the hour

ዮሐንስ ምዕራፍ ፲፱:፩-፲፪ John 19:1-12

# ወንጌል፥ ዮሐንስ ምዕ ፲፱ ቁ. ፩-፲፪

1 በዚያን ጊዜም ጲላጦስ ኢየሱስን ይዞ ገረፈው። 2 ወታደሮችም
ከእሾህ አክሊል ጎንጉነው በራሱ ላይ አኖሩ ቀይ ልብስም አለበሱት ፤
3 እየቀረቡም። የአይሁድ ንጉሥ ሆይ ፥ ሰላም ለአንተ ይሁን
ይሉት ነበር ፤ 4 በጥፊም ይመቱት ነበር። ጲላጦስም ደግሞ ወደ
ውጭ ወጥቶ። እነሆ ፥ አንዲት በደል ስንኳ እንዳላገኘሁበት ታውቁ
ዘንድ እርሱን ወደ ውጭ አወጣላችኋለሁ አላቸው። 5 ኢየሱስም
የእሾህ አክሊል ደፍቶ ቀይ ልብስም ለብሶ ወደ ውጭ ወጣ።

[1] Then Pilate therefore took Jesus, and scourged him. [2] And the soldiers platted a crown of thorns, and put it on his head, and they put on him a purple robe, [3] And said, Hail, King of the Jews! and they smote him with their hands. [4] Pilate therefore went forth again, and saith unto them, Behold, I bring him forth to you, that ye may know that I find no fault in him. [5] Then came Jesus forth, wearing the crown of thorns, and the purple robe. And Pilate saith unto them, Behold the man!

6 ጲላጦስም። እነሆ ሰውዬው አላቸው። የካህናት አለቆችና ሎሌዎች
ባዩትም ጊዜ። ስቀለው ስቀለው እያሉ ጮኹ። ጲላጦስም። እኔስ
አንዲት በደል ስንኳ አላገኘሁበትምና እናንተ ወስዳችሁ ስቀሉት
አላቸው። 7 አይሁድም መልሰው። እኛ ሕግ አለን ፥ እንደ
ሕጋችንም ሊሞት ይገባዋል ፥ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ
አድርጎአልና አሉት። 8 ስለዚህ ጲላጦስ ይህን ነገር በሰማ ጊዜ
አግጅ ፈራ ፤ 9 ተመልሶም ወደ ገዡ ግቢ ገባና ኢየሱስን። አንተ
ከወዴት ነህ? አለው። ኢየሱስ ግን አንድ እንኳ አልመለሰለትም።

**[6] When the chief priests therefore and officers saw him, they cried out, saying, Crucify him, crucify him. Pilate saith unto them, Take ye him, and crucify him: for I find no fault in him. [7] The Jews answered him, We have a law, and by our law he ought to die, because he made himself the Son of God. [8] When Pilate therefore heard that saying, he was the more afraid; [9] And went again into the judgment hall, and saith unto Jesus, Whence art thou? But Jesus gave him no answer.**

10 ስለዚህ ጲላጦስ። አትነግረኝምን? ልሰቅልህ ሥልጣን እንዳለኝ
ወይም ልፈታህ ሥልጣን እንዳለኝ አታውቅምን? አለው። 11
ኢየሱስም መልሶ። ከላይ ካልተሰጠህ በቀር በእኔ ላይ ምንም
ሥልጣን ባልነበረህም ፤ ስለዚህ ለአንተ አሳልፎ የሰጠኝ ኃጢአቱ
የባሰ ነው አለው። 12 ከዚህ በኋላ ጲላጦስ ሊፈታው ፈለገ ፤ ነገር
ግን አይሁድ። ይህንስ ብትፈታው የቄሣር ወዳጅ አይደለህም ፤
ራሱን ንጉሥ የሚያደርግ ሁሉ የቄሣር ተቃዋሚ ነው እያሉ ጮኹ።

[10] Then saith Pilate unto him, Speakest thou not unto
me? knowest thou not that I have power to crucify thee,
and have power to release thee? [11] Jesus answered,
Thou couldest have no power at all against me, except it
were given thee from above: therefore he that delivered me
unto thee hath the greater sin. [12] And from thenceforth
Pilate sought to release him: but the Jews cried out,
saying, If thou let this man go, thou art not Caesar's friend:
whosoever maketh himself a king speaketh against
Caesar.

## ከወንጌል በኋላ ካህኑ፦

## After the Reading of the Gospel

**ጊዜ ሠለስቱ ሰዓት ቀሰፎ ጲላጦስ ለኢየሱስ ወመጠዎሙ ይስቅልዎ።**

**At 9:00 a.m Pilate scourged Jesus and gave Him up to be crucified.**

ሦስት ሰዓት በሆነ ጊዜ ጌታ ኢየሱስን ገርፎ ይሰቅሉት ዘንድ ሰጣቸዉ።

ይካ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተወልደ እምርያም እምቅድስት ድንግል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ልዩ ሕያው የማይሞት ከንጽሕት ድንግል ማርያም የተወለደ አቤቱ ይቅር በለን።

ልዩ ገዥ ልዩ ኃያል ልዩ ሕያው የማትሞት በዮርዳኖስ ዉኃ የተጠመቅህ በዕንጨት መስቀልም የተሰቀልህ አቤቱ ይቅር በለን።

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has born from the holy Virgin Mary; have mercy upon us, Lord.

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has babelized in Jordan and crucified on the tree of the cross; have mercy upon us, Lord.

ከወንጌል በኋላ ካህኑ፦

ጸልዩ በእንተ ጽንዐ ዛቲ የሚባለውን ጸሎት በየክፍሉ ያንብብ ሕዝቡም በየምዕራፉ እግዚኦ ተሣሃለነ (አቤቱ ይቅር በለን) እያሉ እየሰገዱ ይመልሱ።

After the Reading of the Gospel

LITANY PRAYER

The priest prays the Morning Litany prayer, after each part, the congregation responds with Lord have mercy (Egzio Tesehalene) and kneel.

ይካ. ስለዚች ቦታ መጽናት በቅዱሳን አባቶቻችን ስም ስለሚጠሩም ቦታዎችና ገዳማት በውስጣቸውም ስለሚኖሩ ሽማግሎች በጠቅላላም ስለዚህ ዓለም መጠበቅ ጸልዩ ጌታ ከክፉ ሁሉ ይጠብቃቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for this church, and all Orthodox churches, the desert monasteries, the elders dwelling therein, and for the peace of the whole world, that the Lord our God may protect us and them from all evil and malice and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በዚች በታና በሌሎችም በታዎች ስለሚገኙ በነፍስ በሥጋ ስለታመሙ አባቶቻችንና ወንድሞቻችን ጸልዩ። ጌታ ለኛም ለነርሱም ሕይወቱን ጤንነቱን ሰጥቶ በጎ ነገርን ያደርግ ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask God for our fathers and brothers who are sick with any sickness whether in this place or in any place, that the Lord our God, may grant them and us health and healing, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በባሕር በየብስ በወንዝ በቀላይ በሌላውም መንገድ ሁሉ ስለሚጓዙ አባቶቻችንና ወንድሞቻችን ጸልዩ። ጌታ በቀና መንገድ መርቶ በሰላም በደስታ ወደ መኖሪያቸዉ ይመልሳቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for our fathers and brothers who are traveling and those who intend to travel in all places. May God aid their ways. Those who are traveling by seas, rivers, lakes, roads or any other means, may the Lord our God guide them, bring them back to their dwelling place in peace, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ከእርሻ ስለሚገኝ ፍሬ ስለ ዛፎችና ስለ ወይኖች በዓለምም ውስጥ ፍሬን ስለምታፈራ ዕንጨት ሁሉ ጸልዩ። ጌታ ባርኮ አብዝቶ ከጥፋትም ጠብቆ ለፍጻሜ ፍሬ ያደርሳቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for the winds of the heaven, the fruits of the earth, all the trees and vineyards and all fruitful trees in the world, that Christ our God may bless them, preserve them, and bring them to completion in peace, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. አምላካችን ክርስቶስ በገዡችና በፈራጆች ፊት ይቅርታንና ምሕረትን እንዲሰጠን ልቡናቸውንም ሁልጊዜ በቸርነቱ እንዲያራራልን ጸልዩ። ኃጢአታችንንም ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask that God may grant us mercy and compassion before the sovereign rulers and incline their hearts with goodness towards us at all times, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በክርስቶስ አምነው ከዚህ በፊት ስለሞቱ ወንድሞቻችንና አባቶቻችን ጸልዩ። እነርሱም የተቀደሱ አባቶቻችን ሊቃነ ጳጳሳትና አባቶቻችን ጳጳሳት አባቶቻችን ኤጲስ ቆጶሳት አባቶቻችን ቆሞሳት አባቶቻችን ቀሳውስት ወንድሞቻችን ዲያቆናት አባቶቻችን መነኮሳትና አባቶቻችን ሕዝባውያን ሌሎችም ከክርስቲያን ወገን በሞት ያረፉት ሁሉ ናቸዉ። ጌታ ዕረፍተ ነፍስን ይሰጣቸው ዘንድ ጸልዩ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚአ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for our fathers and brethren who have fallen asleep and reposed in the faith of Christ since the beginning, our holy fathers the patriarchs, our fathers the metropolitans, our fathers the bishops, our fathers the hegomens, our fathers the priests, our brethren the deacons, our fathers the monks, and our brethren the laymen, and for the repose of all Christians who have fallen asleep, that the Lord our God may repose their souls, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. የክርስቲያን እምነት ላልተፈጸመላቸው ወገኖቻችን ጸልዩ። ጌታ ይባርካቸው ዘንድ እስከ መጨረሻዪቱም ሕቅታ በቀናች ሃይማኖት ያጸናቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for the catechumens, that the Lord our God may bless them, enlighten their hearts, confirm them in the Orthodox faith until the last breath, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ሐዋርያት ስላጸኗትና ስለሰበሰቧት ስለ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ሰላም ጸልዩ። ስለ ሕዝቡም ሁሉ መዳንና ስለ ቦታው ሁሉ መጠበቅ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray for the peace of the church, for the apostles and the gathering of the church. And for the salvation of all the people, and for all the places and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ንዑድ ክቡር ስለሚሆን ስለአባታችን ____________የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሊቀ ጳጳሳቱ አባታችን አቡነ_____________ና ብፁዕ አባታችን አቡነ_____________ በሕይወት በሞት በኑሮም ስለሚደርስባቸዉ ሁሉ ጸልዩ። ሕይወታቸውን ጠብቆ ለብዙ ዘመን በመንበረ ስብከታቸው ያጸናቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for the life of our honored father, our patriarch Abba (...), the archbishops _______ and ____________, that the Lord God may keep them and confirm them on his throne for many years and long peaceful times, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ስለ አንድነታችንና የቀናች ሃይማኖት ስላላቸው ሕዝበ ክርስቲያን አንድነት ጌታ ይጠብቃቸውና በሰላም ያስፈጸማቸው ዘንድ ጸልዩ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray that the Lord will guard them and make them live in peace by the unity of the Christian community because of our unity and of the true religion and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ለከበረች ቤተ ክርስቲያን መባን ስለሚያቀርቡ ሰዎች ጸልዩ። ጌታ ይባርክላቸው ዘንድ። በሥራቸውም እንዲጸኑ ይረዳቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray for those who offer an offering for the glorious church. That the Lord may bless them. That he might sustain them and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ምእመናንን በየስፍራቸው ሁሉ በቸርነት ስለሚያስቡና ለበጎ ነገር ስለሚደክሙ የቀና ሃይማኖት ስላላቸው ሰዎች ሁሉ ጸልዩ። ጌታ ባርኮ ዋጋቸውን እንዲሰጣቸውና ይቅርታን እንዲያደርግላቸው። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray for every believer who has the true religion and for those who care and labor for the the good of the Church. That the Lord bless them and reward them and forgiveness and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ለቍርባን የሚሆን ስንዴውን ዕጣኑን ዘቢቡን የሚነበብባቸው መጻሕፍትን ሌላውንም የቤተ መቅደስ ዕቃ ሁሉ በመስጠት ስለሚያስቡ ሰዎች ጸልዩ። ጌታ በመንግሥተ ሰማያት የበለጠ ዋጋ ይሰጣቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for those who care for the sacrifices, the oblations, the wine, the oil, the incense, the covering, the books of prayers, the altar vessels, that the Lord our God may reward them in heavenly Jerusalem, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ስማቸውን በያንዳንዳቸው እንድንጠራ ስላዘዙን ስለ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና ስለ ታላላቆች አባቶች ጸልዩ። ጌታ በረከትን ሰጥቶ በባለስልጣኖችና በሹማምት ፊት በፈራጆችም አደባባይ ፍቅርን መወደድን ያድላቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for all for our fathers, the Orthodox metropolitans and bishops in every place who asked us to remember them by name in our prayers, that the Lord God may bless and remember them with His mercy and grant them grace before powerful rulers, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በደዌ ሥጋ በደዌ ነፍስ ለደከሙና ለተቸገሩ ለባልቴቲቱም አባት እናት ለሌላቸው ለድኆቹ ልጆችና ለተጨነቁ ሰዎች ዘር ለዘሩ እርሻ ላረሱ ለሚሸጡ ለሚገዙ ለተጨነቀችም ሰውነት በማናቸውም ቦታ ሁሉ ጸልዩ። ጌታ ራርቶ ይቅር እንዲላቸው። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for the poor, the needy, the afflicted, the weak, the farmers, the traders, the fatherless and all those who are in adversities of any kind, that the Lord our God has kindness on them and us, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በግዞት በምርኮኝነት ተይዘው ለተጨነቁ አገር ለቀው ለተሰደዱ በአጋንንት አሽከላም ለተያዙ ሰዎች ጸልዩ። ጌታ ከግዞት ከምርኮኝነት ያወጣቸው ዘንድ። ይቅርታውንም ሰጥቶ እነርሱንም እኛንም ያድነን ዘንድ። ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for those who are in the distress of prisons and dungeons, and those in captivity or exile, and those who are afflicted by devils, that the Lord our God may free them from their hardships, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ለነፍሳቸው ይቅርታን እየፈለጉ ክቡር በሆነ በዚህ ስፍራ ስለተሰበሰቡ ሁሉ ጸልዩ። የአምላካችን የጌታችን ይቅርታ ፈጥኖ ይደረግላቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for all the souls assembled with us this day, in this holy place, seeking mercy for their souls, that the mercies of the Lord our God may come upon them speedily and us, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በዚህ ዓመት ስለዝናም መዝነም ስለ ባሕርና ስለ ወንዞችም መምላት ጸልዩ። እውነተኛ አምላካችን ክርስቶስ በረከቱን ሰጥቶ እስከ ልካቸው እንዲመላቸው ለምድርም ልምላሜውን ሰጥቶ ደስ እንዲያሰኛት ሥጋዊን ደማዊን ሁሉ በረድኤት እንዲያጸና ለእንስሳትም ሁሉ ድኅነትን እንዲሰጥ ጸልዩ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚአ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for the rising of the waters of the rivers this year, that Christ our Lord may bless them and raise them according to their measure, give joy to the face of the earth, sustain us, deliver man and beast, and lift away from the world death, inflation, plagues, annhilation, evacuation, and the sword of the enemies. Grant peace and tranquility in our holy church and raise the state of Christians in every place and around the whole world till the last breath, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በጸሎታችን እናስባቸው ዘንድ አስቡን (አትርሱን) ስላሉን ሰዎች ጸልዩ። እግዚአብሔር በበጎ ያስባቸው ዘንድ በየጊዜውም ይቅር ይላቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for those who requested from us to remember them in our prayers by name, that the Lord our God may remember them according to His goodness at all times, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ይህችን ሳምንት ጌታ በበጎ ይፈጸማት ዘንድ ከኛም የጠላትን መፈታተን አርቆ ሰውነታችንን እንዲያድን ይቅር እንዲለን ጸልዩ። ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray that the Lord will complete this week in peace and to save our bodies from the temptation of our enemy and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ጌታችን አምላካችን ራርቶ ይቅር እንዲለን ልመናችንንም ተቀብሎ ለዚያ ለፋሲካው እንዲያበቃን የትንሣኤውንም ብርሃን በፍጹም ደስታ እንዲያሳየን ጸልዩ። ኃጢአታችንንም ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for this Holy Week of Pascha, of our Good Savior, that He may complete it for us in peace and show us the joy of His holy resurrection in safety and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ክርስቶስ አምላክነ ዘመጽአ ወሐመ በእንቲአነ በሕማማቲሁ ቤዘወነ።

ክርስቶስ አምላካችን ሰዉ ሁኖ መጥቶ ስለእኛ መከራ ተቀበለ በመከራውም አዳነን።

Christ our Lord who came down from heaven, has suffered for us and saved us through His affliction.

ንሰብሖ ወናልዕል ስሞ ኅቡረ እስመ ውእቱ ገብረ መድኃኒተ በዕበየ ሣህሉ።

እርሱ በይቅርታው ገናናነት ድኅነትን አድርጎአልና በአንድነት ፈጽመን ስሙን እናመስግን።

According to His steadfast love, together we praise and exalt His name because he saves us.

ትእዛዝ ሕዝቡ በሁለት ክፍል ሁነው የሚከተለዉን ጸሎት ሁለት ጊዜ በመከታተል አንድ ጊዜ በማስተዛዘል ይበሉት።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን እብኖዲ ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ታዖስ ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ማስያስ ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ኢየሱስ ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ክርስቶስ ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን አማኑኤል ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ትስቡጣ ናይናን ኪርያላይሶን።

ትእዛዝ ከዚህ በኋላ ኪርያላይሶን (41) አርባ አንድ ጊዜ ይባል። ይኸውም በአንድ ወገን ሃያ አንድ በሌላው ወገን ሃያ ጊዜ።

## መልክአ ሕማማት ዘሠለስቱ ሰዓት

### ጸሎት ሰብዓቱ ጊዜያት ዘደረሰ አባ ጊዮርጊስ መምህር ዘጋሥጫ ሰላመ ማርያም ዘሠለስቱ ሰዓት ።

የሰባቱ ጊዜያት የአባ ጊዮርጊስ ጸሎት የሦስት ሰዓት የእመቤታችን ሰላምታ

ሰላም ለኪ ማርያም ርግብ ሰማያዊት ሰላም ለኪ ፤ወንስር መንፈሳዊት ሰላም ለኪ፡፡

- ሰማያዊት ርግብ መንፈሳዊት ንሥርም እመቤታችን ሆይ ሰላምታ ይገባሻል፡፡

ሥምረተ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ መላኪ እምትካት ዘኃረየኪ ሰላም ለኪ፡፡

- የአሸናፊ የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ከቀድሞ የመረጠሽ እመቤታችን ሆይ ሰላምታ ይገባሻል፡፡

ጊዜ ጸልዮትኪ በጽሐ ከመ ኢይሙት ገብርኪ ቅድሜሁ ስግዲ ወአስተብርኪ እንዘ ታዘክሪዮ እም ጻማ ንግደትኪ ርግብየ የዋሂት ለየዋህ ወልድኪ፡፡ 3ተ ጊዜያተ በል፡፡

- የዋሂት ርግብ እመቤቴ ሆይ እኔ አገልጋይሽ እንዳልሞት የምትጸልዪበት ሰዓት በደረሰ ጊዜ የስደትሽን ድካም ለደጉ ልጅሽ እያሳሰብሽው በፊቱ ፈፅመሽ ስገጂ፡፡

# ስብሐተ ኢየሱስ ዘሠለስቱ ሰዓት

## (የሦስት ሰዓት የጌታችን ምስጋና)

ስብሐት ለከ እኤምኀ አዕጋሪከ በጊዜ ሠለስቱ ሰዓት ቅድመ ጲላጦስ ዘቆማ፡፡ ኢየሱስ ጠቢብ ወንጉሥ ፌማ ዘአድከምከ ኃይለ መስቴማ ስብሐት ለከ፡፡

- የሰይጣንን ኃይል የአደከምክ እውነተኛ ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ በሦስት ሰዓት በጲላጦስ ፊት የቆሙ እግሮችህን እጅ እየነሳሁ ምስጋናን አቀርብልሃለሁ፡፡

እንዘ ይሰልቡ ልብሰከ ወከዳነከ ጸዓዳ እንተ አልበሱከ ከለሜዳ ኢየሱስ ንጉሠ ይሁዳ ስብሐት ለከ፡፡

- ነጭ የሚሆን መጎናጸፊያህንና ቀሚስህን ገፈው ቀይ ግምጃ ያለበሱህ የይሁዳ ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ምስጋና ይገባሃል፡፡

ተፈጸመ ብከ እግዚኦ ቃለ ዳዊት ንጉሥ ሶበ ተካፈሉ በዕፃ ወፋስ ልብስከ ልብሰ ሞገስ ስብሐት ለከ፡፡

- የክብር ልብስ በሚሆን ልብስህ ላይ ዕጣ ተጣለው በተካፈሉ ጊዜ አቤቱ የንጉሥ ዳዊት ቃል በአንተ ተፈጽሞአልና ምስጋና ይገባሃል፡፡

ማኅበራነ አይሁድ አሜሃ አዕፅምቲከ ኈለቁ ወዲበ ገድከ ምራቀ ወረቁ ላዕሌከ እንዘ ይሣለቁ ስብሐት ለከ፡፡

- ያንጊዜ የአይሁድ ማኅበር በአንተ ላይ እየተዘባበቱ አጥንቶችህን የቆጠሩ በፊትህም ላይ ምራቃቸውን የተፉብህ አቤቱ ምስጋና ይገባሃል

እፎ መጠከ ዘባነከ ለጥብጣቤ መቅሰፍት ወጻዕቅ ገድከኒ ተወክፈ ኀፍረተ ምራቅ ዘአእሩግ ወዘደቂቅ ስብሐት ለከ፡፡

- ጀርባህን በሚያስጨንቅ የጅራፍ ግርፋት እንደምን ሰጠህ ፊትህን የልጆችንና የሽምግሌዎችን የሐፍረት ምራቅ እንደምን ተቀበልከ? አቤቱ ምስጋና ይገባሃል፡፡

አዕርግ ለነ እግዚኦ በጊዜ ሠለስቱ ሰዓት ዘናቈርብ ለከ መሥዋዕተ ስብሐት ሕገ ሠርዐ ሐዋርያት ስብሐት ለከ፡፡ 3ተ ጊዜያተ በል፡፡

- ሐዋርያት በሰሩት ሕግ በሦስት ሰዐት ያቀረብንልህን የምስጋና መሥዋዕት ታሳርግልን ዘንድ ምስጋና ይገባል፡፡ 3ት ጊዜ በል።

ኀበ ሐዋርያት ኀብሩ በድርሐ ጽዮን እንግልጋ ዘፈኖከ ሎሙ መንፈሰ ጸጋ ፈኑ ለነ እንበለ ንትጋ ያኀድገነ ምግባረ ዘሥጋ፡፡ 3ተ ጊዜያተ በል፡፡

- በጽዮን አዳራሽ ሐዋርያት በተሰበሰቡ ጊዜ የስጦታ መንፈስ ቅዱስን እንደላክላቸው ሥጋዊ ሥራን ያስተወን ዘንድ ያለጉደል ላክልን፡፡

# ስብሐተ ሥላሴ ዘሠለስቱ ሰዓት
## (የሦስት ሰዓት የሥላሴ ምስጋና)

ግናይ ለከሙ ሥሉስ ቅዱስ ጠበብተ ስድስቱ ዕለት አዳምሃ በሣልስት ሰዓት ዘፈጠርከሙ እንበለ ሞት ግናይ ለከሙ፡፡

- አዳምን በሦስት ሰዓት ያለሞት የጠፈራችሁ የሰባቱ ዕለታት ጥበበኞች ሥሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል፡፡

ድኅረ ተፈጥሮቱ ለሰብእ በኅልቄ ዕለታት አርብዓ እለ ታብዕሉ ወታነድዩ ሰብአ መጽሐፍ ከመ አይድዐ ግናይ ለከሙ፡፡

- መጽሐፍ እንደተናገረው ሰው በተፈጠረ በአርባኛው ቀኑ በእናቱ ማኅፀን የምታስቀሩና የምታለመልሙ ሥሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል፡፡

ለሐዋርያተ ጽድቅ ሥላሴ በጊዜ ሰዓት ሠለስቱ በልሳን ሰብዓ ወክልኤቱ ሥላሴክሙ ዘትከሥቱ ግናይ ለክሙ።

- የቀኑ ብርሃን በርትቶ ሦስት ሰዓት በሆነ ጊዜ በሰባ ሁለት ቋንቋ ሦስትነታችሁን የምትገልጹ የአብርሃም ቤት እንግዶች ሥሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል።

ለጸላሔ ብርሃን ሰብእ ከመ ዘእኩይ ምግባሩ እንዘ ትሬእዩ ወተአምሩ ሥላሴ ዘትምሕሩ ግናይ ለክሙ።

- ብርሃንን የሚጠላ ሰውን ሥራው ክፉ እንደሆነ ፈጽማችሁ ስታውቁ ይቅር የምትሉ ሥሉስ ቅዱስ ሆይ ምስጋና ይገባችኋል።

ድኅረ ሰብኮ ላሕም አቀመ በደብረ ኮሬብ መካን ካህን አሮን ወምእመን ዘመሐርክምዎ አሮን ካህን መሐሩኒ ሥላሴ ኄራን። ሰብሐት ለእግዚአብሔር። 3ተ ጊዜያተ በል።

- ታማኝ የነበረ ካህኑ አሮን በኮሬብ ተራራ በሰላም አምሳል ጣኦት በአቆመ ጊዜ ካህን አሮንን ይቅር ያላችሁን ይቅር ባይ ሥሉስ ቅዱስ ሆይ እኔንም ይቅር በሉኝ።

ስብሐት ለእግዚአብሔር ኪያነ ዘፈጠረ ከመ ናምልኮ

ስብሐት ለማርያም እመ አምላክ እግዝእትነ ወመድኃኒትነ

ስብሐት ለመስቀለ ክርስቶስ ዕፀ መድኃኒት ኃይልነ ወፀወንነ።

ጸሎተ ቡራኬ

## የቡራኬ ጸሎት Prayer of Blessing by Priest

ከዚህ በኋላ ሕዝቡ ይቀመጡ። ካህኑ ግን ቆሞ ፊቱን ወደ ሕዝቡ መልሶ የቡራኬውን ጸሎት ይበል።

Let the people seat and the priest will stand and turn his face to the people, and say the prayer of the blessing.

የኢየሱስ ክርስቶስ ማኅበር ቤተ ሰብእ የምትሆኑ ወንድሞቼ ሆይ በዚች በጌታ ማደርያ መሰብሰባችሁ አይሁድ ፋሲካቸውን በአደረጉበት ቀን በመቅናታቸው ለኀጢያተኞች አሳልፈው በሰጡ ጊዜ ጌታችን የተቀበለውን መከራ ሞቱን ኅኑን መወጋቱን ደሙን ማፍሰሱን መስቀሉን እያሰባችሁ ነው።

ስለዚህ እግዚአብሔር ድካማችሁንና ጸሎታችሁን ስግደታችሁንና መዝሙራችሁን ይቀበልላችሁ ከኀሊና ሥጋ የተነሣ በኀሊና መንፈስ የምትሹትን ሁሉ በፈቃዱ ይፈጽምላችሁ።

ተስፋ ትንሣኤውን ይስጣችሁ የደስታውን ቃል ያሰማችሁ በይቅርታው ቸርነት ከመከራው ይሠውራችሁ።

ደቀ መዛሙርቱን እንደጐበኛቸው እንዲሁ እናንተንም ይጎብኛችሁ።

በኀጢአት እንዳትወድቁ ይደግፋችሁ ከሐዘናችሁ ያረጋጋችሁ ከድካማችሁ ያጽናችሁ።

እናንተንም ለማገልገል የተዘጋጀሁ ከምሆን ከእኔ ከወንድማችሁ ጋር።

በሩቅና በቅርብ ካሉ በጸሎታችሁም ከተማጸኑ ወንድሞቻችን ሁሉ ጋራ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ በደስታ ቀን ከናንተ ጋር አንድ ይሆኑ ዘንድ።

በአባታችሁ ጉባኤ በቀኙ ያቁማችሁ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ተድላ ደስታ ወደሚገኝበት ቤቱ ወደ መንግሥተ ሰማያት ያግባችሁ ለዘላለሙ።

ሕዝቡ ስለ ክርስቶስ ሥጋና ደም አሜን ይደረግልን ይሁን ይሁን ይበሉ።

# ግብረ ሕማማት ዓርብ ቀን
# Gibire Himamati Friday

**በስድስት ሰዓት**
**12 PM**




I.N.R.I.

ትእዛዝ ዓርብ በስድስት ሰዓት ካህናት በከበረች በቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው የዳዊትን መዝሙር አኮኑ ለእግዚአብሔር (መዝሙር 6፲: ፩) ከሚለው ጀምሮ እስከ ወአጽገቦሙ መዓረ እምኰኵሕ ተሀበኒ ተምኔትየ ኵሎ አሚረ (መዝሙር 80: 16) የሚለው ድረስ ይፀልዩ።

ውዳሴ ማርያምን የረቡዕን ይድገሙ። መሪ በአንድ ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ይበል።

ti'izazi (Order) On Friday 6th hour, let the priests gather in Church to pray the Song of David (Psalms 61: 1) to Psalms 80:16

Let them pray the Wednesday Praise of Mary and chant the below hymn.

ትእዛዝ ዓርብ በስድስት ሰዓት ካህናቱ ይፀልዩ መሪዉ በዘጠኝ ሃሌታ ይበል።

በዕዝል ዜማ

በመሪ ወገን አንድ ጊዜ በመከተል በተመሪ ወገን አንድ ጊዜ ለሦስተኛ ጊዜ ደግሞ በጋራ ይባላል።

ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ

ተሰቅለ ተሰቅለ ወሐመ ቤዛ ኵሉ ኮነ ዬ ዬ ዬ በመስቀሉ ቤዘወነ እሞት ባልሐነ።

ቅድመ ዓለም የነበረ ዛሬም ያለ ወደፊትም ዓለምን አሳልፎ የሚኖር ተሰቀለ ታመመ የዓለም ቤዛ ሆነ ወዮ ወዮ ወዮ በመስቀሉ አዳነን ከሞትም ነፃ አወጣን።

ሁሉም በአንድነት እየሰገዱ 6 በግራ 6 በቀኝ በአንድ ዓይነት ዜማ አሥራ ሁለት ጊዜ ለከ ኃይል ይበሉ።

This is chanted 12 times (6 times alternating on the right and left aisles of the Church) with prostrations and after each they recite "Our Father..."

ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወዕዘዝ ለዓለም ዓለም።

ኃይል ክብር ጌትነት ገኽነት ለዘላለሙ ለአንተ ይገባል።

For Thine is the power, the glory, the blessing, and the majesty, forever and ever.

ዐማኑኤል አምላኪየ ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወዕዘዝ ለዓለም ዓለም።

ፈጣሪዬ ዐማኑኤል ሆይ ኃይል ክብር ጌትነት ገኽነት ለዘላለሙ ለአንተ ይገባል።

Emmanuel my God, For Thine is the power, the glory, the blessing, and the majesty, forever and ever.

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወዕዘዝ ለዓለም ዓለም።

ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ኃይል ክብር ጌትነት ገኽነት ለዘላለሙ ለአንተ ይገባል።

O My Lord Jesus Christ, for Thine is the power, the glory, the blessing, and the majesty, forever and ever.

ኃይልየ ወፀወንየ ዉእቱ እግዚእየ እስመ ኮንከኒ ረዳእየ እብል ወአኮቴት

አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ

ኃይሌና አምባ መጠጊያዬ ጌታዬ ነህ ረዳት ሁነኸኛልና በምሥጋና እንዲህ እላለሁ

በሰማያት ያለህ አባታችን ሆይ ስምህ ይመስገን

The Lord is my power, strength and shelter; for you became my Holy Salvation, I say with thanks-giving

Lord's prayer: Our Father

## አቡነ ዘበሰማያት / Abune Zebesemayat / አባታችን ሆይ / Our Father

አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ ትምጻእ መንግሥትከ ወይኩን ፈቃደከ በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር ሲሳየነ ዘለለ ዕለትነ ሀበነ ዮም ንኅድግ ለዘአበሰ ለነ ወጌጋየነ ከመ ንሕነኒ ንኅድግ ለዘአበሰ ለነ ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት አላ አድኅነነ ወባልሐነ እምኵሉ እኩይ እሰመ ዚአከ  ይእቲ መንግሥት ኃይል ወስብሐት ለዓለመ ዓለም አሜን ።

**Abune Zebesemayat Yitkedes Simike Timsa Mengistike Weyikun Fekadeke Bekeme Besemay Kemahu Bemedir Sisayene Zelele Ilitene Habeneyom Hidig Lene Abesane Wegegayene Keme Nihinenee Nihidig Leze Abese Lene Etabiane Igzeeo Wiste Mensut Ala Addihanene Webalihane Imkwulu Ikuy Isme Zeake  Yeite Mengist Hayl We Sebhat Lealem alem Amen.**

**Our Father who art in Heaven, Hallowed be thy name. Thy Kingdom come. Thy will be done On Earth as it is in Heaven.  Give us this day our daily bread And forgive us our trespasses  As we forgive those who trespass against us And lead us not into temptation But deliver us from evil one in Christ Jesus Our Lord.  For thine is the Kingdom The Power and the Glory Forever and ever. Amen.**

ለአምላክ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለአምላክነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to God forever and ever.

ለሥሉስ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለሦስትነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to the Holy Trinity forever and ever.

ለማሕየዊ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለአዳኝነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to the Life giver forever and ever.

ለእዘዙ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለጌትነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to His Glory forever and ever.

ለመንግሥቱ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።
ለመንግሥቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።
Honour and Glory be to His Kingdom forever and ever.

ለዕበዩ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።
ለገናናነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።
Honour and Glory be to His Majesty forever and ever.

ለሥልጣኑ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።
ለሥልጣኑ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።
Honour and Glory be to His Power forever and ever.

ለምኵናኑ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።
ለፈራጅነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።
Honour and Glory be to His Authority forever and ever.

ለኢየሱስ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለኢየሱስ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to Jesus forever and ever.

ለክርስቶስ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለክርስቶስ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to Christ forever and ever

ለሕማሙ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለመከራው ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to His Suffering forever and ever

ለመስቀሉ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለመስቀሉ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to the Cross forever and ever

ለከ ይደሉ ኃይል ለከ ይደሉ ስብሐት ወለከ ይደሉ አኮቴት ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለመ ዓለም።

ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ለአንተ ከሀሊነት ይገባሃል ለአንተ ክብር ይገባሃል ለአንተ ከምስጋና ይገባሃል ለዘላለሙ።

Power, Glory and blessing be to my Lord Jesus Christ forever and ever.

የዓርብ ፲፪ ሰዓት ምንባባት

Friday 12 PM Readings

# የተአምረ ማርያም መቅድም
## Introductory Chant to the Miracle of Mary

ምንተኑ አዐስየኪ ዕሴተ። በእንተ ኵሉ ዘገበርኪ ሊተ። ማርያም ሠናይት ዘታፈቅሪ ምሕረተ። ሶበሰ ትትዓቀቢ ዘዚአየ ኀጢአተ። እምኢሐዮውኩ አሐተ ሰዓተ።

ምሕረትን የምትወጂ መልካሚቱ ማርያም ስለአደረግሽልኝ ሁሉ ምን ዋጋ እከፍልሻለሁ? የእኔንም ኀጢአት የምትቈጣጠሪ ቢሆን አንዲት ሰዓት እንኳን ባልኖርሁ ነበር።

በሰላመ ገብርኤል መልአክ ኦ እግዚእትየ ማርያም ሰላም ለኪ። ድንግል በኅሊናኪ ወድንግል በሥጋኪ። እመ እግዚአብሔር ጸባኦት ሰላም ለኪ። ቡርክት አንቲ እምአንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ። ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልእተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ በመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እልሻለው። በሐሳብሽ ድንግል ነሽ በሥጋሽም ድንግል ነሽ። የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናት ሆይ ሰላምታ ላንቺ ይገባል፡፡ ከሴቶች ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ። የማህፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው፡፡ ጸጋን የተሞላሽ ሆይ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና ደስ ይበልሽ።

ተአምረ ማርያም ይነበባል።

Reading of the Miracles of Saint Mary

## ከተአምረ ማርያም በኋላ

## After reading the Miracles of Saint Mary chant the following

**ወላዲተ አምላክ ማርያም እንበለ ሰብሳብ ወሩካቤ። በይነ ዘአቀረብኩ ለኪ ንስቲተ ቃለ ይባቤ። ፈትቲ እሙ በረከተ አፉኪ መዓዛ ከርቤ። እስመ ለነዳይ ብእሲ ወለዘረከቦ ምንዳቤ። ኅብስተከ ፈትት ኢሳይያስ ይቤ።**

ያለ ርኩሰትና ያለ ሩካቤ አምላክን የወለድሽ ማርያም ሆይ ስለአቀረብኩልሽ ትንሽ የምስጋና ቃል እናቱ የከርቤ መዐዛ ያለዉን የአፍሽን በረከት ስጭ። ኢሳይያስ ለድኃ ሰዉና ችግር ላገኘዉ እንጀራህን ስጥ ብሏልና።

ስብሐት ለኪ ማርያም በኀልቈ መላእክት ዘአርያም።
ስብሐት ለኪ ማርያም በኀልቈ ጻድቃን ዘገዳም።
ስብሐት ለኪ ማርያም በኀልቈ ርደቱ ለዝናም።
ስብሐት ወክብር ወሰጊድ ለተአምርኪ ዮም።
ወበተአምረ ወልድኪ ተፈሥሐ ኵሉ ዓለም።

እመቤታችን ማርያም ሆይ በሰማይ መላእክት ቊጥር ምስጋና ላንቺ ይገባል።
እመቤታችን ማርያም ሆይ በገዳም በሚኖሩ ጻድቃን ቊጥር ምስጋና ላንቺ ይገባል።
እመቤታችን ማርያም ሆይ በዝናሙ መዉረድ ቊጥር ምስጋና ላንቺ ይገባል።
ክብር ስግደትና ምስጋናም ዛሬ ለተአምርሽ ይገባል።
በልጅሽ ተአምር ዓለሙ ሁሉ ደስ ተሰኝቷልና።

## መቅድመ ተአምረ ኢየሱስ

### ተአምረ ኢየሱስ ከመነበቡ በፊት

### Chant before the reading of Miracles of Jesus

ኢየሱስ ክርስቶስ ጥዑመ ስም ለዘይጼዉዖ። ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብስተ ሕይወት ለዘይበልዖ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ጽዋዓ መድኃኒት ለዘይጸዉዖ። ከመ ይባርኩነ ይፈኑ አርዳኦ ለጸባዒነ ይጽብዖ ወልታሁ ነሢአ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚጠራዉ ስሙ ጣፋጭ ነዉ። ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚበላዉ የሕይወት እንጀራ ነዉ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚሰዋዉ የድኅነት በግ ነዉ። ይባርኩን ዘንድ ደቀ መዛሙርቱን ይላክ። ጋሻ ጦሩን አንሥቶ የሚጣላንን ይጣላዉ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ዘአጽልእቲሁ ምስሌሁ። ወመስቀለ ሞቱ ቅድሜሁ።

አዘቅተ ወይን ገቦሁ ቍርባነ አምልኮ ሥጋሁ። ያብአነ ቤተ መርዓሁ ውስተ ደብተራሁ አመ ይትጋብኡ ለምሳሐ ሥርግዋን ሐራሁ።

ቍስሉ ከእርሱ ጋራ መከራ መስቀሉ በፊቱ የሚታሰብ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው

የወይን አዘቅት ሥጋው የአምልኮ መሥዋዕት የሆነ በቅድስና ልብስና ጌጥ የተሸለሙ ባለሟሎቹ ለምሳ በሚሰበሰቡ ጊዜ ወደ ሙሽርነቱ ድንኳን ያስገባን።

ለጥብሐ ሥጋከ ንሴሰዮ ወለነቅዐ ደምከ ንረውዮ ኢየሱስ ክርስቶስ በግዕ ዘቀራንዮ፤

ለላህይከ ገጽከ ንትሜነይ ከመ ንርአዮ። ውስተ ስያሓ ሱራፊ ለስእለትየ ደዮ። ወበሕማመ ሞትከ አምላካዊ ለቍስልነ አጥዕዮ።

የተሠዋውን ሥጋህን ተመግበን ከደምህ ምንጭ እንረካለን የቀራንዮ በግ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ

ውበትህን እናየዉ ዘንድ እንመኛለን። በሱራፌ ጽዋ ውስጥ ልመናችንን ጨምረዉ። አምላክ ሆይ ለሞት በሚያበቃ ሕማምህ ቍስላችንን አድነዉ።

ለጥብሐ ሥጋከ እጸግቦ ወለነቅዓ ደምከ እስርቦ ኢየሱስ ክርስቶስ በግዕ ርጉዘ ገቦ።

አይሁዳዊ ከሃዲ አሚነ ሥላሴ ዘአልቦ። ኢተወልደ እማርያም ዘይቤለከ እመቦ፤ አህጉራተ (ጽጐጓተ) ዓለም ለይዑድ ከመ ከልብ ርኂቦ።

ተአምረ ኢየሱስ አንብብ

Read the Miracles of Jesus

# ከተአምረ ኢየሱስ በኃላ

## Chant after the Miracles of Jesus is read

አመ ትመጽእ ለኰንኖ መስለ ደመ ገቦ ወአእጋር። አማኅፀንኩ ነፍስየ ውስተ እዴከ ክቡር። ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአ ሰማያት ወምድር። ይትዋቀሱ በእንቲአየ ተኰርዖትከ በበትር። ወተሠይጦትከ ከመ ገብር ለኅዳጥ ብሩር።

ከጎንህና ከእግሮችህ ደም ጋራ ለፍርድ በምትመጣ ጊዜ። በከበረዉ እጅህ ውስጥ ነፍሴን አደራ አስጠበቅሁ። የሰማይና የምድር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራስህን በበትር መመታትህና እንደ ባሪያ በጥቂት ብር መሸጥህ ስለ እኔ ይከራከሩልኝ።

ስብሐት ለከ ኢየሱስ በአፈ ኵሉ ውዱስ።
ስብሐት ለከ ኢየሱስ ቀዳሴ ሥጋ ወነፍስ።
ስብሐት ለከ ኢየሱስ ለዕሩቃን ልብስ።
ስብሐት ለከ ኢየሱስ ዘኢትሠአር ንጉሥ።
ስብሐት ለከ ኢየሱስ ቃለ አብ ቅዱስ።

በሁሉም አፍ የተመሰገንክ ኢየሱስ ሆይ ምስጋና ላንተ ይገባል።
ሥጋንና ነፍስን ያከበርክ ኢየሱስ ሆይ ምስጋና ላንተ ይገባል።
ለታረዙት ልብስ የሆንክ ኢየሱስ ሆይ ምስጋና ላንተ ይገባል።
የማትሻር ንጉሥ ኢየሱስ ሆይ ምስጋና ላንተ ይገባል።
ቅዱስ የአብ አካላዊ ቃል ኢየሱስ ሆይ ምስጋና ላንተ ይገባል።

# ዲያቆን ከወንጌል በፊት

## Deacon Chants Psalms before the Gospel is read

በስድስቱ  ሰዓት መዓልት ዘዓርብ: ትእዛዝ

ከምስባክ አስቀድሞ ይህ ከዚህ በታች ያለው መዝሙር ይባላል። ካህኑ ከመቅደስ ገብቶ እያጠነ ፫ ጊዜ እንደዚህ ይበል።

**ለመስቀልከ ንሰግድ ኦሊቅነ ወለትንሣኤከ ቅድስት ንሴብሕ ኵልነ ይእዜኒ ወዘልፈኒ።**

መምህር ሆይ ለመስቀልህ እንሰግዳለን። ልዩ ለሆነች ትንሣኤህም ሁላችን እናመሰግናለን ዛሬም ዘወትርም።

ሕዝቡም ካህኑን እየተከተሉ እንደዚሁ ይበሉ። So let the people say the same way.

ከዚህም ቀጥሎ ፩ ዲያቆን መዝሙር _____ በወርድ ንባብ ያንብብ

# ዲያቆን ከወንጌል በፊት

# Deacon Chants Psalms before the Gospel is read

ቀነዉኒ እደውየ ወእገርየ።
ወኈለቊ ኵሎ አእፅምትየ።
ቀነዉኒ እደውየ ወእገርየ።

እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ። አጥንቶቼ ሁሉ
ተቈጠሩ ፤ እነርሱም አዩኝ ተመለከቱኝም።

they pierced my hands and my feet. I may tell
all my bones: they look and stare upon me.
Psalm 22:16

ሕዝቡም እንዲሁ ይበሉ።

So let the people say the same way.

ዲያቆኑ:ሃሌ ሉያ ቁሙ ወአጽምዑ ከመ ንኩን ድልዋነ ለመንግሥተ ሰማያት አ እግዚእነወ አምላክነ መሐረነ ወተሣሃለነ ወረሰየነ ድልዋነ ለሰሚዓ ወንጌል ቅዱስ።

ካህኑ: ወንጌል ቅዱስ ዘዜነወ ማቴዎስ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር።

ማቴዎስ ያስተማረውን ቅዱስ ወንጌል ይበል።

Priest says the Gospel of Matthew is the Word of God.

Read the Holy Gospel that Matthew taught.

ሕዝቡ ምሥጋና ላንተ ይገባል ይበሉ።

Let the people say thanksgiving belongs to You.

Read the Gospel of the hour

ማቴዎስ ምዕራፍ ፳፯:፳፯-፵፭ Matthew 27:27-45

ይ.ካ ወንጌል ቅዱስ ዘዜነዉ ማቴዎስ ወማርቆስ ሉቃስ ወዮሐንስ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር።

ወንጌል፥ ማቴዎስ ምዕ. ፳፯ ቁ ፳፯-፵፭ (Mt.27:27-45)

27 በዚያን ጊዜ የገዢው ወታደሮች ኢየሱስን ወደ ገዢው
ግቢ ውስጥ ወሰዱት ጭፍራውንም ሁሉ ወደ እርሱ
አከማቹ። 28 ልብሱንም ገፈው ቀይ ልብስ አለበሱት ፥ 29
ከእሾህም አክሊል ጎንጉነው በራሱ ላይ ፥ በቀኝ እጁም መቃ
አኖሩ ፥ በፊቱም ተንበርክከው። የአይሁድ ንጉሥ ሆይ ፥
ሰላም ለአንተ ይሁን እያሉ ዘበቱበት ፤

[27] Then the soldiers of the governor took Jesus into the common hall, and gathered unto him the whole band of soldiers. [28] And they stripped him, and put on him a scarlet robe. [29] And when they had platted a crown of thorns, they put it upon his head, and a reed in his right hand: and they bowed the knee before him, and mocked him, saying, Hail, King of the Jews!

30 ተፋበትም መቃውንም ይዘው ራሱን መቱት። 31
ከዘበቱበትም በኋላ ቀዩን ልብስ ገፈፉት ፥ ልብሱንም
አለበሱት ሊሰቅሉትም ወሰዱት። 32 ሲወጡም ስምዖን
የተባለው የቀሬናን ሰው አገኙ ፤ እርሱንም መስቀሉን
ይሸከም ዘንድ አስገደዱት። 33 ትርጓሜው የራስ ቅል ስፍራ
ወደሚሆን ጎልጎታ ወደሚባለው ስፍራ በደረሱ ጊዜም ፥ 34
በሐሞት የተደባለቀ የወይን ጠጅ ሊጠጣ አቀረቡለት ፤
ቀምሶም ሊጠጣው አልወደደም።

[30] And they spit upon him, and took the reed, and smote him on the head. [31] And after that they had mocked him, they took the robe off from him, and put his own raiment on him, and led him away to crucify him. [32] And as they came out, they found a man of Cyrene, Simon by name: him they compelled to bear his cross. [33] And when they were come unto a place called Golgotha, that is to say, a place of a skull, [34] They gave him vinegar to drink mingled with gall: and when he had tasted thereof, he would not drink.

35 ከሰቀሉትም በኋላ ልብሱን ዕጣ ጥለው ተካፈሉ ፤ 36
በዚያም ተቀምጠው ይጠብቁት ነበር። 37 ይህ ኢየሱስ
የአይሁድ ንጉሥ ነው የሚል የክሱን ጽሕፈት ከራሱ በላይ
አኖሩ። 38 በዚያን ጊዜ ሁለት ወንበዶች አንዱ በቀኝ አንዱም
በግራ ከእርሱ ጋር ተሰቀሉ። 39የሚያልፉትም ራሳቸውን
እየነቀነቁ ይሰድቡት ነበርና። 40 ቤተ መቅደስን የምታፈርስ
በሦስት ቀንም የምትሠራው ፤ ራስህን አድን ፤
የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ ከመስቀል ውረድ አሉት።
[35] And they crucified him, and parted his garments, casting lots: that it might be fulfilled which was spoken by the prophet, They parted my garments among them, and upon my vesture did they cast lots. [36] And sitting down they watched him there; [37] And set up over his head his accusation written, THIS IS JESUS THE KING OF THE JEWS. [38] Then were there two thieves crucified with him, one on the right hand, and another on the left. [39] And they that passed by reviled him, wagging their heads, [40] And saying, Thou that destroyest the temple, and buildest it in three days, save thyself. If thou be the Son of God, come down from the cross.

41 እንዲሁም ደግሞ የካህናት አለቆች ከጻፎችና
ከሽማግሎች ጋር እየዘበቱበት እንዲህ አሉ። 42 ሌሎችን
አዳነ ፥ ራሱን ሊያድን አይችልም ፤ የእስራኤል ንጉሥ
ከሆነ ፥ አሁን ከመስቀል ይውረድ እኛም እናምንበታለን።
43 በእግዚአብሔር ታምኖአል ፤ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ
ብሎአልና ከወደደውስ አሁን ያድነው። 44 ከእርሱ ጋር
የተሰቀሉት ወንበዶች ደግሞ ያንኑ እያሉ ይነቅፉት ነበር።
45 ከስድስት ሰዓትም ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ
በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ።

[41] Likewise also the chief priests mocking him, with the scribes and elders, said, [42] He saved others; himself he cannot save. If he be the King of Israel, let him now come down from the cross, and we will believe him. [43] He trusted in God; let him deliver him now, if he will have him: for he said, I am the Son of God. [44] The thieves also, which were crucified with him, cast the same in his teeth. [45] Now from the sixth hour there was darkness over all the land unto the ninth hour.

## ከወንጌል በኋላ ካህኑ፦

## After the Reading of the Gospel

ጊዜ ስድስቱ ሰዓት አልበስዎ አልባሲሁ ለኢየሱስ ወወሰድዎ ይስቀልዎ።

**At noon they made Jesus to robe Himself and then took Him to be crucified.**

ስድስት ሰዓት በሆነ ጌታችን ኢየሱስን ልብሱን አልብሰው ይሰቅሉት ዘንድ ወሰዱት።

ይካ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተወልደ እምርያም እምቅድስት ድንግል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ልዩ ሕያው የማይሞት ከንጽሕት ድንግል ማርያም የተወለደ አቤቱ ይቅር በለን።

ልዩ ገዥ ልዩ ኃያል ልዩ ሕያው የማትሞት በዮርዳኖስ ዉኃ የተጠመቅህ በዕንጨት መስቀልም የተሰቀልህ አቤቱ ይቅር በለን።

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has born from the holy Virgin Mary; have mercy upon us, Lord.

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has babelized in Jordan and crucified on the tree of the cross; have mercy upon us, Lord.

ዲያቆኑ:ሃሌ ሉያ ቁሙ ወአጽምዑ ከመ ንኩን ድልዋነ ለመንግሥተ ሰማያት ኦ እግዚእነወ አምላክነ መሐረነ ወተሣሃለነ ወረሰየነ ድልዋነ ለሰሚዓ ወንጌል ቅዱስ።

ካህኑ: ወንጌል ቅዱስ ዘዜነወ ማርቆስ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር።

ማቴዎስ ያስተማረውን ቅዱስ ወንጌል ይበል።

Priest says the Gospel of Mark is the Word of God.

Read the Holy Gospel that Mark taught.

ሕዝቡ ምሥጋና ላንተ ይገባል ይበሉ።

Let the people say thanksgiving belongs to You.

Read the Gospel of the hour

ማርቆስ ምዕራፍ ፲፭:፲፮-፴፫ Mark 15:16-33

## ወንጌል፥ ማርቆስ፥ ምዕ. ፲፭ ቁ. ፲፮-፴፫ (Mk. 15:16-33)

16 ወታደሮችም ፕራይቶሪዮን ወደሚባል ግቢ ውስጥ ወሰዱት ፥
ጭፍራውንም ሁሉ በአንድነት ጠሩ። 17 ቀይ ልብስም
አለበሱት ፥ የእሾህ አክሊልም ጎንጉነው ደፉበት ፤ 18 የአይሁድ
ንጉሥ ሆይ ፥ ሰላም ለአንተ ይሁን እያሉ እጅ ይነሱት ጀመር ፤
19 ራሱንም በመቃመቱት ተፉበትም ፥ ተንበርክከውም ሰገዱለት።
20 ከተዘባበቱበትም በኋላ ቀዩን ልብስ ገፈፉት ፥ ልብሱንም
አለበሱት ፥ ሊሰቅሉትም ወሰዱት።

[16] And the soldiers led him away into the hall, called Praetorium; and they call together the whole band. [17] And they clothed him with purple, and platted a crown of thorns, and put it about his head, [18] And began to salute him, Hail, King of the Jews! [19] And they smote him on the head with a reed, and did spit upon him, and bowing their knees worshipped him. [20] And when they had mocked him, they took off the purple from him, and put his own clothes on him, and led him out to crucify him.

21 አንድ መንገድ አላፊም የእሌክስንድሮስና የሩፎስ አባት
ስምዖን የተባለ የቀሬና ሰው ከገጠር ሲመጣ መስቀሉን ይሸከም
ዘንድ አስገደዱት። 22 ትርጓሜውም የራስ ቅል ስፍራ ወደሚሆን
ጎልጎታ ወደተባለ ስፍራ ወሰዱት። 23 ከርቤም የተቀላቀለበትን
የወይን ጠጅ እንዲጠጣ ሰጡት ፤ እርሱ ግን አልተቀበለም። 24
ሰቀሉትም ፥ ልብሱንም ማን ማን እንዲወስድ ዕጣ ተጣጥለው
ተካፈሉ። 25 በሰቀሉትም ጊዜ ሦስት ሰዓት ነበረ።

[21] And they compel one Simon a Cyrenian, who passed by, coming out of the country, the father of Alexander and Rufus, to bear his cross. [22] And they bring him unto the place Golgotha, which is, being interpreted, The place of a skull. [23] And they gave him to drink wine mingled with myrrh: but he received it not. [24] And when they had crucified him, they parted his garments, casting lots upon them, what every man should take. [25] And it was the third hour, and they crucified him.

26 የክሱ ጽሕፈትም። የአይሁድ ንጉሥ የሚል ተጽፎ
ነበር። 27ከእርሱም ጋር ሁለት ወንበዶች አንዱን በቀኙ
አንዱንም በግራው ሰቀሉ። 28 መጽሐፍም። ከአመፀኞች ጋር
ተቆጠረ ያለው ተፈጸመ። 29 የሚያልፉትም ራሳቸውን
እየነቀነቁ ይሰድቡት ነበርና። ዋ ፥ ቤተ መቅደስን የምታፈርስ
በሦስት ቀንም የምትሠራ ፥ 30 ከመስቀል ወርደህ ራስህን
አድን አሉ።

[26] And the superscription of his accusation was
written over, THE KING OF THE JEWS. [27] And with
him they crucify two thieves; the one on his right hand,
and the other on his left. [28] And the scripture was
fulfilled, which saith, And he was numbered with the
transgressors. [29] And they that passed by railed on
him, wagging their heads, and saying, Ah, thou that
destroyest the temple, and buildest it in three days, [30]
Save thyself, and come down from the cross.

31 እንዲሁም የካህናት አለቆች ደግሞ ከጻፎች ጋር እርስ
በርሳቸው እየተዘባበቱ። ሌሎችን አዳነ ፤ ራሱን ሊያድን
አይችልም ፤ 32 አይተን እናምን ዘንድ የእስራኤል ንጉሥ
ክርስቶስ አሁን ከመስቀል ይውረድ አሉ። ከእርሱም ጋር
የተሰቀሉት ይነቅፉት ነበር። 33 ስድስት ሰዓትም በሆነ
ጊዜ ፥ እስከ ዘጠኝ ሰዓት በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ።
[31] Likewise also the chief priests mocking said
among themselves with the scribes, He saved
others; himself he cannot save. [32] Let Christ the
King of Israel descend now from the cross, that we
may see and believe. And they that were crucified
with him reviled him. [33] And when the sixth hour
was come, there was darkness over the whole land
until the ninth hour.

## ከወንጌል በኋላ ካህኑ፦

## After the Reading of the Gospel

ጊዜ ስድስቱ ሰዓት ቀትር ሶቤሃ ሊቃነ ካህናት ሰቀልዎ ለኢየሱስ በቀራንዮ መካን።

**At that time it was noon when the high priest crucified Jesus at Calvary.**

ስድስት ሰዓት በሆነ ጊዜ ያን ጊዜ ቀትር ነበር የካህናት አለቆች ኢየሱስን በቀራንዮ ሰቀሉት።

ይካ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተወልደ እምርያም እምቅድስት ድንግል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ልዩ ሕያው የማይሞት ከንጽሕት ድንግል ማርያም የተወለደ አቤቱ ይቅር በለን።

ልዩ ገዥ ልዩ ኃያል ልዩ ሕያው የማትሞት በዮርዳኖስ ዉኃ የተጠመቅህ በዕንጨት መስቀልም የተሰቀልህ አቤቱ ይቅር በለን።

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has born from the holy Virgin Mary; have mercy upon us, Lord.

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has babelized in Jordan and crucified on the tree of the cross; have mercy upon us, Lord.

ዲያቆኑ:ሃሌ ሉያ ቁሙ ወአጽምዑ ከመ ንኩን ድልዋነ ለመንግሥተ ሰማያት ኦ እግዚእነወ አምላክነ መሐረነ ወተሣሃለነ ወረሰየነ ድልዋነ ለሰሚዓ ወንጌል ቅዱስ።

ካህኑ: ወንጌል ቅዱስ ዘዜነወ ሉቃስ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር።

ሉቃስ ያስተማረውን ቅዱስ ወንጌል ይበል።

Priest says the Gospel of Luke is the Word of God.

Read the Holy Gospel that Luke taught.

ሕዝቡ ምሥጋና ላንተ ይገባል ይበሉ።

Let the people say thanksgiving belongs to You.

Read the Gospel of the hour

ሉቃስ ፳፫ : ፳፯ - ፵፬ Luke 23:27-44

## ወንጌል፥ ሉቃስ ምዕ ፳፫ ቁ. ፳፯-፵፬ (Luke 23:27-44)

27 ዋይ ዋይ ከሚሉና ሙሾ ከሚያወጡ ሴቶችና ከሕዝቡ እጅግ
ብዙዎች ተከተሉት። 28-29 ኢየሱስ ግን ወደ እነርሱ ዘወር
ብሎ እንዲህ አለ። እናንተ የኢየሩሳሌም ልጆች ፥ ለእኔስ
አታልቅሱልኝ ፤ ዳሩ ግን። መካኖችና ያልወለዱ ማኅፀኖች
ያላጠቡ ጡቶችም ብፁዓን ናቸው የሚሉበት ጊዜ እነሆ
ይመጣልና ለራሳችሁና ለልጆቻችሁ አልቅሱ። 30 በዚያን ጊዜ
ተራራዎችን። በላያችን ውደቁ ፥ ኮረብቶችንም። ሰውሩን ይሉ
ዘንድ ይጀምራሉ ፤ 31 በእርጥብ እንጨት እንዲህ የሚያደርጉ
ከሆኑ ፥ በደረቀውስ እንዴት ይሆን?

[27] And there followed him a great company of people, and of women, which also bewailed and lamented him. [28] But Jesus turning unto them said, Daughters of Jerusalem, weep not for me, but weep for yourselves, and for your children. [29] For, behold, the days are coming, in the which they shall say, Blessed are the barren, and the wombs that never bare, and the paps which never gave suck. [30] Then shall they begin to say to the mountains, Fall on us; and to the hills, Cover us. [31] For if they do these things in a green tree, what shall be done in the dry?

32 ሌሎችንም ሁለት ክፉ አድራጊዎች ደግሞ ከእርሱ ጋር
ይገድሉ ዘንድ ወሰዱ። 33 ቀራንዮ-ም ወደሚባል ስፍራ በደረሱ
ጊዜ ፥ በዚያ እርሱን ክፉ አድራጊዎቹንም አንዱን በቀኝ
ሁለተኛውንም በግራ ሰቀሉ። 34 ኢየሱስም። አባት ሆይ ፥
የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ። ልብሱንም
ተካፍለው ዕጣ ተጣጣሉበት። 35 ሕዝቡም ቆመው ይመለከቱ
ነበር። መኳንንቱም ደግሞ። ሌሎችን አዳነ ፤ እርሱ
በእግዚአብሔር የተመረጠው ክርስቶስ ከሆነ ፥ ራሱን ያድን
እያሉ ያፌዙበት ነበር። 36 ጭፍሮችም ደግሞ ወደ እርሱ
ቀርበው ሆምጣጤም አምጥተው።

[32] And there were also two other, malefactors, led with him to be put to death. [33] And when they were come to the place, which is called Calvary, there they crucified him, and the malefactors, one on the right hand, and the other on the left. [34] Then said Jesus, Father, forgive them; for they know not what they do. And they parted his raiment, and cast lots. [35] And the people stood beholding. And the rulers also with them derided him, saying, He saved others; let him save himself, if he be Christ, the chosen of God. [36] And the soldiers also mocked him, coming to him, and offering him vinegar,

37 አንተስ የአሁድ ንጉሥ ከሆንህ ፥ ራስህን አድን እያሉ
ይዘብቱበት ነበር። 38 ይህ የአይሁድ ንጉሥ ነው ተብሎ
በግሪክና በሮማይስጥ በዕብራይስጥም ፊደል የተጻፈ ጽሕፈት
ደግሞ በእርሱ ላይ ነበረ። 39ከተሰቀሉት ከክፉ አድራጊዎቹም
አንዱ። አንተስ ክርስቶስ አይደለህምን? ራስህንም እኛንም አድን
ብሎ ሰደበው። 40 ሁለተኛው ግን መልሶ። አንተ እንደዚህ ባለ
ፍርድ ሳለህ እግዚአብሔርን ከቶ አትፈራውምን? 41 ስለ
አደረግነውም የሚገባንን እንቀበላለንና በእኛስ እውነተኛ ፍርድ
ነው ፤ ይህ ግን ምንም ክፋት አላደረገም ብሎ ገሠጸው።

[37] And saying, If thou be the king of the Jews, save thyself. [38] And a superscription also was written over him in letters of Greek, and Latin, and Hebrew, THIS IS THE KING OF THE JEWS. [39] And one of the malefactors which were hanged railed on him, saying, If thou be Christ, save thyself and us. [40] But the other answering rebuked him, saying, Dost not thou fear God, seeing thou art in the same condemnation? [41] And we indeed justly; for we receive the due reward of our deeds: but this man hath done nothing amiss.

42 ኢየሱስንም። ጌታ ሆይ ፥ በመንግሥትህ በመጣህ
ጊዜ አስበኝ አለው። 43 ኢየሱስም። እውነት
እልሃለሁ ፥ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው። 44
ስድስት ሰዓትም ያህል ነበረ ፥ ጨለማም እስከ ዘጠኝ
ሰዓት በምድር ሁሉ ላይ ሆነ ፥ ፀሐይም ጨለመ ፥

[42] And he said unto Jesus, Lord, remember me
when thou comest into thy kingdom. [43] And
Jesus said unto him, Verily I say unto thee, To
day shalt thou be with me in paradise. [44] And
it was about the sixth hour, and there was a
darkness over all the earth until the ninth hour.

# ከወንጌል በኋላ ካህኑ፦

## After the Reading of the Gospel

ጊዜ ስድስቱ ሰዓት ዐበጥዎ ለስምዖን ከመ ይፁር መስቀሎ

**At noon they forced Simon to carry His cross.**

ስድስት ሰዓት በሆነ ጊዜ መስቀሉን ይሸከም ዘንድ ስምዖንን አስገደዱት።

ይካ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተወልደ እምርያም እምቅድስት ድንግል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ልዩ ሕያው የማይሞት ከንጽሕት ድንግል ማርያም የተወለደ አቤቱ ይቅር በለን።

ልዩ ገዥ ልዩ ኃያል ልዩ ሕያው የማትሞት በዮርዳኖስ ዉኃ የተጠመቅህ በዕንጨት መስቀልም የተሰቀልህ አቤቱ ይቅር በለን።

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has born from the holy Virgin Mary; have mercy upon us, Lord.

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has babelized in Jordan and crucified on the tree of the cross; have mercy upon us, Lord.

ዲያቆኑ:ሃሌ ሉያ ቁሙ ወአጽምዑ ከመ ንኩን ድልዋነ ለመንግሥተ ሰማያት ኦ እግዚእነወ አምላክነ መሐረነ ወተሣሃለነ ወረሰየነ ድልዋነ ለሰሚዓ ወንጌል ቅዱስ።

ካህኑ: ወንጌል ቅዱስ ዘሰበከ ዮሐንስ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር።

ዮሐንስ ያስተማረውን ቅዱስ ወንጌል ይበል።

Priest says the Gospel of John is the Word of God.

Read the Holy Gospel that John taught.

ሕዝቡ ምሥጋና ላንተ ይገባል ይበሉ።

Let the people say thanksgiving belongs to You.

Read the Gospel of the hour

ዮሐንስ ምዕራፍ ፲፱ : ፲፫ - ፳፯ John 19:13-27

## ወንጌል፥ ዮሐንስ ም. ፲፱ ቁ. ፲፫-፳፯ (John 19:13-27)

13 ጲላጦስም ይህን ነገር ሰምቶ ኢየሱስን ወደ ውጭ
አወጣው ፥ በዕብራይስጥም ገበታ በተባለው ጸፍጸፍ በሚሉት
ስፍራ በፍርድ ወንበር ተቀመጠ። 14 ለፋሲካም የማዘጋጀት ቀን
ነበረ ፤ ስድስት ሰዓትም የሚያህል ነበረ ፤ አይሁድንም። እነሆ
ንጉሣችሁ አላቸው። 15እነርሱ ግን። አስወግደው ፥
አስወግደው ፥ ስቀለው እያሉ ጮኹ። ጲላጦስም። ንጉሣችሁን
ልስቀለውን? አላቸው። የካህናት አለቆችም። ከቄሣር በቀር ሌላ
ንጉሥ የለንም ብለው መለሱለት። 16 ስለዚህ በዚያን ጊዜ
እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጣቸው።

[13] When Pilate therefore heard that saying, he brought
Jesus forth, and sat down in the judgment seat in a place
that is called the Pavement, but in the Hebrew, Gabbatha.
[14] And it was the preparation of the passover, and about
the sixth hour: and he saith unto the Jews, Behold your
King! [15] But they cried out, Away with him, away with him,
crucify him. Pilate saith unto them, Shall I crucify your King?
The chief priest answered, We have no king but Caesar. [16]
Then delivered he him therefore unto them to be crucified.
And they took Jesus, and led him away.

17 ኢየሱስንም ይዘው ወሰዱት ፤ መስቀሉንም ተሸክሞ
በዕብራይስጥ ጎልጎታ ወደ ተባለው የራስ ቅል ስፍራ ወደሚሉት
ወጣ። 18 በዚያም ሰቀሉት ፥ ከእርሱም ጋር ሌሎች ሁለት ፥
አንዱን በዚህ አንዱን በዚያ ኢየሱስንም በመካከላቸው ሰቀሉ።
19 ጲላጦስም ደግሞ ጽሕፈት ጽፎ በመስቀሉ ላይ አኖረው ፤
ጽሕፈቱም። የአይሁድ ንጉሥ የናዝሬቱ ኢየሱስ የሚል ነበረ።
20 ኢየሱስም የተሰቀለበት ስፍራ ለከተማ ቅርብ ነበረና
ከአይሁድ ብዙዎች ይህን ጽሕፈት አነበቡት ፤ በዕብራይስጥና
በሮማይስጥ በግሪክም ተጽፎ ነበር።

[17] And he bearing his cross went forth into a place called the place of a skull, which is called in the Hebrew Golgotha: [18] Where they crucified him, and two other with him, on either side one, and Jesus in the midst. [19] And Pilate wrote a title, and put it on the cross. And the writing was, JESUS OF NAZARETH THE KING OF THE JEWS. [20] This title then read many of the Jews: for the place where Jesus was crucified was nigh to the city: and it was written in Hebrew, and Greek, and Latin.

21 ስለዚህ የአይሁድ ካህናት አለቆች ጲላጦስን። እርሱ። የአይሁድ
ንጉስ ነኝ እንዳለ እንጂ የአይሁድ ንጉሥ ብለህ አትጻፍ አሉት። 22
ጲላጦስም። የጻፍሁትን ጽፌአለሁ ብሎ መለሰ። 23 ጭፍሮችም
ኢየሱስን በሰቀሉት ጊዜ ልብሶቹን ወስደው ለእያንዳንዱ ጭፍራ አንድ
ክፍል ሆኖ በአራት ከፋፈሉት ፤ እጀጠባቡን ደግሞ ወሰዱ። እጀ
ጠባቡም ከላይ ጀምሮ ወጥ ሆኖ የተሠራ ነበረ እንጂ የተሰፋ
አልነበረም። 24 ስለዚህ እርስ በርሳቸው። ለማን እንዲሆን በእርሱ
ዕጣ እንጣጣልበት እንጂ አንቅደደው ተባባሉ። ይህም። ልብሴን እርስ
በርሳቸው ተከፋፈሉ በእጀ ጠባቤም ዕጣ
ተጣጣሉበት የሚለው የመጽሐፍ ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው።

[21] Then said the chief priests of the Jews to Pilate, Write not, The King of the Jews; but that he said, I am King of the Jews. [22] Pilate answered, What I have written I have written. [23] Then the soldiers, when they had crucified Jesus, took his garments, and made four parts, to every soldier a part; and also his coat: now the coat was without seam, woven from the top throughout. [24] They said therefore among themselves, Let us not rend it, but cast lots for it, whose it shall be: that the scripture might be fulfilled, which saith, They parted my raiment among them, and for my vesture they did cast lots. These things therefore the soldiers did.

25 ጭፍሮችም እንዲህ አደረጉ። ነገር ግን በኢየሱስ
መስቀል አጠገብ እናቱ ፥ የእናቱም እኅት ፥ የቀለዮጳም
ሚስት ማርያም ፥ መግደላዊትም ማርያም ቆመው ነበር።
26 ኢየሱስም እናቱን ይወደው የነበረውንም ደቀ መዝሙር
በአጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ እናቱን። አንቺ ሴት ፥ እነሆ ልጅሽ
አላት። 27 ከዚህ በኋላ ደቀ መዝሙሩን። እናትህ እነኋት
አለው። ከዚህም ሰዓት ጀምሮ ደቀ መዝሙሩ ወደ
ቤቱ ወሰዳት።

[25] Now there stood by the cross of Jesus his mother,
and his mother's sister, Mary the wife of Cleophas,
and Mary Magdalene. [26] When Jesus therefore saw
his mother, and the disciple standing by, whom he
loved, he saith unto his mother, Woman, behold thy
son! [27] Then saith he to the disciple, Behold thy
mother! And from that hour that disciple took her unto
his own home.

## ከወንጌል በኋላ ካህኑ፦

## After the Reading of the Gospel

**ጊዜ ስድስቱ ሰዓት ስቀልዎ ለኢየሱስ ማዕከለ ክልኤ ፈያት**

**At noon they crucified Jesus between two thieves.**

ስድስት ሰዓት በሆነ ጊዜ የካህናት አለቆች ጌታ ኢየሱስን በሁለት ወንበዴዎች መካከል ሰቀሉት።

ይካ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተወልደ እምርያም እምቅድስት ድንግል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ልዩ ሕያው የማይሞት ከንጽሕት ድንግል ማርያም የተወለደ አቤቱ ይቅር በለን።

ልዩ ገዥ ልዩ ኃያል ልዩ ሕያው የማትሞት በዮርዳኖስ ዉኃ የተጠመቅህ በዕንጨት መስቀልም የተሰቀልህ አቤቱ ይቅር በለን።

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has born from the holy Virgin Mary; have mercy upon us, Lord.

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has babelized in Jordan and crucified on the tree of the cross; have mercy upon us, Lord.

ከወንጌል በኋላ ካህኑ፦

ጸልዩ በእንተ ጽንዐ ዛቲ የሚባለውን ጸሎት በየክፍሉ ያንብብ ሕዝቡም በየምዕራፉ እግዚኦ ተሣሃለነ (አቤቱ ይቅር በለን) እያሉ እየሰገዱ ይመልሱ።

After the Reading of the Gospel

LITANY PRAYER

The priest prays the Morning Litany prayer, after each part, the congregation responds with Lord have mercy (Egzio Tesehalene) and kneel.

ይካ. ስለዚች ቦታ መጽናት በቅዱሳን አባቶቻችን ስም ስለሚጠሩም ቦታዎችና ገዳማት በውስጣቸውም ስለሚኖሩ ሽማግሎች በጠቅላላም ስለዚህ ዓለም መጠበቅ ጸልዩ ጌታ ከክፉ ሁሉ ይጠብቃቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሠርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

**Priest:** Pray and ask for this church, and all Orthodox churches, the desert monasteries, the elders dwelling therein, and for the peace of the whole world, that the Lord our God may protect us and them from all evil and malice and forgive us our sins.

**People:** Lord have mercy.

ይካ. በዚች ቦታና በሌሎችም ቦታዎች ስለሚገኙ በነፍስ በሥጋ ስለታመሙ አባቶቻችንና ወንድሞቻችን ጸልዩ። ጌታ ለኛም ለነርሱም ሕይወቱን ጤንነቱን ሰጥቶ በጎ ነገርን ያደርግ ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask God for our fathers and brothers who are sick with any sickness whether in this place or in any place, that the Lord our God, may grant them and us health and healing, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በባሕር በየብስ በወንዝ በቀላይ በሌላውም መንገድ ሁሉ ስለሚጓዙ አባቶቻችንና ወንድሞቻችን ጸልዩ። ጌታ በቀና መንገድ መርቶ በሰላም በደስታ ወደ መኖሪያቸዉ ይመልሳቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for our fathers and brothers who are traveling and those who intend to travel in all places. May God aid their ways. Those who are traveling by seas, rivers, lakes, roads or any other means, may the Lord our God guide them, bring them back to their dwelling place in peace, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ከእርሻ ስለሚገኝ ፍሬ ስለ ዛፎችና ስለ ወይኖች በዓለምም ውስጥ ፍሬን ስለምታፈራ ዕንጨት ሁሉ ጸልዩ። ጌታ ባርኮ አብዝቶ ከጥፋትም ጠብቆ ለፍጻሜ ፍሬ ያደርሳቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for the winds of the heaven, the fruits of the earth, all the trees and vineyards and all fruitful trees in the world, that Christ our God may bless them, preserve them, and bring them to completion in peace, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. አምላካችን ክርስቶስ በገዥችና በፈራጆች ፊት ይቅርታንና ምሕረትን እንዲሰጠን ልቡናቸውንም ሁልጊዜ በቸርነቱ እንዲያራራልን ጸልዩ። ኃጢአታችንንም ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask that God may grant us mercy and compassion before the sovereign rulers and incline their hearts with goodness towards us at all times, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በክርስቶስ አምነው ከዚህ በፊት ስለሞቱ ወንድሞቻችንና አባቶቻችን ጸልዩ። እነርሱም የተቀደሱ አባቶቻችን ሊቃነ ጳጳሳትና አባቶቻችን ጳጳሳት አባቶቻችን ኤጲስ ቆጶሳት አባቶቻችን ቆሞሳት አባቶቻችን ቀሳውስት ወንድሞቻችን ዲያቆናት አባቶቻችን መነኮሳትና አባቶቻችን ሕዝባውያን ሌሎችም ከክርስቲያን ወገን በሞት ያረፉት ሁሉ ናቸዉ። ጌታ ዕረፍተ ነፍስን ይሰጣቸው ዘንድ ጸልዩ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚአ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for our fathers and brethren who have fallen asleep and reposed in the faith of Christ since the beginning, our holy fathers the patriarchs, our fathers the metropolitans, our fathers the bishops, our fathers the hegomens, our fathers the priests, our brethren the deacons, our fathers the monks, and our brethren the laymen, and for the repose of all Christians who have fallen asleep, that the Lord our God may repose their souls, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. የክርስቲያን እምነት ላልተፈጸመላቸው ወገኖቻችን ጸልዩ። ጌታ ይባርካቸው ዘንድ እስከ መጨረሻዪቱም ሕቅታ በቀናች ሃይማኖት ያጸናቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for the catechumens, that the Lord our God may bless them, enlighten their hearts, confirm them in the Orthodox faith until the last breath, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ሐዋርያት ስላጸኗትና ስለሰበሰቧት ስለ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ሰላም ጸልዩ። ስለ ሕዝቡም ሁሉ መዳንና ስለ ቦታው ሁሉ መጠበቅ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray for the peace of the church, for the apostles and the gathering of the church. And for the salvation of all the people, and for all the places and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ንዑድ ክቡር ስለሚሆን ስለአባታችን ___________የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሊቀ ጳጳሳቱ አባታችን አቡነ____________ና ብፁዕ አባታችን አቡነ____________ በሕይወት በሞት በኑሮም ስለሚደርስባቸዉ ሁሉ ጸልዩ። ሕይወታቸውን ጠብቆ ለብዙ ዘመን በመንበረ ስብከታቸው ያጸናቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for the life of our honored father, our patriarch Abba (...), the archbishops ______ and ___________, that the Lord God may keep them and confirm them on his throne for many years and long peaceful times, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ስለ አንድነታችንና የቀናች ሃይማኖት ስላላቸው ሕዝበ ክርስቲያን አንድነት ጌታ ይጠብቃቸውና በሰላም ያስፈጸማቸው ዘንድ ጸልዩ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray that the Lord will guard them and make them live in peace by the unity of the Christian community because of our unity and of the true religion and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ለከበረች ቤተ ክርስቲያን መባን ስለሚያቀርቡ ሰዎች ጸልዩ። ጌታ ይባርክላቸው ዘንድ። በሥራቸውም እንዲጸኑ ይረዳቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray for those who offer an offering for the glorious church. That the Lord may bless them. That he might sustain them and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ምእመናንን በየስፍራቸው ሁሉ በቸርነት ስለሚያስቡና ለበጎ ነገር ስለሚደክሙ የቀና ሃይማኖት ስላላቸው ሰዎች ሁሉ ጸልዩ። ጌታ ባርኮ ዋጋቸውን እንዲሰጣቸውና ይቅርታን እንዲያደርግላቸው። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray for every believer who has the true religion and for those who care and labor for the the good of the Church. That the Lord bless them and reward them and forgiveness and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ለቍርባን የሚሆን ስንዴውን ዕጣኑን ዘቢቡን የሚነበብባቸው መጻሕፍትን ሌላውንም የቤተ መቅደስ ዕቃ ሁሉ በመስጠት ስለሚያስቡ ሰዎች ጸልዩ። ጌታ በመንግሥተ ሰማያት የበለጠ ዋጋ ይሰጣቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for those who care for the sacrifices, the oblations, the wine, the oil, the incense, the covering, the books of prayers, the altar vessels, that the Lord our God may reward them in heavenly Jerusalem, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ስማቸውን በያንዳንዳቸው እንድንጠራ ስላዘዙን ስለ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና ስለ ታላላቆች አባቶች ጸልዩ። ጌታ በረከትን ሰጥቶ በባለስልጣኖችና በሹማምት ፊት በፈራጆችም አደባባይ ፍቅርን መወደድን ያድላቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for all for our fathers, the Orthodox metropolitans and bishops in every place who asked us to remember them by name in our prayers, that the Lord God may bless and remember them with His mercy and grant them grace before powerful rulers, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በደዌ ሥጋ በደዌ ነፍስ ለደከሙና ለተቸገሩ ለባልቴቲቱም አባት እናት ለሌላቸው ለድኆቹ ልጆችና ለተጨነቁ ሰዎች ዘር ለዘሩ እርሻ ላረሱ ለሚሸጡ ለሚገዙ ለተጨነቀችም ሰውነት በማናቸውም ቦታ ሁሉ ጸልዩ። ጌታ ራርቶ ይቅር እንዲላቸው። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for the poor, the needy, the afflicted, the weak, the farmers, the traders, the fatherless and all those who are in adversities of any kind, that the Lord our God has kindness on them and us, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በግዞት በምርኮኝነት ተይዘው ለተጨነቁ አገር ለቀው ለተሰደዱ በአጋንንት አሽክላም ለተያዙ ሰዎች ጸልዩ። ጌታ ከግዞት ከምርኮኝነት ያወጣቸው ዘንድ። ይቅርታውንም ሰጥቶ እነርሱንም እኛንም ያድነን ዘንድ። ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for those who are in the distress of prisons and dungeons, and those in captivity or exile, and those who are afflicted by devils, that the Lord our God may free them from their hardships, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ለነፍሳቸው ይቅርታን እየፈለጉ ክቡር በሆነ በዚህ ስፍራ ስለተሰበሰቡ ሁሉ ጸልዩ። የአምላካችን የጌታችን ይቅርታ ፈጥኖ ይደረግላቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for all the souls assembled with us this day, in this holy place, seeking mercy for their souls, that the mercies of the Lord our God may come upon them speedily and us, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በዚህ ዓመት ስለዝናም መዝነም ስለ ባሕርና ስለ ወንዞችም መምላት ጸልዩ። እውነተኛ አምላካችን ክርስቶስ በረከቱን ሰጥቶ እስከ ልካቸው እንዲመላቸው ለምድርም ልምላሜውን ሰጥቶ ደስ እንዲያሰኛት ሥጋዊን ደማዊን ሁሉ በረድኤት እንዲያጸና ለእንስሳትም ሁሉ ድኅነትን እንዲሰጥ ጸልዩ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for the rising of the waters of the rivers this year, that Christ our Lord may bless them and raise them according to their measure, give joy to the face of the earth, sustain us, deliver man and beast, and lift away from the world death, inflation, plagues, annhilation, evacuation, and the sword of the enemies. Grant peace and tranquility in our holy church and raise the state of Christians in every place and around the whole world till the last breath, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በጸሎታችን እናስባቸው ዘንድ አስቡን (አትርሱን) ስላሉን ሰዎች ጸልዩ። እግዚአብሔር በበጎ ያስባቸው ዘንድ በየጊዜውም ይቅር ይላቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for those who requested from us to remember them in our prayers by name, that the Lord our God may remember them according to His goodness at all times, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ይህችን ሳምንት ጌታ በበጎ ይፈጸማት ዘንድ ከኛም የጠላትን መፈታተን አርቆ ሰውነታችንን እንዲያድን ይቅር እንዲለን ጸልዩ። ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray that the Lord will complete this week in peace and to save our bodies from the temptation of our enemy and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ጌታችን አምላካችን ራርቶ ይቅር እንዲለን ልመናችንንም ተቀብሎ ለዚያ ለፋሲካው እንዲያበቃን የትንሣኤውንም ብርሃን በፍጹም ደስታ እንዲያሳየን ጸልዩ። ኃጢአታችንንም ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for this Holy Week of Pascha, of our Good Savior, that He may complete it for us in peace and show us the joy of His holy resurrection in safety and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ክርስቶስ አምላክነ ዘመጽአ ወሐመ በእንቲአነ በሕማማቲሁ ቤዘወነ።

ክርስቶስ አምላካችን ሰዉ ሁኖ መጥቶ ስለእኛ መከራ ተቀበለ በመከራውም አዳነን።

Christ our Lord who came down from heaven, has suffered for us and saved us through His affliction.

ንሰብሖ ወናልዕል ስሞ ኄኡረ እስመ ውእቱ ገብረ መድኃኒተ በዕበየ ሣህሉ።

እርሱ በይቅርታው ገናናነት ድኅነትን አድርጎአልና በአንድነት ፈጽመን ስሙን እናመስግን።

According to His steadfast love, together we praise and exalt His name because he saves us.

ትእዛዝ ሕዝቡ በሁለት ክፍል ሁነው የሚከተለዉን ጸሎት ሁለት ጊዜ በመከታተል አንድ ጊዜ በማስተዛዘል ይበሉት።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን እብኖዲ ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ታዖስ ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ማስያስ ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ኢየሱስ ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ክርስቶስ ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን አማኑኤል ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ትስቡጣ ናይናን ኪርያላይሶን።

ትእዛዝ ከዚህ በኋላ ኪርያላይሶን (41) አርባ አንድ ጊዜ ይባል። ይኸውም በአንድ ወገን ሃያ አንድ በሌላው ወገን ሃያ ጊዜ።

## መልክአ ሕማማት ዘቀትር ሰዓት

### ጸሎት ሰብዓቱ ጊዜያት ዘደረሰ አባ ጊዮርጊስ መምህር ዘጋሥጫ ሰላመ ማርያም ዘሠለስቱ ሰዓት ።

የሰባቱ ጊዜያት የአባ ጊዮርጊስ ጸሎት የስድስት ሰዓት የእመቤታችን ሰላምታ

ሰላም ለኪ አትሮንሰ መለኮት
ሰላም ለኪ ማርያም መንበረ ስብሐት
ሰላም ለኪ ደብተራ ብርሃን ስፍሕት።

ሰላም ለኪ ንግሥተ ይሁዳ
ሰላም ለኪ ፀሐየ መርሙዳ
ሰላም ለኪ ድንግላዊት እም
ዘምስለ ሰጊድ ንኤምኀኪ በል።

ሰላም ለኪ ማርያም ውድስት በአፈ ኲሉ ፍጥረት
ታቦት አንቲ ዘሙሴ ጽላት
ዘሕግ ወዘሥርዓት ሰላም ለኪ።

ገይበ ብሩር ጽሪት ወምቅዳሐ ንጹሕ ሐሊብ
ማርያም መሶብ ዘመና ልሁብ እንተ ጾርኪ ሲሳየ
ሕዝብ ሰላም ለኪ።

ትርሲተ ቤቱ ሠናይ ለነቢይ ሐጌ
ወወለት አንቲ ዘሰሎሞን ሐርጌ
ማርያም ዘመነ ጽጌ ሰላም ለኪ።

እመ ቅድው በግዕ ዘቀተልዎ በግፍዕ
ወደብተራ ስምዕ ዘጳውሎስ ረድእ
ማርያም ዘመነ ፍግዕ ሰላም ለኪ።

ኦርያሬስ ሰማይ ልብስኪ ወአሣእንኪ እብላ
ጽጌ ደንጐላት ቀይሕ ዘምድረ ቈላ
ማርያም ዘመነ ተድላ ሰላም ለኪ።

በመድበለ ማኅበር ጽፉቅ እዌድስኪ በጻሕቅ
ከመ ትምዐድኒ ነገራተ ጽድቅ
ማርያም ዘመነ ዕርቅ ሰላም ለኪ።

ተደንግሎ ሥጋ ወነፍስ ለባሕቲትከ ኮነ
አመኒ በኀል ወለድኪ ሕፃነ
ኢረስሐ ወኢማሰነ ሰላም ለኪ።

እሙ በሊዮ በእንቲአየ ለፍሬ ከርሥኪ እብኖዲ
ላዕሌሁ ምሕረተ ኢታጕንዲ
እመ አሕዘነከ ብእሲ አባዲ
ቤዛ ነፍሱ ንጽሕየ እፈዲ።

ስብሐት ለከ ኦ ዘተቀኖከ ኢየሱስ ጻድቅ ማእከለ ፪ ፈያት።
እንዘ ኢትከውን አንተ ገባሬ እኪት
ከመ ትስዐር ቀኖተ ሞት ስብሐት ለከ።

እፎ ሰፋሕከ አዕዳዊከ ወተሰቀልከ በዕፅ
ዕጽወተ ቀላያት ታርኍ አምሳለ አንቀጽ
እንተ ሖርከ ብሔረ ግብጽ ስብሐት ለከ።

ፀሐይ ብሩህ አሜሃ ጊዜ ቀትር ጸልመ
ወርኅኒ ጽዱል ተመሰለ ደመ
ትንቢት ከመ ቀደመ ስብሐት ለከ።

ለአብርሃም አብ ቀዳሚ ዘአስተርአይኮ ክርስቶስ
ቀትረ ታሕተ ዕፀ ድርስ
ዘሰቀልከ ከመ እቡስ ስብሐት ለከ።

ሐዘነ ማርያም እምከ ነጺረከ ለዘታፈቅሮ ሐዋርያ
ትቤሎ እምከ ነያ
ከመ ትናዝዝ ብዝኅ ብካያ ስብሐት ለከ።

ዘሰአልከ ማየ እምነ ሳምራዊት ብእሲት
ከመ ትፈጽም ኵሎ ነገረ ትስብእት
እንዘ አንተ ማየ ሕይወት።

ሕጽረነ ወትረ እግዚኦ ለደቂቅ ዛቲ ማኅበር
በመስቀልከ መግረሬ ፀር
እምድድቅ ወእምጋኔነ ቀትር
ወእምኵሉ ዘይመጽእ ግብር

ግናይ ለከሙ ሥሉስ ቅዱስ ዕሩያነ አካል ወገጽ
ዘአስተርአይከሙ እንበለ ሕጸጽ
ጊዜ ቀትር ታሕተ ዕፅ ግናይ ለከሙ።

ለንግሥክሙ ሰገደ አብርሃም በርእሱ
ቤተ ገብርክሙ እንዘ ይብል ገፃሡ
አጋዕዝትየ ዘትሤለሱ ግናይ ለከሙ።

በላዕለ ማርያም ድንግል ሥላሴክሙ ተረክበ
በዮርዳኖስ ቅድመ ወበታቦር ካዕበ
ወንጌል ከመ ነበበ ግናይ ለከሙ።

ለቤተ ክርስቲያን ሥላሴ አናቅጺሃ አንትሙ
ሱራፌልኒ በቅዳሴሆሙ
ያኤምሩ ግጻዌክሙ ግናይ ለክሙ።

ፈጣሪያነ ፀሐይ ወወርኀ አጋዕዝትየ ሥላሴ
ዘነጸሩክሙ ኤልያስ ወሙሴ
በክብር ወበዉዳሴ ግናይ ለክሙ።

ጠፈረ ቤትክሙ ማይ ዘኅብሩ
የአኰቴክሙ እንተ ነጸርዎ ኅሩያን አንጋድ
በስኢል ወበሰጊድ ግናይ ለክሙ።

አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ለዝክርክሙ
ሕይወት
ሶበ ከናፍርየ አክሥት
ስመ ዚአክሙ በኵሉ ሰዓት
ይስማዕ እምአፉየ ወይደንግፅ ሞት።

ስብሐት ለእግዚአብሔር ኪያነ ዘፈጠረ ከመ ናምልኮ

ስብሐት ለማርያም እመ አምላክ እግዝእትነ ወመድኃኒትነ

ስብሐት ለመስቀለ ክርስቶስ ዕፀ መድኃኒት ኃይልነ ወፀወንነ።

ጸሎተ ቡራኬ

## የቡራኬ ጸሎት Prayer of Blessing by Priest

ከዚህ በኋላ ሕዝቡ ይቀመጡ። ካህኑ ግን ቆሞ ፊቱን ወደ ሕዝቡ መልሶ የቡራኬውን ጸሎት ይበል።

Let the people seat and the priest will stand and turn his face to the people, and say the prayer of the blessing.

የኢየሱስ ክርስቶስ ማኅበር ቤተ ሰብእ የምትሆኑ ወንድሞቼ ሆይ በዚች በጌታ ማደርያ መሰብሰባችሁ አይሁድ ፋሲካቸውን በአደረጉበት ቀን በመቅናታቸው ለኅጢያተኞች አሳልፈው በሰጡ ጊዜ ጌታችን የተቀበለውን መከራ ሞቱን ኅኑን መወጋቱን ደሙን ማፍሰሱን መስቀሉን እያሰባችሁ ነው።

ስለዚህ እግዚአብሔር ድካማችሁንና ጸሎታችሁን ስግደታችሁንና መዝሙራችሁን ይቀበልላችሁ ከኀሊና ሥጋ የተነሣ በኀሊና መንፈስ የምትሹትን ሁሉ በፈቃዱ ይፈጽምላችሁ።

ተስፋ ትንሣኤውን ይስጣችሁ የደስታውን ቃል ያሰማችሁ በይቅርታው ቸርነት ከመከራው ይሠውራችሁ።

ደቀ መዛሙርቱን እንደጐበኛቸው እንዲሁ እናንተንም ይጎብኛችሁ።

በኀጢአት እንዳትወድቁ ይደግፋችሁ ከሐዘናችሁ ያረጋጋችሁ ከድካማችሁ ያጽናችሁ።

እናንተንም ለማገልገል የተዘጋጀሁ ከምሆን ከእኔ ከወንድማችሁ ጋር።

በሩቅና በቅርብ ካሉ በጸሎታችሁም ከተማጸኑ ወንድሞቻችን ሁሉ ጋራ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጌዜ በደስታ ቀን ከናንተ ጋር አንድ ይሆኑ ዘንድ።

በአባታችሁ ጉባኤ በቀኙ ያቁማችሁ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ተድላ ደስታ ወደሚገኝበት ቤቱ ወደ መንግሥተ ሰማያት ያግባችሁ ለዘላለሙ።

ሕዝቡ ስለ ክርስቶስ ሥጋና ደም አሜን ይደረግልን ይሁን ይሁን ይበሉ።


Η ΣΤΑΥΡΩΣΙΣ

# ግብረ ሕማማት ዓርብ ቀን
# Gibire Himamati Friday

**በዘጠኝ ሰዓት**
**3 PM**

ትእዛዝ ዓርብ በዘጠኘ ሰዓት ካህናት በከበረች በቤተ ክርስቲያን ተሰብስበው የዳዊትን መዝሙር አኮኑ ለእግዚአብሔር (መዝሙር 8፲፩) ከሚለው ጀምሮ እስከ ወአጽገቦሙ መዓረ እምኰኵሕ ተሀበኒ ተምኔትየ ኵሎ አሚረ (መዝሙር 110፡ 10) የሚለው ድረስ ይፀልዩ።

ውዳሴ ማርያምን የሐሙስን ይድገሙ። መሪ በአንድ ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ይበል።

ti’izazi (Order) On Friday 9th hour, let the priests gather in Church to pray the Song of David (Psalms 81: 1) to Psalms 110:10

Let them pray the Thursday Praise of Mary and chant the below hymn.

ትእዛዝ ዓርብ በዘጠኝ ሰዓት ካህናቱ ይፀልዩ መሪዉ በዘጠኝ ሃሌታ ይበል።

በዕዝል ዜማ

በመሪ ወገን አንድ ጊዜ በመከተል በተመሪ ወገን አንድ ጊዜ ለሦስተኛ ጊዜ ደግሞ በጋራ ይባላል።

ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ

ሶበ ሰቀልዎ ሶበ ሰቀልዎ ለእግዚእነ ፀሐይ ጸልመ ወወርኅ ደመ ኮነ ዬ ዬ ዬ አድለቅ ለቀት ምድር ወተከሥቱ መቃብራት።

ጌታችንን በሰቀሉት ጊዜ ፀሐይ ጨለመ ጨረቃ ደም ሆነ ወዮ ወዮ ወዮ ምድር ተናወጠች መቃብሮችም ተከፈቱ።

ሁሉም በአንድነት እየሰገዱ 6 በግራ 6 በቀኝ በአንድ ዓይነት ዜማ አሥራ ሁለት ጊዜ ለከ ኃይል ይበሉ።

This is chanted 12 times (6 times alternating on the right and left aisles of the Church) with prostrations and after each they recite "Our Father..."

ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወዕዘዝ ለዓለም ዓለም።

ኃይል ክብር ጌትነት ገዥነት ለዘላለሙ ለአንተ ይገባል።

For Thine is the power, the glory, the blessing, and the majesty, forever and ever.

ዐማኑኤል አምላኪየ ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወዕዘዝ ለዓለም ዓለም።

ፈጣሪዬ ዐማኑኤል ሆይ ኃይል ክብር ጌትነት ገዥነት ለዘላለሙ ለአንተ ይገባል።

Emmanuel my God, For Thine is the power, the glory, the blessing, and the majesty, forever and ever.

ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ለከ ኃይል ክብር ወስብሐት ወዕዘዝ ለዓለም ዓለም።

ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ኃይል ክብር ጌትነት ገዥነት ለዘላለሙ ለአንተ ይገባል።

O My Lord Jesus Christ, for Thine is the power, the glory, the blessing, and the majesty, forever and ever.

ኃይልየ ወፀወንየ ዉእቱ እግዚእየ እስመ ኮንከኒ ረዳእየ እብል ወአኮቴት

አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ

ኃይሌና አምባ መጠጊያዬ ጌታዬ ነህ ረዳት ሁነኸኛልና በምሥጋና እንዲህ እላለሁ

በሰማያት ያለህ አባታችን ሆይ ስምህ ይመስገን

The Lord is my power, strength and shelter; for you became my Holy Salvation, I say with thanks-giving

Lord’s prayer: Our Father

## አቡነ ዘበሰማያት / Abune Zebesemayat / አባታችን ሆይ / Our Father

አቡነ ዘበሰማያት ይትቀደስ ስምከ ትምጻእ መንግሥትከ ወይኩን ፈቃደከ በከመ በሰማይ ከማሁ በምድር ሲሳየነ ዘለለ ዕለትነ ሀበነ ዮም ንኅድግ ለዘአበሰ ለነ ወጌጋየነ ከመ ንሕነኒ ንኅድግ ለዘአበሰ ለነ ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት አላ አድኅነነ ወባልሐነ እምኲሉ እኩይ እስመ ዚአከ ይእቲ መንግሥት ኃይል ወስብሐት ለዓለመ ዓለም አሜን ።

Abune Zebesemayat Yitkedes Simike Timsa Mengistike Weyikun Fekadeke Bekeme Besemay Kemahu Bemedir Sisayene Zelele Ilitene Habeneyom Hidig Lene Abesane Wegegayene Keme Nihinenee Nihidig Leze Abese Lene Etabiane Igzeeo Wiste Mensut Ala Addihanene Webalihane Imkwulu Ikuy Isme Zeake Yeite Mengist Hayl We Sebhat Lealem alem Amen.

Our Father who art in Heaven, Hallowed be thy name. Thy Kingdom come. Thy will be done On Earth as it is in Heaven. Give us this day our daily bread And forgive us our trespasses As we forgive those who trespass against us And lead us not into temptation But deliver us from evil one in Christ Jesus Our Lord. For thine is the Kingdom The Power and the Glory Forever and ever. Amen.

ለአምላክ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለአምላክነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to God forever and ever.

ለሥሉስ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለሦስትነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to the Holy Trinity forever and ever.

ለማሕየዊ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለአዳኝነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to the Life giver forever and ever.

ለእዘዙ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለጌትነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to His Glory forever and ever.

ለመንግሥቱ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።
ለመንግሥቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።
Honour and Glory be to His Kingdom forever and ever.

ለዕበዩ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።
ለገናናነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።
Honour and Glory be to His Majesty forever and ever.

ለሥልጣኑ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።
ለሥልጣኑ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።
Honour and Glory be to His Power forever and ever.

ለምኲናኑ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።
ለፈራጅነቱ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።
Honour and Glory be to His Authority forever and ever.

ለኢየሱስ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለኢየሱስ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to Jesus forever and ever.

ለክርስቶስ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለክርስቶስ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to Christ forever and ever

ለሕማሙ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለመከራው ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to His Suffering forever and ever

ለመስቀሉ ይደሉ ክብር ወስብሐት ወእዘዝ ለዓለመ ዓለም።

ለመስቀሉ ክብር ምስጋና ጌትነት ለዘላለሙ ይገባል።

Honour and Glory be to the Cross forever and ever

ለከ ይደሉ ኃይል ለከ ይደሉ ስብሐት ወለከ ይደሉ አኮቴት ኦ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዓለመ ዓለም።

ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ለአንተ ከሀሊነት ይገባሃል ለአንተ ክብር ይገባሃል ለአንተ ከምስጋና ይገባሃል ለዘላለሙ።

Power, Glory and blessing be to my Lord Jesus Christ forever and ever.

የዓርብ ፱ ሰዓት ምንባባት

Friday 3 PM Readings

# የተአምረ ማርያም መቅድም
## Introductory Chant to the Miracle of Mary

ምንተኑ አዐስየኪ ዕሴተ። በእንተ ኵሉ ዘገበርኪ ሊተ። ማርያም ሠናይት ዘታፈቅሪ ምሕረተ። ሶበሰ ትትዓቀቢ ዘዚአየ ኀጢአተ። እምኢሐየውኩ አሐተ ሰዓተ።

ምሕረትን የምትወጂ መልካሚቱ ማርያም ስለአደረግሽልኝ ሁሉ ምን ዋጋ እከፍልሻለሁ? የእኔንም ኀጢአት የምትቈጣጠሪ ቢሆን አንዲት ሰዓት እንኳን ባልኖርሁ ነበር።

በሰላመ ገብርኤል መልአክ ኦ እግዚእትየ ማርያም ሰላም ለኪ። ድንግል በኅሊናኪ ወድንግል በሥጋኪ። እመ እግዚአብሔር ጸባኦት ሰላም ለኪ። ቡርክት አንቲ እምአንስት ወቡሩክ ፍሬ ከርሥኪ። ተፈሥሒ ፍሥሕት ኦ ምልእተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ።

እመቤቴ ማርያም ሆይ በመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ ሰላም እልሻለው። በሐሳብሽ ድንግል ነሽ በሥጋሽም ድንግል ነሽ። የአሸናፊ የእግዚአብሔር እናት ሆይ ሰላምታ ላንቺ ይገባል፡፡ ከሴቶች ተለይተሽ አንቺ የተባረክሽ ነሽ። የማህፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው፡፡ ጸጋን የተሞላሽ ሆይ እግዚአብሔር ከአንቺ ጋር ነውና ደስ ይበልሽ።

ተአምረ ማርያም ይነበባል።

Reading of the Miracles of Saint Mary

# ከተአምረ ማርያም በኋላ

## After reading the Miracles of Saint Mary chant the following

ወላዲተ አምላክ ማርያም እንበለ ሰብሳብ ወሩካቤ። በይነ ዘአቀረብኩ ለኪ ንስቲተ ቃለ ይባቤ። ፈትቲ እሙ በረከተ አፉኪ መዓዛ ከርቤ። እስመ ለነዳይ ብእሲ ወለዘረከቦ ምንዳቤ። ኅብስተከ ፈትት ኢሳይያስ ይቤ።

ያለ ርኩሰትና ያለ ሩካቤ አምላክን የወለድሽ ማርያም ሆይ ስለአቀረብኩልሽ ትንሽ የምስጋና ቃል እናቱ የከርቤ መዐዛ ያለዉን የአፍሽን በረከት ስጭ። ኢሳይያስ ለድኃ ሰዉና ችግር ላገኘዉ እንጀራህን ስጥ ብሏልና።

ስብሐት ለኪ ማርያም በኀልቈ መላእክት ዘአርያም።
ስብሐት ለኪ ማርያም በኀልቈ ጻድቃን ዘገዳም።
ስብሐት ለኪ ማርያም በኀልቈ ርደቱ ለዝናም።
ስብሐት ወክብር ወሰጊድ ለተአምርኪ ዮም።
ወበተአምረ ወልድኪ ተፈሥሓ ኵሉ ዓለም።

እመቤታችን ማርያም ሆይ በሰማይ መላእክት ቍጥር ምስጋና ላንቺ ይገባል።
እመቤታችን ማርያም ሆይ በገዳም በሚኖሩ ጻድቃን ቍጥር ምስጋና ላንቺ ይገባል።
እመቤታችን ማርያም ሆይ በዝናሙ መውረድ ቍጥር ምስጋና ላንቺ ይገባል።
ክብር ስግደትና ምስጋናም ዛሬ ለተአምርሽ ይገባል።
በልጅሽ ተአምር ዓለሙ ሁሉ ደስ ተሰኝቷልና።

# መቅድመ ተአምረ ኢየሱስ

## ተአምረ ኢየሱስ ከመነበቡ በፊት

## Chant before the reading of Miracles of Jesus

ኢየሱስ ክርስቶስ ጥዑመ ስም ለዘይጼዉዖ። ኢየሱስ ክርስቶስ ኅብስተ ሕይወት ለዘይበልዖ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ጽዋዓ መድኃኒት ለዘይጸዉዖ። ከመ ይባርኩነ ይፈኑ አርዳኦ ለጸባዒነ ይጽብዖ ወልታሁ ነሢኦ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚጠራዉ ስሙ ጣፋጭ ነዉ። ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚበላዉ የሕይወት እንጀራ ነዉ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ለሚሰዋዉ የድኅነት በግ ነዉ። ይባርኩን ዘንድ ደቀ መዛሙርቱን ይላክ። ጋሻ ጦሩን አንሥቶ የሚጣላንን ይጣላዉ።

ኢየሱስ ክርስቶስ ዘአጽልእቲሁ ምስሌሁ። ወመስቀለ ሞቱ ቅድሜሁ።

አዘቅተ ወይን ገቦሁ ቍርባነ አምልኮ ሥጋሁ። ያብእነ ቤተ መርዓሁ ውስተ ደብተራሁ አመ ይትጋብኡ ለምሳሕ ሥርግዋን ሐራሁ።

ቍስሉ ከእርሱ ጋራ መከራ መስቀሉ በፊቱ የሚታሰብ ኢየሱስ ክርስቶስ ጎኑ

የወይን አዘቅት ሥጋው የአምልኮ መሥዋዕት የሆነ በቅድስና ልብስና ጌጥ የተሸለሙ ባለሟሎቹ ለምሳ በሚሰበሰቡ ጊዜ ወደ ሙሽርነቱ ድንኳን ያስገባን።

ለጥብሓ ሥጋከ ንሴሰዮ ወለነቅዐ ደምከ ንረውዮ ኢየሱስ ክርስቶስ በግዕ ዘቀራንዮ፤

ለላህይከ ገጽከ ንትሜነይ ከመ ንርአዮ። ውስተ ስያሓ ሱራፌ ለስእለትየ ደዮ። ወበሕማመ ሞትከ አምላካዊ ለቊስልነ አጥዕዮ።

የተሠዋውን ሥጋህን ተመግበን ከደምህ ምንጭ እንረካለን የቀራንዮ በግ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ

ውበትህን እናየዉ ዘንድ እንመኛለን። በሱራፌ ጽዋ ውስጥ ልመናችንን ጨምረዉ። አምላክ ሆይ ለሞት በሚያበቃ ሕማምህ ቊስላችንን አድነዉ።

ለጥብሐ ሥጋከ እጸግቦ ወለነቅዓ ደምከ እሰርቦ ኢየሱስ ክርስቶስ በግዕ ርጉዘ ገቦ።

አይሁዳዊ ከሃዲ አሚነ ሥላሴ ዘአልቦ። ኢተወልደ እማርያም ዘይቤለከ እመቦ፤ አህጉራተ (ጽጌዓተ) ዓለም ለይዑድ ከመ ከልብ ርኂቦ።

ተአምረ ኢየሱስ አንብብ

Read the Miracles of Jesus

# ከተአምረ ኢየሱስ በኋላ

## Chant after the Miracles of Jesus is read

አመ ትመጽእ ለኰንኖ መስለ ደመ ገቦ ወአእጋር። አማኅፀንኩ ነፍስየ ውስተ እዴከ ክቡር። ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአ ሰማያት ወምድር። ይትዋቀሱ በእንቲአየ ተኰርዖትከ በበትር። ወተሠይጦትከ ከመ ገብር ለኅዳጥ ብሩር።

ከጎንህና ከእግሮችህ ደም ጋራ ለፍርድ በምትመጣ ጊዜ። በከበረዉ እጅህ ውስጥ ነፍሴን አደራ አስጠበቅሁ። የሰማይና የምድር ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራስህን በበትር መመታትህና እንደ ባሪያ በጥቂት ብር መሸጥህ ስለ እኔ ይከራከሩልኝ።

ስብሐት ለከ ኢየሱስ በአፈ ኵሉ ውዱስ።
ስብሐት ለከ ኢየሱስ ቀዳሴ ሥጋ ወነፍስ።
ስብሐት ለከ ኢየሱስ ለዕሩቃን ልብስ።
ስብሐት ለከ ኢየሱስ ዘኢትሠአር ንጉሥ።
ስብሐት ለከ ኢየሱስ ቃለ አብ ቅዱስ።

በሁሉም አፍ የተመሰገንክ ኢየሱስ ሆይ ምስጋና ላንተ ይገባል።
ሥጋንና ነፍስን ያከበርክ ኢየሱስ ሆይ ምስጋና ላንተ ይገባል።
ለታረዙት ልብስ የሆንክ ኢየሱስ ሆይ ምስጋና ላንተ ይገባል።
የማትሻር ንጉሥ ኢየሱስ ሆይ ምስጋና ላንተ ይገባል።
ቅዱስ የአብ አካላዊ ቃል ኢየሱስ ሆይ ምስጋና ላንተ ይገባል።

**መሪ ካህን**

አ ዘጥዕመ ሞተ በሥጋ።
አ ዘጥዕመ ሞተ በሥጋ።
አ ዘጥዕመ ሞተ በሥጋ።

አምንስቲቲ ሙኪርያ አንቲ ፋሲልያሱ።
አምንስቲቲ ሙአግያ አንቲ ፋሲልያሱ።
አምንስቲቲ ሙዳሱጣ አንቲ ፋሲልያሱ።

ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ
ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ
ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ።

**Remember us, Lord, in Thy kingdom (3X)**

እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ።

**Lord have compassion upon us O! Christ!**

ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ።
ተዘከረነ እግዚኦ ኦሊቅነ።
ተዘከረነ እግዚኦ በውስተ መንግሥትከ።

አስበን አቤቱ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ።
አስበን አቤቱ ቅዱስ ሆይ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ።
አስበን አቤቱ አስታራቂያችን ሆይ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ።

# ዲያቆን ከወንጌል በፊት

# Deacon Chants Psalms before the Gospel is read

## መዝሙር ፷፰ ፡ ፳፩ - ፳፪ Psalm 68:21-22

**መሪ ዲያቆን**

ወወደዩ ሐሞተ ውስተ መብልዕየ።
ወአስተዩኒ ብኂአ ለጽምእየ።
ወወደዩ ሐሞተ ወስተ መብልዕየ።

ለመብሌ ሐሞት ሰጡኝ ፤ ለጥማቴም ሆምጣጤ አጠጡኝ።

They gave me also gall for my meat; and in my thirst they gave me vinegar to drink.

ዲያቆኑ:ሃሌ ሉያ ቁሙ ወአጽምዑ ከመ ንኩን ድልዋነ ለመንግሥተ ሰማያት አ እግዚእነወ አምላክነ መሐረነ ወተሣሃለነ ወረሰየነ ድልዋነ ለሰሚዓ ወንጌል ቅዱስ።

ካህኑ: ወንጌል ቅዱስ ዘዜነወ ማቴዎስ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር።

ማቴዎስ ያስተማረውን ቅዱስ ወንጌል ይበል።

Priest says the Gospel of Matthew is the Word of God.

Read the Holy Gospel that Matthew taught.

ሕዝቡ ምሥጋና ላንተ ይገባል ይበሉ።

Let the people say thanksgiving belongs to You.

Read the Gospel of the hour

ማቴዎስ ምዕራፍ ፳፯:፵፮ - ፶ Matthew 27:46-50

## ወንጌል፥ ማቴዎስ ምዕ. ፳፯ ቁ ፵፮-፶ (Mt. 27:46 – 50)

46 በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ። ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ? ብሎ
በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ይህም። አምላኬ አምላኬ ፥ ስለ ምን
ተውኸኝ? ማለት ነው። 47 በዚያም ከቆሙት ሰዎች ሰምተው።
ይህስ ኤልያስን ይጠራል አሉ። 48 ወዲያውም ከእነርሱ አንዱ
ሮጠ ፤ ሰፍነግም ይዞ ሆምጣጤ ሞላበት ፥ በመቃም አድርጎ
አጠጣው። 49 ሌሎቹ ግን። ተው ፥ ኤልያስ መጥቶ ያድነው እንደ
ሆነ እንይ አሉ። 50 ኢየሱስም ሁለተኛ በታላቅ ድምፅ ጮኾ
ነፍሱን ተወ።

[46] And about the ninth hour Jesus cried with a loud voice, saying, Eli, Eli, lama sabachthani? that is to say, My God, my God, why hast thou forsaken me? [47] Some of them that stood there, when they heard that, said, This man calleth for Elias. [48] And straightway one of them ran, and took a spunge, and filled it with vinegar, and put it on a reed, and gave him to drink. [49] The rest said, Let be, let us see whether Elias will come to save him. [50] Jesus, when he had cried again with a loud voice, yielded up the ghost.

# ከወንጌል በኋላ ካህኑ፦

## After the Reading of the Gospel

ጊዜ ተስዓቱ ሰዓት ጸርሐ ኢየሱስ በቃሉ
ወይቤ ኤሎሄ ኤሎሄ።

**At 3 p.m. Jesus cried saying Eloi Eloi – My God why has Thou forsaken me?**

በዘጠኝ ሰዓት ጌታ ኢየሱስ ቃሉን አሰምቶ ኤሎሄ ኤሎሄ አለ።

ይካ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተወልደ እምርያም እምቅድስት ድንግል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ልዩ ሕያው የማይሞት ከንጽሕት ድንግል ማርያም የተወለደ አቤቱ ይቅር በለን።

ልዩ ገዥ ልዩ ኃያል ልዩ ሕያው የማትሞት በዮርዳኖስ ዉኃ የተጠመቅህ በዕንጨት መስቀልም የተሰቀልህ አቤቱ ይቅር በለን።

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has born from the holy Virgin Mary; have mercy upon us, Lord.

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has babelized in Jordan and crucified on the tree of the cross; have mercy upon us, Lord.

ዲያቆኑ:ሃሌ ሉያ ቁሙ ወአጽምዑ ከመ ንኩን ድልዋነ ለመንግሥተ ሰማያት ኦ እግዚእነወ አምላክነ መሐረነ ወተሣሃለነ ወረሰየነ ድልዋነ ለሰሚዓ ወንጌል ቅዱስ።

ካህኑ: ወንጌል ቅዱስ ዘዜነወ ማርቆስ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር።

ማርቆስ ያስተማረውን ቅዱስ ወንጌል ይበል።

Priest says the Gospel of Mark is the Word of God.

Read the Holy Gospel that Mark taught.

ሕዝቡ ምሥጋና ላንተ ይገባል ይበሉ።

Let the people say thanksgiving belongs to You.

Read the Gospel of the hour

ማርቆስ ፲፭:፴፬-፴፯ Mark 34-37

## ወንጌል፥ ማርቆስ፥ ምዕ. ፲፭ ቁ. ፴፬-፴፯ (Mk. 15:34 – 37)

34 በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ። ኤሎሄ ፥ ኤሎሄ ፥ ላማ ሰበቅታኒ?
ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ ፤ ትርጓሜውም አምላኬ ፥ አምላኬ ፥
ለምን ተውኸኝ? ማለት ነው። 35 በዚያም ከቆሙት ሰዎች
ሰምተው። እነሆ ፥ ኤልያስን ይጠራል አሉ። 36 አንዱም ሮጦ
ሆምጣጤ በሰፍነግ ሞላ በመቃም አድርጎ። ተዉ ፤ ኤልያስ
ሊያወርደው ይመጣ እንደ ሆነ እንይ እያለ አጠጣው። 37
ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኸ ነፍሱንም ሰጠ።

[34] And at the ninth hour Jesus cried with a loud voice, saying, Eloi, Eloi, lama sabachthani? which is, being interpreted, My God, my God, why hast thou forsaken me?
[35] And some of them that stood by, when they heard it, said, Behold, he calleth Elias. [36] And one ran and filled a spunge full of vinegar, and put it on a reed, and gave him to drink, saying, Let alone; let us see whether Elias will come to take him down. [37] And Jesus cried with a loud voice, and gave up the ghost.

## ከወንጌል በኋላ ካህኑ፦

## After the Reading of the Gospel

**ጊዜ ተስዓቱ ሰዓት ከልሐ ኢየሱስ በቃሉ ወአማህጸነ ነፍሶ ሶቤሃ**

**At 3 p.m. Jesus cried out offered up His soul.**

በዘጠኝ ሰዓት ጌታ ኢየሱስ ቃሉን አሰምቶ ተናገረ ያን ጊዜም ነፍሱን አደራ ሰጠ።

ይካ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተወልደ እምርያም እምቅድስት ድንግል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ልዩ ሕያው የማይሞት ከንጽሕት ድንግል ማርያም የተወለደ አቤቱ ይቅር በለን።

ልዩ ገዥ ልዩ ኃያል ልዩ ሕያው የማትሞት በዮርዳኖስ ውኃ የተጠመቅህ በዕንጨት መስቀልም የተሰቀልህ አቤቱ ይቅር በለን።

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has born from the holy Virgin Mary; have mercy upon us, Lord.

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has babelized in Jordan and crucified on the tree of the cross; have mercy upon us, Lord.

ዲያቆኑ፡ሃሌ ሉያ ቁሙ ወአጽምዑ ከመ ንኩን ድልዋነ ለመንግሥተ ሰማያት አ እግዚእነወ አምላክነ መሐረነ ወተሣሃለነ ወረሰየነ ድልዋነ ለሰሚዓ ወንጌል ቅዱስ።

ካህኑ፡ ወንጌል ቅዱስ ዘዜነወ ሉቃስ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር።

ሉቃስ ያስተማረውን ቅዱስ ወንጌል ይበል።

Priest says the Gospel of Luke is the Word of God.

Read the Holy Gospel that Luke taught.

ሕዝቡ ምሥጋና ላንተ ይገባል ይበሉ።

Let the people say thanksgiving belongs to You.

Read the Gospel of the hour

ሉቃስ ምዕራፍ ፳፫:፵፭-፵፮ Luke 23:45-46

## ወንጌል፥ሉቃስ ምዕ ፳፫ ቁ. ፵፭-፵፮ (Luke 23:45 – 46)

45 የቤተ መቅደስም መጋረጃ ከመካከሉ ተቀደደ። 46
ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኾ። አባት ሆይ ፥ ነፍሴን
በእጅህ አደራ እሰጣለሁ አለ። ይህንም ብሎ ነፍሱን
ሰጠ።

**[45] And the sun was darkened, and the veil of the temple was rent in the midst.**
**[46] And when Jesus had cried with a loud voice, he said, Father, into thy hands I commend my spirit: and having said thus, he gave up the ghost.**

## ከወንጌል በኋላ ካህኑ፦

## After the Reading of the Gospel

ጊዜ ተስዓቱ ሰዓት ገአረ ኢየሱስ በቃሉ ወወጽአት መንፈሱ ሶቤሃ።

**At 3 p.m. Jesus cried and His soul departed from His body.**

በዘጠኝ ሰዓት ጌታ ኢየሱስ ቃሉን አሰምቶ ጮኸ ያን ጊዜም ነፍሱ ከሥጋው ተለየች።

ይካ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተወልደ እምርያም እምቅድስት ድንግል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ልዩ ሕያው የማይሞት ከንጽሕት ድንግል ማርያም የተወለደ አቤቱ ይቅር በለን።

ልዩ ገዥ ልዩ ኃያል ልዩ ሕያው የማትሞት በዮርዳኖስ ዉኃ የተጠመቅህ በዕንጨት መስቀልም የተሰቀልህ አቤቱ ይቅር በለን።

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has born from the holy Virgin Mary; have mercy upon us, Lord.

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has babelized in Jordan and crucified on the tree of the cross; have mercy upon us, Lord.

ዲያቆኑ:ሃሌ ሉያ ቁሙ ወአጽምዑ ከመ ንኩን ድልዋነ ለመንግሥተ ሰማያት አ እግዚእነወ አምላክነ መሐረነ ወተሣሃለነ ወረሰየነ ድልዋነ ለሰሚዓ ወንጌል ቅዱስ።

ካህኑ: ወንጌል ቅዱስ ዘሰበከ ዮሐንስ ቃለ ወልደ እግዚአብሔር።

ዮሐንስ ያስተማረውን ቅዱስ ወንጌል ይበል።

Priest says the Gospel of John is the Word of God.

Read the Holy Gospel that John taught.

ሕዝቡ ምሥጋና ላንተ ይገባል ይበሉ።

Let the people say thanksgiving belongs to You.

Read the Gospel of the hour

ዮሐንስ ምዕራፍ ፲፱:፳፰-፴ John 9:28-30

## ወንጌል፥ ዮሐንስ ም. ፲፱ ቁ. ፳፰-፴ (John 19:28 – 30)

28 ከዚህ በኋላ ኢየሱስ አሁን ሁሉ እንደተፈጸመ አውቆ
የመጽሐፉ ቃል ይፈጸም ዘንድ። ተጠማሁ አለ። 29 በዚያም
ሆምጣጤ የሞላበት ዕቃ ተቀምጦ ነበር ፤ እነርሱም
ሆምጣጤውን በሰፍነግ ሞልተው በሁሶፕም አድርገው ወደ አፉ
አቀረቡለት። 30 ኢየሱስም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ።
ተፈጸመ አለ ፥ ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ።

**[28] After this, Jesus knowing that all things were now accomplished, that the scripture might be fulfilled, saith, I thirst. [29] Now there was set a vessel full of vinegar: and they filled a spunge with vinegar, and put it upon hyssop, and put it to his mouth. [30] When Jesus therefore had received the vinegar, he said, It is finished: and he bowed his head, and gave up the ghost.**

## ከወንጌል በኋላ ካህኑ፦

## After the Reading of the Gospel

**ጊዜ ተስዓቱ ሰዓት አጽነነ ርእሶ ኢየሱስ ወይቤ ተፈጸመ ኩሉ።**

**At 3 p.m. Jesus bowed His head and said everything is finished.**

በዘጠኘ ሰዓት ጌታ ኢየሱስ ራሱን ዘንበል (ዘለስ) አድርጎ ሁሉ ተፈጸመ አለ።

ይካ ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተወልደ እምርያም እምቅድስት ድንግል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ሕያው ዘኢይመውት። ዘተጠምቀ በዮርዳኖስ ወተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል ተሣሃለነ እግዚኦ።

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ኃያል ቅዱስ ልዩ ሕያው የማይሞት ከንጽሕት ድንግል ማርያም የተወለደ አቤቱ ይቅር በለን።

ልዩ ገዥ ልዩ ኃያል ልዩ ሕያው የማትሞት በዮርዳኖስ ዉኃ የተጠመቅህ በዕንጨት መስቀልም የተሰቀልህ አቤቱ ይቅር በለን።

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has born from the holy Virgin Mary; have mercy upon us, Lord.

Holy God, holy Mighty, holy living, Immortal, who has babelized in Jordan and crucified on the tree of the cross; have mercy upon us, Lord.

ከወንጌል በኋላ ካህኑ፦

ጸልዩ በእንተ ጽንዐ ዛቲ የሚባለውን ጸሎት በየክፍሉ ያንብብ ሕዝቡም በየምዕራፉ እግዚኦ ተሣሃለነ (አቤቱ ይቅር በለን) እያሉ እየሰገዱ ይመልሱ።

After the Reading of the Gospel

LITANY PRAYER

The priest prays the Morning Litany prayer, after each part, the congregation responds with Lord have mercy (Egzio Tesehalene) and kneel.

ይካ. ስለዚች ቦታ መጽናት በቅዱሳን አባቶቻችን ስም ስለሚጠሩም ቦታዎችና ገዳማት በውስጣቸውም ስለሚኖሩ ሽማግሎች በጠቅላላም ስለዚህ ዓለም መጠበቅ ጸልዩ ጌታ ከክፉ ሁሉ ይጠብቃቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for this church, and all Orthodox churches, the desert monasteries, the elders dwelling therein, and for the peace of the whole world, that the Lord our God may protect us and them from all evil and malice and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በዚች ቦታና በሌሎችም ቦታዎች ስለሚገኙ በነፍስ በሥጋ ስለታመሙ አባቶቻችንና ወንድሞቻችን ጸልዩ። ጌታ ለኛም ለነርሱም ሕይወቱን ጤንነቱን ሰጥቶ በጎ ነገርን ያደርግ ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask God for our fathers and brothers who are sick with any sickness whether in this place or in any place, that the Lord our God, may grant them and us health and healing, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በባሕር በየብስ በወንዝ በቀላይ በሌላውም መንገድ ሁሉ ስለሚጓዙ አባቶቻችንና ወንድሞቻችን ጸልዩ። ጌታ በቀና መንገድ መርቶ በሰላም በደስታ ወደ መኖሪያቸዉ ይመልሳቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for our fathers and brothers who are traveling and those who intend to travel in all places. May God aid their ways. Those who are traveling by seas, rivers, lakes, roads or any other means, may the Lord our God guide them, bring them back to their dwelling place in peace, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ከእርሻ ስለሚገኝ ፍሬ ስለ ዛፎችና ስለ ወይኖች በዓለምም ውስጥ ፍሬን ስለምታፈራ ዕንጨት ሁሉ ጸልዩ። ጌታ ባርኮ አብዝቶ ከጥፋትም ጠብቆ ለፍጻሜ ፍሬ ያደርሳቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for the winds of the heaven, the fruits of the earth, all the trees and vineyards and all fruitful trees in the world, that Christ our God may bless them, preserve them, and bring them to completion in peace, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. አምላካችን ክርስቶስ በገዦችና በፈራጆች ፊት ይቅርታንና ምሕረትን እንዲሰጠን ልቡናቸውንም ሁልጊዜ በቸርነቱ እንዲያራራልን ጸልዩ። ኃጢአታችንንም ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask that God may grant us mercy and compassion before the sovereign rulers and incline their hearts with goodness towards us at all times, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በክርስቶስ አምነው ከዚህ በፊት ስለሞቱ ወንድሞቻችንና አባቶቻችን ጸልዩ። እነርሱም የተቀደሱ አባቶቻችን ሊቃነ ጳጳሳትና አባቶቻችን ጳጳሳት አባቶቻችን ኤጲስ ቆጶሳት አባቶቻችን ቆሞሳት አባቶቻችን ቀሳውስት ወንድሞቻችን ዲያቆናት አባቶቻችን መነኮሳትና አባቶቻችን ሕዝባውያን ሌሎችም ከክርስቲያን ወገን በሞት ያረፉት ሁሉ ናቸዉ። ጌታ ዕረፍተ ነፍስን ይሰጣቸው ዘንድ ጸልዩ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for our fathers and brethren who have fallen asleep and reposed in the faith of Christ since the beginning, our holy fathers the patriarchs, our fathers the metropolitans, our fathers the bishops, our fathers the hegomens, our fathers the priests, our brethren the deacons, our fathers the monks, and our brethren the laymen, and for the repose of all Christians who have fallen asleep, that the Lord our God may repose their souls, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. የክርስቲያን እምነት ላልተፈጸመላቸው ወገኖቻችን ጸልዩ። ጌታ ይባርካቸው ዘንድ እስከ መጨረሻዪቱም ሕቅታ በቀናች ሃይማኖት ያጸናቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for the catechumens, that the Lord our God may bless them, enlighten their hearts, confirm them in the Orthodox faith until the last breath, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ሐዋርያት ስላጸኗትና ስለሰበሰቧት ስለ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ሰላም ጸልዩ። ስለ ሕዝቡም ሁሉ መዳንና ስለ ቦታው ሁሉ መጠበቅ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray for the peace of the church, for the apostles and the gathering of the church. And for the salvation of all the people, and for all the places and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ንዑድ ክቡር ስለሚሆን ስለአባታችን ____________የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ሊቀ ጳጳሳቱ አባታችን አቡነ_____________ና ብፁዕ አባታችን አቡነ_____________ በሕይወት በሞት በኑሮም ስለሚደርስባቸዉ ሁሉ ጸልዩ። ሕይወታቸውን ጠብቆ ለብዙ ዘመን በመንበረ ስብከታቸው ያጸናቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for the life of our honored father, our patriarch Abba (...), the archbishops ______ and ____________, that the Lord God may keep them and confirm them on his throne for many years and long peaceful times, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ስለ አንድነታችንና የቀናች ሃይማኖት ስላላቸው ሕዝበ ክርስቲያን አንድነት ጌታ ይጠብቃቸውና በሰላም ያስፈጸማቸው ዘንድ ጸልዩ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray that the Lord will guard them and make them live in peace by the unity of the Christian community because of our unity and of the true religion and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ለከበረች ቤተ ክርስቲያን መባን ስለሚያቀርቡ ሰዎች ጸልዩ። ጌታ ይባርክላቸው ዘንድ። በሥራቸውም እንዲጸኑ ይረዳቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray for those who offer an offering for the glorious church. That the Lord may bless them. That he might sustain them and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ምእመናንን በየስፍራቸው ሁሉ በቸርነት ስለሚያስቡና ለበጎ ነገር ስለሚደክሙ የቀና ሃይማኖት ስላላቸው ሰዎች ሁሉ ጸልዩ። ጌታ ባርኮ ዋጋቸውን እንዲሰጣቸውና ይቅርታን እንዲያደርግላቸው። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray for every believer who has the true religion and for those who care and labor for the the good of the Church. That the Lord bless them and reward them and forgiveness and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ለቍርባን የሚሆን ስንዴውን ዕጣኑን ዘቢቡን የሚነበብባቸው መጻሕፍትን ሌላውንም የቤተ መቅደስ ዕቃ ሁሉ በመስጠት ስለሚያስቡ ሰዎች ጸልዩ። ጌታ በመንግሥተ ሰማያት የበለጠ ዋጋ ይሰጣቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for those who care for the sacrifices, the oblations, the wine, the oil, the incense, the covering, the books of prayers, the altar vessels, that the Lord our God may reward them in heavenly Jerusalem, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ስማቸውን በያንዳንዳቸው እንድንጠራ ስላዘዙን ስለ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትና ስለ ታላላቆች አባቶች ጸልዩ። ጌታ በረከትን ሰጥቶ በባለስልጣኖችና በሹማምት ፊት በፈራጆችም አደባባይ ፍቅርን መወደድን ያድላቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for all for our fathers, the Orthodox metropolitans and bishops in every place who asked us to remember them by name in our prayers, that the Lord God may bless and remember them with His mercy and grant them grace before powerful rulers, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በደዌ ሥጋ በደዌ ነፍስ ለደከሙና ለተቸገሩ ለባልቴቲቱም አባት እናት ለሌላቸው ለድኆቹ ልጆችና ለተጨነቁ ሰዎች ዘር ለዘሩ እርሻ ላረሱ ለሚሸጡ ለሚገዙ ለተጨነቀችም ሰውነት በማናቸውም ቦታ ሁሉ ጸልዩ። ጌታ ራርቶ ይቅር እንዲላቸው። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for the poor, the needy, the afflicted, the weak, the farmers, the traders, the fatherless and all those who are in adversities of any kind, that the Lord our God has kindness on them and us, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በግዞት በምርኮኝነት ተይዘው ለተጨነቁ አገር ለቀው ለተሰደዱ በአጋንንት አሽክላም ለተያዙ ሰዎች ጸልዩ። ጌታ ከግዞት ከምርኮኝነት ያወጣቸው ዘንድ። ይቅርታውንም ሰጥቶ እነርሱንም እኛንም ያድነን ዘንድ። ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for those who are in the distress of prisons and dungeons, and those in captivity or exile, and those who are afflicted by devils, that the Lord our God may free them from their hardships, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ለነፍሳቸው ይቅርታን እየፈለጉ ክቡር በሆነ በዚህ ስፍራ ስለተሰበሰቡ ሁሉ ጸልዩ። የአምላካችን የጌታችን ይቅርታ ፈጥኖ ይደረግላቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for all the souls assembled with us this day, in this holy place, seeking mercy for their souls, that the mercies of the Lord our God may come upon them speedily and us, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በዚህ ዓመት ስለዝናም መዝነም ስለ ባሕርና ስለ ወንዞችም መምላት ጸልዩ። እውነተኛ አምላካችን ክርስቶስ በረከቱን ሰጥቶ እስከ ልካቸው እንዲመላቸው ለምድርም ልምላሜውን ሰጥቶ ደስ እንዲያሰኛት ሥጋዊን ደማዊን ሁሉ በረድኤት እንዲያጸና ለእንስሳትም ሁሉ ድኅነትን እንዲሰጥ ጸልዩ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚአ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for the rising of the waters of the rivers this year, that Christ our Lord may bless them and raise them according to their measure, give joy to the face of the earth, sustain us, deliver man and beast, and lift away from the world death, inflation, plagues, annhilation, evacuation, and the sword of the enemies. Grant peace and tranquility in our holy church and raise the state of Christians in every place and around the whole world till the last breath, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. በጸሎታችን እናስባቸው ዘንድ አስቡን (አትርሱን) ስላሉን ሰዎች ጸልዩ። እግዚአብሔር በበጎ ያስባቸው ዘንድ በየጊዜውም ይቅር ይላቸው ዘንድ። የኛንም ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for those who requested from us to remember them in our prayers by name, that the Lord our God may remember them according to His goodness at all times, and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ይህችን ሳምንት ጌታ በበጎ ይፈጸማት ዘንድ ከኛም የጠላትን መፈታተን አርቆ ሰውነታችንን እንዲያድን ይቅር እንዲለን ጸልዩ። ኃጢአታችንን ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray that the Lord will complete this week in peace and to save our bodies from the temptation of our enemy and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ይካ. ጌታችን አምላካችን ራርቶ ይቅር እንዲለን ልመናችንንም ተቀብሎ ለዚያ ለፋሲካው እንዲያበቃን የትንሣኤውንም ብርሃን በፍጹም ደስታ እንዲያሳየን ጸልዩ። ኃጢአታችንንም ያስተሥርይልን።

ይሕ. እግዚኦ ተሣሃለነ። (አቤቱ ይቅር በለን)

Priest: Pray and ask for this Holy Week of Pascha, of our Good Savior, that He may complete it for us in peace and show us the joy of His holy resurrection in safety and forgive us our sins.

People: Lord have mercy.

ክርስቶስ አምላክነ ዘመጽአ ወሐመ በእንቲአነ በሕማማቲሁ ቤዘወነ።

ክርስቶስ አምላካችን ሰዉ ሁኖ መጥቶ ስለእኛ መከራ ተቀበለ በመከራውም አዳነን።

Christ our Lord who came down from heaven, has suffered for us and saved us through His affliction.

ንሰብሖ ወናልዕል ስሞ ኅቡረ እስመ ውእቱ ገብረ መድኃኒተ በዕበየ ሣህሉ።

እርሱ በይቅርታው ገናናነት ድኅነትን አድርጎአልና በአንድነት ፈጽመን ስሙን እናመስግን።

According to His steadfast love, together we praise and exalt His name because he saves us.

ትእዛዝ ሕዝቡ በሁለት ክፍል ሁነው የሚከተለዉን ጸሎት ሁለት ጊዜ በመከታተል አንድ ጊዜ በማስተዛዘል ይበሉት።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን እብኖዲ ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ታዖስ ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ማስያስ ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ኢየሱስ ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ክርስቶስ ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን አማኑኤል ናይናን ኪርያላይሶን።

ኪርያላይሶን ኪርያላይሶን ትስቡጣ ናይናን ኪርያላይሶን።

ትእዛዝ ከዚህ በኋላ ኪርያላይሶን (41) አርባ አንድ ጊዜ ይባል። ይኸውም በአንድ ወገን ሃያ አንድ በሌላው ወገን ሃያ ጊዜ።

# መልክአ ሕማማት ዘተሰዓቱ ሰዓት

## ጸሎት ሰብዓቱ ጊዜያት ዘደረሰ አባ ጊዮርጊስ መምህር ዘጋሥጫ ሰላመ ማርያም ዘሠለስቱ ሰዓት ።

## የሰባቱ ጊዜያት የአባ ጊዮርጊስ ጸሎት ዘተሰዓቱ ሰዓት የእመቤታችን ሰላምታ

ሰላም ለኪ መንጦላዕተ ገርዜን ሰላም ለኪ
ማርያም አንቀፀ ብርሃን ሰላም ለኪ
ምግባአ ቅዱሳን ሰላም ለኪ
ሙዳየ ቁርባን ሰላም ለኪ
መዐዛ ዕጣን ሰላም ለኪ
ታቦተ ኪዳን ሰላም ለኪ።

ማርያም እክል ሰላም ለኪ
መጽንዒተ ኃይል ሰላም ለኪ
ቅብዐ ብርሃኑ ለገጽ ሰላም ለኪ

ስቴ ወይን ዘነፈርዓጽ ሰላም ለኪ።

ሠርጐ ክብር ወአራዝ ሰላም ለኪ

ወመቅደስ ቤተ ትእዛዝ ሰላም ለኪ

ዘአሣእንኪ ወርኀ ሰላም ለኪ

ወዘአክሊልኪ ኀሐ ጽባሕ ሰላም ለኪ።

ደመና ዝናም ንጽሕት ሰላም ለኪ

ዘይከውን ለቅድሳት ሰላም ለኪ።

ወለተ ኢያቄም ወሐና ሰላም ለኪ

ስርጉት በቅድስና ሰላም ለኪ

ደብረ መቅደሱ ለኖኅ ሰላም ለኪ

ዘአድኃንኪዮ እማየ አይኅ ሰላም ለኪ።

ኀይመተ አብርሃም አብ ሰላም ለኪ

ዘኮንኪ ከመ ተድባብ ሰላም ለኪ።

ቤዛዊተ ኵሉ ዓለም ሰላም ለኪ።

ሰፋኒት በአርያም ሰላም ለኪ።

ሥርጉት በቅድስና ሰላም ለኪ።

ያስምዐኒ ቃለ ፍሥሓ ጊዜ በሐዝን አስቆቁ ፤ ሣህልኪ

ይምጻእ እምሥራቁ ለእሳተ ሐዘን እስከ ይቈርር ሞቁ

ማርያም ለኃጥእ ጽድቁ።

ስብሐት ለከ አምላኪየ አምላኪየ ነጽረኒ ወትረ ወኢትኅድገኒ ዘልፈ ፤እስመ አንተ ትቤ እንዘ ትከሥት አፈ ፤ ትፈጽም ሕገ ተጽሕፈ ስብሐት ለከ።

ጊዜ ትወፅእ ነፍስከ እስከ ይሰማዕ ኵለሄ ፤ አ ዘትቤ ኤሎሄ ኤሎሄ ፤ኢየሱስ አምላክ ርኅራኄ ስብሐት ለከ።

ከመ ታስትየነ ለነ ደመ ገቦከ ነባቤ ፤ አንተ አስተዩከ ሐሞተ ወከርቤ ጸማእኩ በጊዜ ትቤ ስብሐት ለከ።

ድኅረ ሰለጥከ መዊተ በመልዕልተ ቅዱስ ጸልቦ ፤ እንዘ
ኃጢአት ለዕሌከ አልቦ ፤ ኢየሱስ ርጉዘ ገቦ ስብሐት ለከ።

ስታየ ጽሙአን ይኩን ወዘያረስዕ ትካዘ
ማይ ምስለ ደም ውኅዘ
ገቦከ ጊዜ ተረግዘ ስብሐት ለከ።

ኖላዊነ ኄር ወዐቃቢነ ጽኑዕ
አንተ ተሰቀልከ መልዕልተ ምሥዋዕ
ኢየሱስ ቤዛ አባግዕ ስብሐት ለከ።

ድጎረ ሰለጥከ መዊተ በመልዕልተ ቅዱስ ጸልቦ ፤ እንዘ

ኃጢአት ላዕሌከ አልቦ ፤ ኢየሱስ ርጉዘ ገቦ ስብሐት ለከ።

ስታየ ጽሙአን ይኩን ወዘ,ያረሰዕ ትካዘ

ማይ ምስለ ደም ውኅዘ

ገቦከ ጊዜ ተረግዘ ስብሐት ለከ።

ኖላዊነ ኄር ወዐቃቢነ ጽኑዕ

እንተ ተሰቀልከ መልዕልተ ምሥዋዕ

ኢየሱስ ቤዛ አባግዕ ስብሐት ለከ።

ተወከፍ ሊተ እግዚእ ከመ ቍርባን ጥሉል ፤ በበሱባዔ
እንዘ እከፍል ፤ ዘአቅረብኩ ለከ ኍልቈ ኢዮቤል ፤
ስብሐታተ ከመ አንሰ እክል።

ግናይ ለክሙ ሥሉስ ቅዱስ ነገሥተ ሰብዓቱ አብያት ፤
እለ በላዕክሙ ውሳጤ ኀይመት አሐደ ኅብስተ ትሥልሥት
ግናይ ለክሙ።

ድኅረ በላዕክሙ ላሕመ እንበይነ ፍቅረ ሰብእ ፍጹም ፤
ዘበኃይልክሙ ሐይወ ላሕም ፤ ሥላሴ ክቡራነ ስም ግናይ
ለክሙ።

ከመ ባሕር ስፉሕ ወከመ እሳት ጽዱል ፤
ዘሀለወክሙ ትሥልስተ አካል ፤
ሥላሴ ነገሥተ ኃይል ግናይ ለክሙ።

ዘኢትቀሥፉ ወትረ ወኢትትመዐዑ ዘልፈ ፤
እንዘ ሰብእ ይገብር ኃጣውአ እልፈ ፤
በመጽሐፍ ከመ ተጽሕፈ ግናይ ለክሙ።

ድኅረ ልቡናሁ ጼወወ ፍቅረ አሐቲ ብእሲት ፤ ለዘወፅአ
ረድእ እምሃይማኖት ፤ዘመሐርክምዎ በዕሥራ ዕለት ፤መሐሩነ
ሥላሴ ነገሥት።

ስብሐት ለእግዚአብሔር ኪያነ ዘፈጠረ ከመ ናምልኮ

ስብሐት ለማርያም እመ አምላክ እግዝእትነ ወመድኃኒትነ

ስብሐት ለመስቀለ ክርስቶስ ዕፀ መድኃኒት ኃይልነ ወፀወንነ።

ጸሎተ ቡራኬ

## የቡራኬ ጸሎት Prayer of Blessing by Priest

ከዚህ በኋላ ሕዝቡ ይቀመጡ። ካህኑ ግን ቆሞ ፊቱን ወደ ሕዝቡ መልሶ የቡራኬውን ጸሎት ይበል።

Let the people seat and the priest will stand and turn his face to the people, and say the prayer of the blessing.

የኢየሱስ ክርስቶስ ማኅበር ቤተ ስብእ የምትሆኑ ወንድሞቼ ሆይ በዚች በጌታ ማደርያ መሰብሰባችሁ አይሁድ ፋሲካቸውን በአደረጉበት ቀን በመቅናታቸው ለኅጢያተኞች አሳልፈው በሰጡ ጊዜ ጌታችን የተቀበለውን መከራ ሞቱን ጎኑን መወጋቱን ደሙን ማፍሰሱን መስቀሉን እያሰባችሁ ነው።

ስለዚህ እግዚአብሔር ድካማችሁንና ጸሎታችሁን ስግደታችሁንና መዝሙራችሁን ይቀበልላችሁ ከኅሊና ሥጋ የተነሣ በኅሊና መንፈስ የምትሹትን ሁሉ በፈቃዱ ይፈጽምላችሁ።

ተስፋ ትንሣኤውን ይስጣችሁ የደስታውን ቃል ያሰማችሁ በይቅርታው ቸርነት ከመከራው ይሠውራችሁ።

ደቀ መዛሙርቱን እንደጐበኛቸው እንዲሁ እናንተንም ይጎብኛችሁ።

በኃጢአት እንዳትወድቁ ይደግፉችሁ ከሐዘናችሁ ያረጋጋችሁ ከድካማችሁ ያጽናችሁ።

እናንተንም ለማገልገል የተዘጋጀሁ ከምሆን ከእኔ ከወንድማችሁ ጋር።

በሩቅና በቅርብ ካሉ በጸሎታችሁም ከተማጸኑ ወንድሞቻችን ሁሉ ጋራ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ በደስታ ቀን ከናንተ ጋር አንድ ይሆኑ ዘንድ።

በአባታችሁ ጉባኤ በቀኙ ያቁማችሁ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ተድላ ደስታ ወደሚገኝበት ቤቱ ወደ መንግሥተ ሰማያት ያግባችሁ ለዘላለሙ።

ሕዝቡ ስለ ክርስቶስ ሥጋና ደም አሜን ይደረግልን ይሁን ይሁን ይበሉ።